ይህ የጥናት መምሪያ የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በተሰማሩ ሰዎች ላይ ሲሆን የጥናት መምሪያውን በብዙ የተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይቻላል። በግል የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትም ሆነ በአዋቂዎች የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጠቀም ይቻላል።

ይሁንና መምሪያው የተዘጋጀው በትምህርተ–መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ ነው። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ መምህርን ተክቶ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርተ–መለኮት ወይም አገልግሎት ለተማሪው ጠቃሚ ትምህርቶችን ያስተላልፋል። ተማሪው በዚህ የጥናት መጽሐፍ እየተመራ ጥያቄዎችን በመመለስና የተማረውን ከሕይወቱ ጋር በማዛመድ በቀን አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ያሳልፋል።

ከሁሉም የላቀ ትርፍ የሚገኘው ደግሞ ተማሪዎቹ በሳምንት አንድ ቀን ተሰባስበው የተማሩትን ሲከልሱና የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ካሉበት ሁኔታ ጋር እንደሚዛመድ ሲወያዩ ነው።

# የቤተ ክርስቲያን አመራር

## በክህሎት መምራት

## እና ሌሎችም የአመራር ጉዳዮች

### ክፍል 2

### በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ

### (ት.መ.ማ) መልክ የተዘጋጀ

### የጥናት መምሪያና ማብራሪያ

ከቲም ፌሎስ

August 30, 2006

ትርጉም:- በግርማዊ

አርትዖት:- በዘነበ ገብረሐና

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All rights reserved.

አሳታሚ } የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
Publisher SIM Publications

የፖ.ሣ.ቁጥር } 127፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
P.O.Box Addis Ababa, ETHIOPIA

ስልክ ቁጥር } 011-349-3252፣ 011 - 349-3069፣
Tel. 011-551-2973, 011 - 550 - 3899

ፋክስ } 011 - 551 - 1242
Fax

ኢ-ሜይል } SIMmedia@ethionet.et
E-mail

የመጀመሪያ እትም - 2002 ዓ.ም
First Printing - 2009



# ማውጫ

ትምህርት ስምንት ....................4
ትምህርት ዘጠኝ ....................89
ትምህርት አሥር ....................158
ትምህርት አሥራ አንድ ....................233
ትምህርት አሥራ ሁለት ....................314
ትምህርት አሥራ ሦስት ....................399
ትምህርት አሥራ አራት ....................490
ትምህርት አሥራ አምስት ....................577
ትምህርት አሥራ ስድስት ....................666
ትምህርት አሥራ ሰባት ....................739
ትምህርት አሥራ ስምንት ....................801
ትምህርት አሥራ ዘጠኝ ....................871
ትምህርት ሃያ ....................931
ትምህርት ሃያ አንድ ....................1011
ትምህርት ሃያ ሁለት ....................1111
ዋቢ መጻሕፍት ....................1194

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Evangelical
Baptist Church
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

# ክፍል 2: ቤተ ክርስቲያንን በክህሎት መምራት

# ትምህርት ስምንት

## አንደኛ ቀን ቤተ ክርስቲያንን በክህሎት መምራት

ተፈራወርቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለብዙ ዓመታት በድቁና አገልግሏል። እስፈላጊ በሆነው መንገድ ሁሉ ለማገልገል ጊዜውን በፈቃደኝነት ሲሠዋ ነበር የኖረው። ሰዎች፣ የእገልጋይ መንፈስ ያለውና መንፈሳዊ ባሕርያትን የተለባሰ በመሆኑ፣ ደስ ይሰኙበት ነበር። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ እንዲሆን መረጡት። ተፈራወርቅ ከዚህ በፊት በትልቅ የመሪነት ቦታ ላይ ተቀምጦ አያውቅም ነበር። ለእግዚአብሔር ሥራ ጸሎት ወሳኝ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ በሁሉም ስብሰባዎች ላይ ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር ለብዙ ሰዓታት ይጸልዩ ነበር። የተመረጠው በምእመናን መሆኑን ስለሚያውቅ፣ ሰዎቹ የፈለጉትን ለማድረግ ይጥር ነበር። አንድ ሰው አንድ ጥያቄ ይዞ በሚመጣበት ሰዓት፣ ጥያቄውን ለማሟላት ደፋ ቀና ይል ነበር። ለዚህ ሰውዬ የሚደረገው ነገር እጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጠቀሜታ መኖሩን ቢጠራጠርም፣ ይህንኑ ከማድረግ ወደ ኋላ እይልም ነበር። ብዙም ሳይቆይ፣ ሰዎች በእርሱ ተስፋ ቆረጡ። የሽማግሌዎች ስብሰባ በሚገባ የተደራጀ እልነበረም። ተፈራወርቅ ሰው እንዳያስቀይም ስለሚፈራ ጠንከር ያለ ውሳኔ እድርጎ አያውቅም። የሽማግሌዎቹንም ውሳኔ ለምእመናን አያሳውቅም ነበር። በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለእግዚአብሔር ክብር ምን ለማድረግ እየሞከረች እንዳለች የሚያውቅ ሰው እልነበረም።

ተፈራወርቅ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ስለሚፈራ፣ ስኬታማ መሪ ለመሆን ከፈለገ እንዴት «መምራት» እንዳለበት መማር ያለበት መሆኑን ይረዳ ነበር። እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ለማገልገል የሚፈልግ መንፈሳዊ ሰው መሆን ብቻ በቂ እልነበረም። ለእግዚአብሔር ቤተሰብ አንድነትንና ዓላማን የሚሰጥ መንፈሳዊ አመራር በክህሎት መከናወን እንዳለበት ተፈራወርቅ ተገነዘበ።



መጻሕፍትን በማንበብ፣ ከሌሎች ስኬታማ መሪዎች ጋር በመነጋገር፣ እና እዳዲስ ነገሮችን በመሞከር የመሪነት ክህሎቶቹን አሻሻለ። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የፈለጋቸውን ነገሮች እንዲገነዘቡ ለመርዳት ቻለ። ሰዎች በራሳቸው ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ዕድገት መከሰቱንና ሌሎች ያልዳኑ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መጨመራቸውን ሲመለከቱ ደስ እላቸው። ሰዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል አብረን መሥራት እለብን በሚል እሳብ ላይ በማተኮራቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታዩ የነበሩት በርካታ ትንንሽ አለመስማማቶች እየከሰሙ ሄዱ።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ክህሎት ሳይኖረው የመሪነትን ሚና በመጫወቱ በእረኝነት የሚመራቸው ለዎች ሲቸገሩ ያየህበት ሁኔታ ካለ ግለጽ። ለ) የክህሎት መጉደል በአመራር ላይ ሊያስከትል የሚችላቸውን አንዳንድ ችግሮች ዘርዝር። ሐ) በክህሎት የታገዘ አመራር ለቤተ ክርስቲያን አንድነትን ሊያመጣ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ።

የሚያሳዝነው፣ በቤተ ክርስቲያኖቻችን እንደ ተፈራወርቅ ያሉ መሪዎች ብዙ ናቸው። እግዚአብሔርን ለማገልገል እየፈለጉ በክህሎት ባለመምራታቸው ምክንያት ምእመኖቻቸውን የሚያሳዝኑ ብዙ መሪዎችና አገልጋዮች አሉ። የእገልጋይ መሪነት ትክክለኛ አመለካከት መያዝ ወይም የመንፈሳዊ መሪን ባሕርይ መያዝ ብቻም በቂ አይደለም። ብዙ መጸለይ ወይም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መላበሱ ብቻ በቂ እይደለም። ደካማ እመራርን ወደ ሕይወት-ለዋጭ እመራር የሚቀይረው ክህሎት ያለው መሪ መሆን መቻል ነው።

2ኛ ጥያቄ:- መዝ. 78:72ን አንብብ። ዳዊት ስኬታማ መንፈሳዊ መሪ እንዲሆን ያስቻሉትን ሁለት መለያዎች ግለጽ።

ከብሉይ ኪዳን ታላላቅ መሪዎች አንዱ የሆነው ዳዊት ስኬታማ የሆነው እመራሩ በሁለት ነገሮች የተገለጸ በመሆኑ ነው። በመጀመሪያ፣ ዳዊት ሕዝቡን የመራው «በልበ ቅንነት» ነበር።

የመሪነት መሠረቱ የመሪው ባሕርይ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ምእመኖቻቸው መንፈሳዊና በሳል እንዲሆኑ ለማድረግ የሚችሉበት ትልቁ መንገድ ራሳቸው መንፈሳዊ ብስለትን ተ ላብሰው መገኘታቸው ነው። መንፈሳዊ ብስለት ያለው የቤተ ክርስቲያን መሪ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ምን እንደ ሆነ በአርአያነት ለማሳየት የሚያስችሉ መንፈሳዊ ባሕርያት አሉት። መንፈሳዊ መሪዎች እንደ ጳውሎስ፣ «እኔ ኢየሱስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» የማለት ድፍረት ይኖራቸዋል (1ኛ ቆሮ. 11:1)። በቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ያሉትን የአመራር ቀውሶች መፍታት ካለብን፣ መጀመሪያ እግዚአብሔር ከመሪዎቹ የሚጠብቃቸውን መንፈሳዊ ባሕርያት የተላበሱ መሪዎች መፍጠር አለብን። ስለ እነዚህ መንፈሳዊ ባሕርያትና ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ስለሚፈጽሟቸው ኃጢአቶች በመጀመሪያው ክፍል ጥናታችን ውስጥ አጥንተናል። (የቤተ ክርስቲያን አመራር፡- የመንፈሳዊ መሪ ባሕርይ ከሚለው የትምህርት መጽሐፍ ክፍል አንድን አንብብ።)

ሁለተኛ፣ መዝ. 78:72 ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ «በእጁ ብልሃት» እንደ መራቸው ይነግረናል። በቤተ ክርስቲያን አመራር ሁለተኛ መጽሐፍ ውስጥ አንድ መሪ ለውጤታማ አመራር ሊጠቀምባቸው ስለሚገባቸው የተለያዩ ክህሎቶች እንነጋገራለን። ምንም እንኳን እግዚአብሔር እነዚህ ክህሎቶች የሌሉትን መንፈሳዊ መሪ በመጠቀም ሰዎችን ሊመራ ቢችልም፣ እነዚህን የመሪነት ክህሎቶች ቢያውቅ አገልግሎቱ ይጎለብታል። ክህሎቶችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተለያዩ ሁኔታዎች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ዝርዝር ማብራሪያዎችን እንሰጣለን። ይኸኛው የመጽሐፉ ክፍል መሪዎች አመራራቸውን ለማሻሻል በተደጋጋሚ ሊያጠኑት የሚገባው «መምሪያ» ዓይነት ነው።

በዚህ የትምህርት መጽሐፍ ሦስተኛ ክፍል ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያስቧቸው የሚገቧቸውን አንዳንድ ጉዳዮችን እናቀርባለን። ምንም እንኳን እነዚህ ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ በቤተ እምነት መሪዎች የሚወሰኑ ቢሆኑም፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎችም ሊረዷቸው ይገባል። ይህም እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

[ማስታወሻ፡- ወደ ሰርግ ቤት በምንሄድበት ጊዜ፣ በአብዛኛው የተለያዩ ዓይነት የምግብ ዓይነቶች የሚቀርቡበት ቡፌ ይኖራል። በዚህ ጊዜ የምንወደውን ምግብ እያነሣን የማንወደውን ትተን እናልፋለን። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ክፍል ሁለትንና ሦስትን በምታጠናበት ጊዜ የምትፈልጋቸውና እምብዛም የማትፈልጋቸው ትምህርቶች ያጋጥሙሃል። እንዲያውም ከደራሲው አስተሳሰብ ጋር የማትስማማበት ቦታም ሊያጋጥምህ ይችላል። የእግዚአብሔርን ቃል አንብብና እግዚአብሔር ለአንተና ለቤተ ክርስቲያናችሁ የሚፈልገው ምን እንደ ሆነ እንዲያሳውቅህ ጠይቀው። ጠቃሚ የሆኑትን ትምህርቶች በጥንቃቄ እያሰባሰብክ ተጠቀምባቸው። ከትምህርቱ ጋር ካልተስማማህ ደግሞ፣ ለቤተ ክርስቲያናችሁ ሊጠቅሙ የሚችሉ ሌሎች ትምህርቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ሞክር። የቀረውን ከአንተ ጋር የማይስማማ የሌላ ሰው አመለካከት አድርገህ በመቁጠር ተወው።]

## በክህሎት ማገልገል እግዚአብሔርን ያስከብራል

1. እግዚአብሔር ሊያገለግሉት የሚፈልጉ ሰዎች ክህሎት እንዲኖራቸው ይፈልጋል።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- ዘጸአ. 26:1፣ 31:1-11፣ 35:10፣ 35:30-36:2 አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ለእግዚአብሔር ክህሎት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ያስተምሩናል? ለ) እነዚህ ጥቅሶች የመገናኛው ድንኳን ሠራተኞች ክህሎት ያላቸው ወንዶችና ሴቶች መሆን እንዳለባቸው በተደጋጋሚ የሚገልጹት ለምን ይመስልሃል? ሐ) ክህሎት የሚመጣው ከየት ነው? |

ሀ. እግዚአብሔር አማኞች ለእርሱ የሚያከናውኗቸው ተ ግባራት ሁሉ በክህሎትና በጥራት እንዲከናወኑ ይሻል። የአገልጋይ

አገልግሎቱ ክህሎትን የተሳበሰ መሆኑ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲያውም፣ እግዚአብሔር የሚኖርበትና ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት የመገናኛ ድንኳን እንዲሠራ በፈለገ ጊዜ፣ የመገናኛውን ድንኳን በጥበብ ይሠሩ ዘንድ እግዚአብሔር ለሁለት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንደ ሰጣቸው እናነብባለን። ሰዎቹ የመገናኛውን ድንኳን አሳምረው በመሥራታቸው እግዚአብሔር ከብሯል። ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ ለሰዎቹ ክህሎትን የሰጣቸው ቀደም ሲል ሞክረው የማያውቁትን ሥራ እንዲያከናውኑ ላይሆን ይችላል። ይልቁንም፣ ልምድ የነበራቸው ሠራተኞች የመገናኛውን ድንኳን በበለጠ ብልሃት አሳምረው እንዲሠሩ ኃይልን ሰጣቸው። በኋላ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ታሳቅ ቤተ መቅደስ በሚሠራበት ጊዜ ሥራውን ሰማከናወን ብልሃተኛ ሰዎችን በጥንቃቄ መርጧል (1ኛ ነገሥ. 5)። ይህ ለእግዚአብሔር አንድን ነገር በግድየለሽነት መሥራቱ በቂ እንዳልሆነ ያሳየናል። ይልቁን፣ የሰጠንን ሥራ በብልሃት በማከናወን እናስከብረዋለን።

ሁላችንም አንድን ነገር ያለ ክህሎት ጥራቱን ባልጠበቀ መንገድ በሚሠራና ያንኑ ነገር በክህሎት በሚሠራ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ሳንታዘብ አልቀረንም። ቤት መሥራት የሚችሉ ብዙ ሰምች አሉ። ነገር ግን ክህሎት ስለሚጎድላቸው፣ ቤቱ ቀንጆ ላይሆን ይችላል። በሮቹና መስኮቶቹ ቀጥተኛ ላይሆኑ፣ በአግባቡ ላይዘጉና ላይከፈቱ ይችላሉ። ነገር ግን ክህሎት ያስው አናጺ ተመሳሳይ ቤት በሚሠራበት ጊዜ በሮችና መስኮቶች ለዓይን እንዲስቡና በትክክል እንዲገጥሙ ያደርጋል። ቤቱን በምንመለከትበት ጊዜ ለጥራት ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ ክህሎት ያለው ሰው እንደ ሠራው እንረዳለን። ስለ ምግብ አሠራርም ተመሳሳይ ነገር መናገር ይቻላል። ብዙ ሴቶች የሚሠሩት ምግብ ደህና የሚባል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጣት የሚያስቆረጥም ምግብ የሚሠሩ ጥቂት ክህሎት ያላቸው ሴቶች አሉ። ምርጫው ቢሰጠን፣ ቆንጆ ወጥ



የሚሠሩትን ሴቶች ምግብ ብንበላ ደስ ይለናል። ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ ከእዚህኛው ምግብ ቤት ያኛው ይሻላል የምንለው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ክህሎት ያላቸውና የሌላቸው ሰባኪዎች መኖራቸውን እናጤናለን። ምንም እንኳን ክህሎት ከሌላቸው ሰባኪምች ብዙ ነገሮችን ልንማር ብንችልም፣ ክህሎት ያለውን ሰባኪ በምንሰማበት ጊዜ ስብከቱን ለሰዓታት ቁጭ ብለን ምንም ሳይታወቀን ልንሰማና ያስተማረውንም ትምህርት ለረዥም ጊዜ ልናስታውስ እንችላለን። በዚህ ዓይነት ሰባኪ የተላለፈው መልእክት ግልጽ ነው። ሰባኪው በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ታሪኮችና ቀልዶች አዋዝቶ ስለሚያቀርብ፣ ትምህርቱ ይጥማል። የቤተ ክርስቲያን አመራርን ጨምሮ፣ በብዙ የሕይወት ገጠመኞች ውስጥ ተራውን ነገር ወደ ላቀና አስደሳች ነገር የሚያደርሰው ክህሎት ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ከልባችን ለማስደሰት ከፈለግን፣ አገልግሎታችንን ሁሉ በክህሎት ማከናወን መማር አለብን። እንደ ሽማግሌዎች በክህሎት ልንመራ፣ እንደ መጋቢዎች በክህሎት ልንሰብክ፣ እንደ አስተማሪዎች የሰንበት ትምህርቶችን በክህሎት ልናስተምር፣ እንደ ወንጌላውያን በክህሎት ልንመሰክር ይገባል። ክህሎት ያላቸው መዘምራንና የሙዚቃ ተጨዋቾች እንዲኖሩን ያስፈልጋል። ታላቁ አምላካችንን በክህሎት ለማገልገል አለመማሩ ግድየለሾችና ለእግዚአብሔር አክብሮት የሌለን መሆናችንን ያሳያል። እግዚአብሔር እንደ ምግብና መጠጥ ያሉ ቀላል ነገሮች እርሱን በሚያስከብር መንገድ እንዲካሄዱ ከፈለገ (1ኛ ቆሮ. 10:31 አንብብ)፣ ለእርሱ የምናቀርበው አገልግሎት በክህሎት እንዲከናወን የሚፈልግ መሆኑ የሚያጠራጥር አይሆንም።

4ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች በክህሎትና ያለ ክህሎት በሚሰጡት አገልግሎት ያለውን ልዩነት እንዴት እንዳጤንህ ግለጽ። ለ) ሥራቸውን በክህሎት ይሠራሉ የምትላቸውን ሽማግሌዎች፣ ሰባኪዎችና ወንጌላውያን ስሞች

ዘርዝር:: ሐ) እነዚህ አገልጋዮች አገልግሎታቸው የበለጠ ያማረ እንዲሆን ከሌሎች የተለየ ምን እንደሚያደርጉ ተናገር::

5ኛ ጥያቄ:- ምሳሌ 22:29፣ መክ. 10:10ን አንብብ:: ሀ) ሰሎሞን ስለ ክህሎት (ጥበብ) ጥቅም ምን አለ? ለ) በሕይወትህ ወይም በሌሎች ሰዎች ሕይወት እነዚህ ጥቅሶች እውነት መሆናቸውን እንዴት እንዳረጋገጥክ ግለጽ:: ሐ) ክህሎት ያለው የቤተ ክርስቲያን መሪ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያሳድግ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ::

ሰ. በክህሎት የሚሠሩ ሰዎች የኋላ ኋላ ያለ ክህሎት ከሚሠሩት የበለጠ ክብርና የአገልግሎት በሮች ይገጥሟቸዋል:: ሰሎሞን ክህሎት (ጥበብ) ያለው ሰው ንጉሥን የማገልገል ዕድል በማግኘት ከሌሎች የበለጠ እንደሚከበር ገልጾአል:: ይህ ማለት ክህሎት ያለው ሰው ከሌለው በላይ ይፈለጋል ማለት ነው:: ጥበብ ከአንድ ሰው ቤተሰብ፣ ጎሳ ወይም የትምህርት ደረጃ በላይ አስፈላጊ ነው:: ሰሎሞን ሰዎች ብዙ ትምህርት ኖሮት ጥበብ ከሌለው ሰው ይልቅ፣ አነስተኛ ትምህርትና ክህሎት ያለውን ሰው እንደሚመርጡ ይናገራል:: እግዚአብሔር የአገልግሎት በሮችን በመክፈት የሚያሳድገው በክህሎት የሚያገለግሉትን ሰዎች ነው::

ሐ. ክህሎት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የማገልገሉን ተግባር ቀለል ያደርገዋል:: ንጉሥ ሰሎሞን ክህሎት አንድ ሥራ በቀላሉና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እንደሚያደርግ ተናግሯል:: ይህም ስለታም መጥረቢያ ከዱልዱሙ በበለጠ እንጨትን እንደሚቆርጥ ነው:: (መክ. 10:10ን አንብብ::) በተመሳሳይ መንገድ፣ አገልግሎትን በክህሎት ማካሄድ የመንፈሳዊ መሪን አገልግሎት የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል:: የተወሰኑ ክህሎቶችን ብንማር መሪዎች የሚጋፈጧቸው ብዙ ችግሮች ይወገዳሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ ውጤታማ የመግባባት ክህሎት ሰዎች በአመራራችን ላይ እምኔታ እንዲኖራቸው በማድረግ ምእመናን አመራራችንን ተቀብለው አዳዲስ ነገሮችን እንዲያከናውኑ



ያግዛቸዋል:: ስለሆነም፣ ክህሎት ያለው መሪ መሆናችን እግዚአብሔር ወደ ላቀ የመሪነት ደረጃ እንዲያደርሰን ማስቻል ብቻ ሳይሆን፣ የአመራር ሥራችን ቀለል እንዲል ያደርገዋል:: እግዚአብሔር ብዙዎቻችንን በአመዛኙ አስቸጋሪ በሆነ የመሪነት ስፍራ ላይ ስላስቀመጠን፣ የአመራርን ክህሎቶች ማጥናትና ከሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅብናል:: ይህም በዚህ የቤተ ክርስቲያን አመራር ሁለተኛ መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናው ይሆናል::

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚካሄዱትን አገልግሎቶች ዘርዝር:: ለእያንዳንዱ አገልግሎት ጎን በክህሎት ወይም በጥራት፣ ወይም ደግሞ ያለ ክህሎት ወይም ያለ ጥራት መከናወኑን ግለጽ:: ለ) በክህሎት በሚካሄዱና ያለ ክህሎት በሚካሄዱ አገልግሎቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ያለ ክህሎት በሚካሄዱ አገልግሎቶች የሚከብር ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: መ) ሰዎች እግዚአብሔርን በክህሎት እንዲያገለግሉ ብዙዎች ስለ አገልግሎት የያዟቸውና መለወጥ ያለባቸው አመለካከቶች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) 1ኛ ቆሮ. 10:31ን አንብብ:: ጳውሎስ እንደ መብላትና መጠጣት ያሉ ትናንሽ ነገሮች እንኳን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መካሄድ አለባቸው ሲል ምን ማለቱ ነው? ረ) እንደ መብላትና መጠጣት ወይም የቤተ ክርስቲያን አመራር ያሉትን ነገሮች እንዴት እግዚአብሔርን በማያስከብር መንገድ ልንጠቀም እንደምንችል ግለጽ:: ሰ) እንደ መብላትና መጠጣት የመሳሰሉትን ነገሮች እንዴት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ልናደርግ እንደምንችል ግለጽ:: ሸ) አንድ ነገር እግዚአብሔርን በሚያስከብር ወይም በማያስከብር መንገድ እንዲካሄድ የሚያደርገው ምንድን ነው?

2. እግዚአብሔርን በጥልቀት ለማገልገል፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአመራር ክህሎታቸውን ለማሳደግ ተግተው መሥራት አለባቸው::

ሀ. በ1ኛ ቆሮ. 10:31 ጳውሎስ እንደ መብላትና መጠጣት ያሉ መሠረታዊ ነገሮች ሳይቀር ለእግዚአብሔር ክብር መደረግ አለባቸው ይላል:: የምናደርገው ነገር እግዚአብሔርን እንዲያስከብር

ወይም እንዳያስከብር የሚያደርገው ምንድን ነው? አንድ ነገር እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዲካሄድ ሁለት ዓበይት ነገሮች መሟላት አለባቸው:: የመጀመሪያው አንድን ነገር የምናደርግበት <u>ዓላማ</u> ነው:: ዓላማችን ሌሎችን ከመርዳት ይልቅ የራሳችንን ፍላጎቶች በሟሟላት ላይ ያተኮረ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ሊያስከብር አይችልም:: በ1ኛ ቆሮ. 10 አማኞች ለጣዖት የተሠዋ ምግብ መብላት ይቻላል ወይ? በሚል ጥያቄ ላይ ይከራከሩ ነበር:: ጳውሎስ ሥጋውን መብላቱ ምስክርነታቸውን ወይም የሌላውን ሰው እምነት የሚጎዳ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን እንደማያስከብር ነገራቸው:: በተመሳሳይ መንገድ፣ በአመራር ውስጥ አንድን ነገር የምናደርግበት ምክንያት እግዚአብሔር በአመራራችን መደሰት አለመደሰቱን ይወስናል:: (ለምሳሌ ያህል፣ በከተማይቱ ውስጥ ከሁሉም የሚበልጥ ሕንጻ እንዲኖረን ወይም ከሚወዳደረን ቤተ እምነት ለመብለጥ በማሰብ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ብንገነባ፣ ይህን ያደረግነው ለራሳችን ክብር እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ክብር አለመሆኑ ግልጽ ነው::)

ሁለተኛ፣ አንድን ነገር እግዚአብሔር በሰጠን <u>ችሎታ መጠን</u> ማድረግ አለብን:: ጳውሎስ ሰዎች የተለያዩ ችሎታዎች፣ ወይም የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዳሏቸው ይናገራል:: እግዚአብሔር እንደ ስብከት፣ ማስተማር ወይም አመራር በመሳሰሉት መንፈሳዊ ስጦታዎች ለሁላችንም የሰጠው ችሎታ እኩል አይደለም:: እነዚህ ስጦታዎች ከሰው ሰው የሚለያዩ ናቸው:: ነገር ግን እግዚአብሔር በስጦታችን ልክ እንድንሠራለት ይፈልጋል:: በአመራር ብዙ ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ ስጦታ ከሰጠን፣ ይህንን ስጦታ በመጠቀም ስጦታው ከሌላው ሰው የላቀ የአመራር ተግባር እንድናከናውንለት ይፈልጋል:: ልንሰጠው የሚገባን ያለንን ትልቁን ችሎታችንን ስለሆነ፣ ከዚያ ያነሰ ነገር ለእግዚአብሔር ስድብ ነው፤ የሰጠንንም ስጦታ የሚያባክን ይሆናል:: ነገር ግን ስጦታችንን



በሚገባ በምንጠቀምበት ጊዜ፣ ምንም እንኳን ከሌላው ሰው ሥራ ያነሰ ሊሆን ቢችልም፣ እግዚአብሔር ይከብራል::

ለ. የአመራርን ክህሎት ይዞ የተወለደ ሰው የለም:: ስለ ክህሎት በምንነጋገርበት ጊዜ አንድ ሰው በተፈጥሮ ወይም በቀላሉ ስለሚያደርገው ነገር መናገራችን አይደለም:: ክህሎት በትምህርትና በልምምድ የምናገኘው ነገር ነው:: ይህ ለዝማሬ የሚመች ጥሩ ድምጽ ወይም በሩጫ የሚቀድሙ ፈጣን እግሮች ይዞ እንደ መወለድ አይደለም:: በተፈጥሮ የታደሉ ብዙ ሰዎች ምርጥ ዘማሪ ዎች ወይም ፈጣን ሯጮች አይደሉም:: የተፈጥሮ ችሎታቸውን ከላቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ ሥልጠና ማግኘት ያስፈልጋቸዋል:: ስለ- ሆነም አንድ ሰው በመሪነት የተፈጥሮ ችሎታ ሊኖረው ቢችልም፣ ክህሎቱ አለው ማለት ግን አይደለም:: የተሻለ መሪ ለመሆን፣ አመራርን የሚያሳድጉ የተወሰኑ ክህሎቶችን መማር አለበት:: በአመራር የተፈጥሮ ችሎታ የሌለውም ሰው ቢሆን በትምህርትና በጠንካራ ሥራ የአመራር ክህሎቶችን ሊያዳብር ይችላል::

ሐ. ማንም ሰው በክህሎት የታገዘ አመራር ለመስጠት ካልቆረጠ በስተቀር የአመራር ክህሎት ሊያዳብር አይችልም:: የአመራር ጥራት የሚመነጨው ነገሮችን ምርጥ አድርጎ (በልቀት) ለመሥራት ከመሻት ነው:: አንድ ሰው ክህሎት የሚኖረው የችሎታውን ያህል ተጠቅሞ ነገሮችን ለማከናወን ሲፈልግ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው አንድን ነገር ጥሩ አድርጎ መሥራት የሚያስችል ክህሎት ለማዳበር በትጋት ይማራል::

የተፈጥሮ ችሎታ አንድ ሰው የመሪነት ክህሎት እንዲቀዳጅ ነገሮችን ያቀልለታል፣ ወይም ከሌላ ሰው በበለጠ ውጤታማ አመራር እንዲሰጥ ያስችለዋል:: ነገር ግን አንድ ሰው የተፈጥሮ የመሪነት ብቃት ባይኖረው እንኳን፣ አመራሩን የሚያሳድጉ ክህሎቶችን ሊማር ይችላል:: ይሁንና፣ አንድ ሰው ክህሎቶችን የሚያዳብረው ነገሮችን በጥራት (በልቀት) ለማከናወን ፍላጎት ካለው ነው:: ለእግዚአብሔር ክብር የችሎታችንን የመጨረሻ ብቃት ተጠቅመን ለመሥራት ካልፈለግን፣ ክህሎትን ለማግኘት

እንጥርም ማለት ነው። ከዚህ ይልቅ፣ ቀለል ያለውን አሠራር ብቻ እንከተላለን፣ ይህ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ላቅ ያለ ክህሎት የሚጠይቅ አይሆንም። ብዙም ሳንዘጋጅ እንሰብካለን። እንዴት አድርገን በጥሩ ሁኔታ እንደምንሠራ ሳናስብ የማስተማር ተግባራችንን እናከናውናለን። የቤተ ክርስቲያንን ወቅታዊ ችግሮችን ብቻ በመቅረፍ ላይ ያተከረና ዘለቄታዊ ዕድገት የማያስገኝ አመራር እንሰጣለን።

አንድ መንፈሳዊ ሰው እግዚአብሔርን መውደዱና የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ማደሩ ብቻ ክህሎት ያለው መሪ አያደርገውም። ጥሩ አድርጎ የመምራት ክህሎት ባለማዳበራቸው ምክንያት የሚቸገሩ መንፈሳዊ መሪዎች መኖራቸውን ሁላችንም እናውቃለን። እግዚአብሔርን በክህሎት ለማገልገል ትፈልጋለህ? ይህ ከባድ ሥራን የሚጠይቅ ነገር ነው። ይሁንና፣ ታላቁ አምላካችን በክህሎት ሊገለገል የሚገባው አምላክ አይደለምን? በክህሎት በማናገለግልበት ጊዜስ የእግዚአብሔርን ክብር ማጉደላችን አይደለምን?

> 7ኛ ጥያቄ:- ሀ) በክህሎት የምትሠራው አንዳች ነገር አለን? ካለ፣ ምንድን ነው? ከሌለስ፣ ለምን? ለ) ብዙውን ጊዜ የምታደርገውን አንድ ነገር ጥቀስ። በክህሎት ማድረግን ብትማር እንዴት ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ግለጽ። ሐ) ክህሎቶችን በማዳበር ሊጎለብቱ የሚችሉ የመሪዎች ተግባራት ምን ምንድን ናቸው?

### 3. አንድ ሰው የመሪነትን ክህሎት ሊያዳብር የሚችለው እንዴት ነው?

በአንድ ነገር ላይ ክህሎትን ማዳበር በድንገት የሚከሰት ነገር አይደለም። አንድ ሰው በድንገት አሪፍ የጊታር ተጫዋች፣ አሪፍ አስተማሪ፣ መስካሪ ወይም አሪፍ መሪ ሊሆን አይችልም። በየትኛውም ተግባር ክህሎትን ለማሳደግ፣ የሚከተሉትን ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው:-

ሀ. ክህሎቱን የማጎልበት ፍላጎት መኖር አለበት። ችሎታችንን በሚገባ አሳድገን እግዚአብሔርን ለማገልገል ካልፈለግን፣ በክህሎት



የበሰጸገ የመሪነት ብቃት ሊኖረን አይችልም። ክህሎት ያለን መሪ መሆን ለኢየሱስ ያለን ፍቅር መገለጫ ነው። እግዚአብሔር ኢየሱስ ለእኛ እንዲሞት በማድረግ ያለውን ምርጥ ነገር ለእኛ ሰጥቷል። እኛም ራሳችንን በክህሎት የምናሳድገው ችሎታችንን አልቀን እርሱንና ሕዝቡን በማገልገል ፍቅራችንን ልንሰጠው ከወሰንን ብቻ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዳለው፣ ከሕይወት ግብግቦች 90 በመቶው ትክክለኛውን አመለካከት በማዳበር ላይ ያተከረ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በቤተ ክርስቲያን አመራር ክህሎትን ማዳበር የሚጀምረው ለጌታችንና ለአዳኛችን ነገሮችን በክህሎት ጥሩ አድርገን ለማከናወን ስንፈልግ ነው። ነገሮችን በክህሎት ከማከናወን ያነሰ ማንኛውም ነገር ከሁሉም የላቀ አገልግሎታችን ለሚገባው አምላካችን እንደ ስድብ የሚቆጠር ነው።

ለ. የአመራር ክህሎቶችን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል። የትኛውንም ክህሎት መማር ጊዜና ጥረት እንደሚጠይቅ ይታወቃል። ለምሳሌ፣ የጊታር ክህሎት ለማዳበር ብንሞክር፣ ጥሩ አድርገው የሚጫወቱ ሰዎች እንዲያስተምሩን እንጠይቃቸዋለን። ከዚያ በኋላ ለሰዓታት ቁጭ ብለን መለማመድ አለብን። እንዲሁም ደግሞ ክህሎቱ ያላቸው ሰዎች ሲጫወቱ በማየት አጨዋወታቸውን እንከርጃለን። የኋላ ኋላ ምንም ሳናስብ እንደ ልባችን ከምንጫወትበት ደረጃ የምንደርሰው ለሰዓታት ከተለማመድን በኋላ ብቻ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናቸውን የአመራር ክህሎቶች መቀዳጀት የሚቻለውም በዚሁ መንገድ ነው። በመጀመሪያ፣ የተወሰኑ የአመራር ክህሎቶችን መማሩ ብዙ ጥረት ይጠይቃል። ክህሎቱን ለማግኘት ሰዓታት ማጥፋት አለብን። ይህ አንድን ነገር በትክክል ለማከናወን መማርን የሚጠይቅ ነው። በርእሰ-ጉዳዩ ላይ መጻሕፍት በማንበብ፣ ሴሚናር በመካፈል፣ ልንማር የምንፈልገውን ነገር ሌሎች ክህሎቱ ያላቸው ሰዎች እንዴት እንደሚያከናውኑት በማጥናት፣ በግል ልምምድ በማድረግና ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሥራት የምንፈልገውን ክህሎት ልንቀዳጅ እንችላለን። አንድን ነገር በምናከናውንበት ጊዜ

ሁሉ፣ እንዴት እንደምናሻሽለው እናስባለን:: የኋላ ኋላም ክህሎቱን እንቀዳጃለን:: የአንድን ነገር ክህሎት ካገኘን በኋላ፣ እንደ ልማድ ይቀልለናል:: አንድን ክህሎት በሚገባ ከተለማመድን በኋላ፣ ሳናስብ ልናከናውነው እንችላለን:: ብዙውን ጊዜ ክህሎታችንን እየተገበርን መሆናችንን ልብ አንልም፣ ሌሎች ግን ልብ ይላሉ::

ሐ. አንድን ክህሎት መማር ማለት የኋላ ኋላ ሳናስብ እስክምናከናውን ድረስ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ መለማመድ ማለት ነው:: ክህሎቱን ልናገኝ የምንችለው የተሻለ ችሎታ እስክናዳብር ድረስ ደጋግመን ባደረግነው መጠን ነው:: የትኛውም ትምህርት ቤት «ክህሎት»ን ሊያስተምረን አይችልም:: ትምህርት ቤት እንዴት መመስከር፣ ማስተማር ወይም፣ መስበክ እንደሚቻል የሚያሳዩትን መርሖዎች ሊያስተምር ይችላል:: ይህ ግን ክህሎትን አይሰጠንም:: በማስተማር፣ በምስክርነት፣ ወይም በስብከት ክህሎታችንን ለማዳበር፣ የተማርነውን ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ አለብን:: በተደጋጋሚ እጥጋቢ ዕቅድ ማውጣት የመሳሰሉትን የአመራር ክህሎቶችን ስናከናውን፣ የኋላ ኋላ ወደ ልማድነት ይቀየራል::

መ. ክህሎትን መማር ማለት አንድን ነገር የምናደርግበትን ሁኔታ በተደጋጋሚ በመገምገም በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን መጣር ማለት ነው:: የአንድን ነገር ክህሎት ለማዳበር አንድ ሰው ሊያደርግ የነበረውን ነገር በመመርመር፣ «እንዴት ላሻሽለው እችላለሁ?» ብሎ መጠየቁ ወሳኝ ነው:: ክህሎት ያላቸው ሰዎች ሁሉ እንዴት ሊያሻሽሉት እንደሚችሉ ለማወቅ ሥራቸውን ይገመግማሉ::

ሠ. ክህሎትን ለማዳበር የዕድሜ ልክ የመማር ሂደትን ይጠይቃል:: እውነተኛ ክህሎት ያለው ሰው መቼም መማርን አያቆምም:: በሚያደርገው ነገር የተሻለ ደረጃ ላይ ለመድረስ የማይጥርበት ጊዜ የለም:: ሁልጊዜም ክህሎቱን የሚያሻሽልበትን መንገድ ይፈልጋል:: የቤተ ክርስቲያን አመራር ክህሎታችንን ለማሻሻል ሁልጊዜም አንድን ነገር ልናሻሽል የምንችልባቸውን መንገዶች ማሰብ አለብን:: «እንዴት የተሻለ ስብከት ላቀርብ እችላለሁ? እንዴት የተሻለ ምስክርነት ማቅረብ እችላለሁ? የቦርድ



ስብሰባውን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልመራ እችላለሁ? እንዴት በተሻለ ሁኔታ ላስተምር እችላለሁ? ቤተ ክርስቲያን የበለጠ መንፈሳዊነትን እንድታሳይ እንዴት በበለጠ ልንረዳት እንችላለን? ሰዎች በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ እንዴት አድርገን በተሻለ መንገድ ልንረዳቸው እንችላለን?» ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ሙዚቀኞች፣ ወንጌላውያንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክህሎታቸውን ለማጎልበትና ችሎታቸውን በበለጠ ለማሳደግ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው:: ሥራውን በመገምገም እንዴት አገልግሎቱን ሊያሻሽል እንደሚችል የማያስብ መሪ ክህሎት ያለው መሪ ሊሆን አይችልም::

ችግሩ፣ የምናከናውናቸውን ነገሮች በክህሎት ለማሳደግ የምንፈልግ ሰዎች ብዙዎች አይደለንም:: በትምህርት ቤት ክህሎትን ለማጎልበት የሚያስችሉንን ነገሮች ከማድረግ ይልቅ ጥሩ ማርክ በማምጣቱ ላይ ትኩረት እናደርጋለን:: ስለሆነም፣ የስብከት ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ብዙ ተማሪዎች ጥሩ ሰባኪዎች ለመሆን ከመሞከር ይልቅ፣ የተወሰኑ ነገሮችን በመሸምደድ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ይጥራሉ:: ጥሩ ውጤት ማምጣት አምብዛም ክህሎትን አያሳይም:: ይህ ጥሩ የሸምደዳ ችሎታ እንዳለንና የፈተና ጥያቄዎችን መመለስ እንደምንችል ከማሳየት ያለፈ መረጃ አይሆንም:: ይሁን እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምናገለግልበት ጊዜ አይረዳንም:: በአግባቡ የአመራር ሥልጣና መውሰድ ካለብን፣ የአገልግሎት ክህሎት በማዳበሩ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን::

8ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተሻለ ሁኔታ ታገለግለው ዘንድ ክህሎትን እንድታዳብር የሚፈልግበትን አንድ አገልግሎት ምረጥ:: ለ) አሁን ያንን አገልግሎት እንዴት እያካሄድክ እንዳለህ ገምግም:: አገልግሎትህ በክህሎት የዳበረ ነው ወይስ አማካይ ብቃት ብቻ የሚታይበት? ሐ) አገልግሎቱን በክህሎት ለማዳበር መለወጥ ያለብህ ነገር ምንድን ነው? በክህሎት ለማደግ ማድረግ አለብኝ የምትላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: በክህሎት እያደግክ መሆንህን ለማወቅ በየወሩ የዘረዘርካቸውን ነገሮች ገምግም::

በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የምናካሂደው የዚህ የሁለተኛው መጽሐፍ ዓላማ ክህሎት ያለው የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን የሚያስችሉትን አንዳንድ እውነቶች መማር ነው። በክህሎት እንደ በለጸገ መሪ በማገልገል እግዚአብሔርን ለማስከበር ካልፈለግክ ግን እነዚህ እውነቶች ሊረዱህ አይችሉም። በአገልግሎትህ ክህሎትን ልታዳብር የምትችለው ተግተህ ስትሠራና የተማርካቸውን ነገሮች ተግባራዊ ስታደርግ፣ ብሎም ክህሎት ሊያመጡ የሚችሉትን ነገሮች ደጋግመህ ስታደርግ ብቻ ነው። አገልግሎትህን የምታሻሽልባቸውን መንገዶች ስትፈልግ ተከታታይ ግምገማዎችን ማድረግ ይጠበቅብሃል።

> ጥናትህን ከመቀጠልህ በፊት፣ መንፈስ ቅዱስ ክህሎት ያለው አገልጋዩ የመሆን ፍላጎት እንዲያድርብህ እንዲያግዝህ ጸልይ። እግዚአብሔር በሰጠህ አገልግሎት የመጨረሻ ብቃትህን ለመጠቀም እሁኑኑ ቃል ግባ።

## ሁለተኛ ቀን

## ነህምያ፣ በክህሎት የበለጸገ አመራር አርአያ

«የአመራር ክህሎት ማዳበር በአገልግሎታችን ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለን? ክህሎት ባይኖረንስ እግዚአብሔር መሥራቱ ይቀራል? ሁላችንም የግል ኃላፊነቶቻችንን ለመወጣትና የቤተ ክርስቲያን ተግባራትን ለማከናወን ደፋ ቀና ስለምንል፣ ሥራ ይበዛብናል። ስለሆነም፣ «በክህሎት ለማገልገል የምንችልበትን ጊዜ ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው» እንላለን። በአመራራችን ክህሎትን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ አለማድረጋችን ለውጥ ያመጣል። አነስተኛና ብስለት የሚጎድላት ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ አገልግሎት ከምትሰጥ በሳል ቤተ ክርስቲያን በምን ትለያለች? ዕድገትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ቢሆንም (1ኛ ቆሮ. 3:6)፣ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ መንግሥቱን ለማሳደግ ሲል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሾማቸውን መሪዎች ክህሎት ይጠቀማል። መሪዎች ክህሎት ካሌ



ላቸው፣ ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው ደካማ ትሆናለች። ነገር ግን መሪዎች የመምራት ክህሎት ሲኖራቸው፣ ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ታድጋለች።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ መንፈሳዊና አካላዊ ለውጦችን ለማምጣት ስለ ተጠቀመባቸው እያሌ ክህሎት ያላቸው መሪዎች ይነግረናል። ለምሳሌ ያህል፣ ሙሴ ከሁለት ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎችን ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ውስጥ መርቷል። እግዚአብሔር ዳዊትን በመጠቀም አነስተኛ ጎሳዎችን በዘመኑ ወደር ወደሌለው ታላቅ ሕዝብነት ለውጦአል። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያትን በሚያስደንቅ ሁኔታ በመጠቀም በአንድ ትውልድ ውስጥ የኢየሱስ ተከታዮች በሮም ግዛት ሁሉ እንዲዳረሱ አድርጓል። ነገር ግን እጅግ አስደናቂ ከሆኑት የአመራር ክህሎት አርአያዎች አንዱ ነህምያ ነው። እግዚአብሔር ነህምያን በመጠቀም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ቅጥር ሠርቷል። በ52 ቀናት ውስጥ ነህምያ ከተማይቱን የሚከልል ቅጥር ለመሥራት ችሏል። ቅጥሩ ከሦስት ኪሎ ሜትር የሚበልጥ ርዝመት ነበረው። ይህን ለማድረግ የቻለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር የአመራር ክህሎቱን ስለ ተጠቀመ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመሪው ነህምያን ክህሎቶች ሙሉ ለሙሉ ልናብራራ አንችልም። ይሁንና፣ ነህምያ ይህንን አስደናቂ ተግባር ለማከናወን የተጠቀመባቸውን የተለያዩ ክህሎቶች ከዚህ በታች እንዘረዝራሰን።

> 9ኛ ጥያቄ:- ነህ. 1-2 አንብብ። ሀ) የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች የመገንባቱ ራእይ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ለመወሰን ነህምያ የተጠቀመባቸውን ነጥቦች ዘርዝር። ለ) ነህምያ ከሕዝቡ ጋር ከመነጋገሩ በፊት ቅጥሮቹን ዞሮ ቅኝት ያካሄደው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ነህምያ የተቀበለው ራእይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣለት መሆኑን ሕዝቡ እንዲቀበል ለማሳመን ምን አደረገ?

1. ነህምያ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ነገሮች ግልጽ ራእይ የማዘጋጀት ክህሎትን ተጠመቀ። በዚህ

መጽሐፍ ውስጥ እንደምንመለከተው፣ አንድ መሪ ሊያደርግ የሚገባው የመጀመሪያው ነገር እግዚአብሔር እንዲያከናውን የሚፈልገውን ሥራ በትክክል መረዳት ነው። ልናደርገው የምንፈልገውን ነገር የመጨረሻ ውጤት አርቆ ማስብን/ ማየትን «ራእይ» እንለዋለን። ብዙውን ጊዜ ታሳቅን ነገር የምናደርገው ለእግዚእብሔር ልናደርግ የምንሞክረውን ሥራ በትክክል ስናውቅ ነው። ነህምያ ሥራውን ለመወሰን ያደረጋቸውን ነገሮች ከዚህ በታች ተመልከት።

ሀ. በኢየሩሳሌም ዙሪያ ቅጥሮች አለመኖራቸው ነህምያን እለሰበው። ስለ ሁኔታው እንደ ሰማ፣ ማልቀስና መጸለይ ጀመ ረ (ነህ. 1፡1-11)። ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትክክል ለሳልሆን ነገር የሚለማን ሸክም እግዚአብሔር አዲስን ነገር ለክብሩ ለማድረግ የመፈለጉ ምልክት ነው።

ለ. ነህምያ ለለ ችግሩ መጸለይ ጀመረ። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በመጠቀም ወደ ተለታፊነት ያሸጋግ ረናል። በመሆኑም፣ እግዚአብሔር ችግሩን ለማስተካከል ይጠቀምብናል። እግዚአብሔር የጸሎታችን መልስ አካል እንድንሆን ይጠይቀናል።

ሐ. ነህምያ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ እንደሚፈልግ በግልጽ ተረዳ። እግዚአብሔር ቅጥሩን በኃላፊነት እንዲያሠራ የሚፈልግ መሆኑን ተገንዝቦ ነበር። እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን እንዲገነባ ወይም ነገሮችን እንዲያሻሽል ወይም የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲረዳ አልጠየቀውም። እግዚአብሔር በትክክል ምን እንዲያደርግ አንደሚፈልግ ያውቅ ነበር። ይኸውም በኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ ቅጥሮችን መሥራት ነበር፣ ነህምያ እግዚአብሔር በሰጠው ራእይ ላይ በፍጥነትና በብቃት እንዲሠራ ያስቻለው እግዚአብሔር ምን አንዲሠራ እንደሚፈልግ ማወቁ ነበር።

መ. ነህምያ ለራእዩ መፈጸም ራሱን ስጠ። ቅጥሮችን የመሥራቱ ራእይ ሊጀመር የሚችለው ነህምያ የመንግሥት



ሥራውን በመልቀቅ በግንባታው ሥራ ላይ ከተሰማራ ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ለነህምያ የሰጠው ራእይ በወረቀት ላይ የሚሰፍር ንድፈ-አሳባዊ ዕቅድ አልነበረም። በተግባር ላይ የማይውል የወረቀት ላይ ራእይ ዋጋ የሌለው ነገር ነው። ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራእዮቻቸውን ወይም ሊያከናውኑ የሚፈልጓቸውን ነገሮች በወረቀት ላይ አስፍረው ግድግዳ ላይ ይሰቅላሉ። እነዚህ ራእዮች ግን የግድግዳ ጌጦች ሆነው የሚቀሩባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ራሱን ለራእዩ አሳልፎ በመስጠት በእግዚአብሔር ርዳታ ከፍጻሜ የሚያደርስ ሰው ብዙ አይደለም። ራእዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነ፣ ምንም ያህል መሥዋዕትነት ቢያስከፍል ሕይወታችንን ለዚሁ ራእይ መስጠት ይኖርብናል። ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ለስጣት ራእይ ራሳቸውን አሳልፈው የማይሰጡ ከሆነ፣ ራእዩ ሊፈጸም አይችልም። ቤተ ክርስቲያንም ባለመታዘዝ ስለምትመላለስ አግዚአብሔር ወደሚፈልጋት የዕድገት ደረጃ ልትደርስ አትችልም። ከአንድ ራእይና ዕቅድ ጋር በምንስማማበት ጊዜ ተግባራዊ አንደምናደርገው ለእግዚአብሔር ቃል መግባታችን ነው። ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ ለመወሰን ከመፈለጋቸው በፊት፣ የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ ራሳቸውን መስጠት አለባቸው። ከዚያም፣ አግዚአብሔር በሚሰጣቸው ጉልበት፣ ሥራውንና ራእዩን ከፍጻሜ ለማድረስ መጣር አሰባቸው። ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ ራሳችንን የማንሰጥ ከሆነ፣ በወረቀት ላይ ባናሰፍረው ይሻላል። ስማድረግ «ተስፋ የምናደርጋቸውን» ነገሮች እየዘረዘርን ተግባራዊ ሳናደርግ በምንቀርበት ጊዜ፣ ዕቅዶቻችንንና ለእግዚአብሔር የገባነውን ቃል ኪዳን ላንፈጽም እንቀራለን። የእግዚአብሔር ሕዝብም ዕቅዳችንን አይተው፣ «መልካም ነው» ቢሉም፣ ምንም ነገር ሳይፈጸም ይቀራል። ኢየሱስ ከአፋችን ለሚወጣ ቃል ሁሉ እንደምንጠየቅ እንደ ተናገረ ሁሉ (ማቴ. 12:36-37)፣ እንተገብራለን ብለን ለወጠንናቸውና ነገር ግን ተግባራዊ ሳላደርግናቸው ነገሮች ሁሉ

የቤተ ክርስቲያንን መሪዎችና ምእመናን ተጠያቂ እንደሚያደርግ መረዳት ይኖርብናል::

እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ካልተገነዘብን፣ ለእርሱ ታላቅ ነገር ልናደርግ አንችልም:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎችና ምእመናን መረዳት ያለባቸው የመጀመሪያው ክህሎት ለእግዚአብሔር ክብር እንድንፈጽም የታዘዝነውን ነገር በትክክል መ ረዳት ነው::

ነህምያ እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዲገነባ የሰጠውን ተግባር ለማከናወን ዕቅዶችን በሚገባ የማዘጋጀትን ክህሎት ተጠቅሟል:: ነህምያ እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዲገነባ መፈለጉን ካረጋገጠ በኋላ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ቅጥሮቹን ለመገንባት ምን ማድረግ እንዳለበት ያቅድ ጀመር:: ይህ ዕቅድ በሁለት ደረጃዎች ነበር የተዘጋጀው:: በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመነሻ ዕቅድ ነደፈ:: ንጉሡ ምን ሊያደርግ እንደሚፈልግ በጠየቀው ጊዜ ነህምያ ዕቅዱን አዘጋጅቶ ነበር:: ስንጉሡ ሥራው ምን ያህል ጊዜ፣ እንደሚፈጅበት፣ ለሥራው ምን ዓይነት ፈቃድ እንደሚያስፈልገው፣ ወዘተ. . . ሊነግረው ችሎ ነበር:: ዕቅድ ለማውጣት ጊዜ አላስፈለገውም ነበር (ነህ. 2:1-10)::

ነህምያ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ ዋናውን ሥራ ከመጀመሩ በፊት ዕቅዱን ይበልጥ አጠራው:: ምንም ዓይነት ሥራ ከመጀመሩ በፊት በኢየሩሳሌም ቅጥሮች ዙሪያ በመዟዟር ቅኝት ያካሂድና ራእዩን ለመፈጸም ምን እንደሚያስፈልግ ያጠና ጀመር (ነህ. 2:11-15):: ሁልጊዜም አንድ ዕቅድ እየጎለበተ ሲሄድ ነገሮች እየጠሩ መሄድ አለባቸው:: ነህምያ ስለ ፈራረሱት ቅጥሮች ቢሰማም፣ አላያቸውም ነበር:: በቅጥሮቹ ዙሪያ በሚዟዟርበት ጊዜ ሥራውን ለማከናወን ስለሚያስችሉ መንገዶች የሚያስብ መሆኑ አያጠራጥርም:: ራእዩን ወደ ተግባር ለመለወጥ በዚህ መንገድ ነበር ዕቅዱን ያጠራው::



ሁኔታዎች ሲለወጡ፣ ነህምያ ዕቅዶቹን ከሁኔታዎች ጋር ማዛመዱን ቀጠለ:: ለምሳሌ ያህል፣ ሰዎች በቅጥር ግንባታው ላይ የሚሠሩትን ግንበኞች ለማጥቃት በዛቱ ጊዜ ነህምያ አሠራሩን መቀየር ነበረበት:: በዚህ ጊዜ ሰይፋቸውን ታጥቀው ሥራቸውን ለማከናወን ተገደዱ:: ዘበኞችንም መመደብ ያስፈልገው ነበር (ነህ. 4):: ነገር ግን ምንም እንኳን ዕቅዶቹ ቢለወጡም፣ ነህምያ በፍጹም ራእዩን አልቀየረውም:: ምንም ነገር ቢመጣም የቅጥሩ ግንባታ እንዲቀጥል ወሰኗል::

አንድ እሳብ ወይም ራእይ ወደ ተግባር ሊለወጥ የሚችለው በሚገባ በታሰበባቸው ዕቅዶች አማካኝነት ነው:: ልናደርግ የምንፈልገው ነገር ራእይ ብቻ ኖሮን ዳሩ ግን ግልጽ ዕቅዶች ከሌ ሉን፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ተግባር በብቃት ለመወጣት እንቸገራለን:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ እንድትፈጽም የሚፈልገው ራእይ ትንሽ ወይም ቀስ በቀስ ይለወጣል:: ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የምትመራ ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን በተሻለ ሁኔታ እውን ለማድረግ ዕቅዶቿን ከሁኔታዎች ጋር ታዛምዳለች::

ነህምያ ሌሎች የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ በማድረጉ በኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ የመግባባትን ክህሎት ተጠቅሟል:: ነህምያ እግዚአብሔር የሚከብርበትና ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው የሚጠበቁበት ቅጥር ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት አብራራላቸው:: ከዚያም በአሁኑ ሰዓት ከተማቸው ያለ ቅጥር መሆኗን ገለጸላቸው:: በመቀጠልም ሕዝቡ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ቅጥሮችን እንዲሠሩ አደፋፈራቸው (ነህ. 2:17-18)::

ሰዎች ተግባራዊ ለማድረግ ካልተነሣሡ፣ ራእይ ዋጋ የለውም:: ነህምያ ብቻውን ቅጥሮቹን ሊሠራ አይችልም ነበር:: ሌሎች ከእርሱ ጋር በፈቃደኝነት መሥራት ያስፈልጋቸው ነበር:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲከናወን የሚያፈልጋቸውን ሥራዎች ማንኛውም መጋቢ ወይም የሽማግሌ ዎች ቡድን ብቻውን አይሠራም:: የቤተ ክርስቲያን አባላት በአንድነት የእግዚአብሔርን ራእይ ማከናወን አለባቸው::

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ራእይ ተግባራዊ የምናደርግበት ብቸኛው መንገድ ይኸው ነው:: የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በኅብረት የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል ጥሩ የመግባባት (የተግባቦት) ክህሎትን ይጠይቃል:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድታከናውን የሚፈልገውን ራእይ ለሕዝቡ ለማስተላለፍ፣ መሪዎች ራእዩን በግልጽ ማብራራት አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ያ ራእይ እንዴት እንደሚጎድላትም ማሳየት ያስፈልጋል:: ሕዝቡ እንዲሳተፉና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽሙ ማነሣሣት አለብን:: እግዚአብሔር በሚፈልገውና አሁን ባለው ሁኔታ መካከል ያለውን ልዩነት በመመልከት፣ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለመሰወጥ ይወስናሉ:: ነገር ግን መሪዎች ሕዝበ በችግሮቹ ሳይ እንዲያተኩር ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለሰጣቸው ራእይ ከታዘዙ ችግሮቹን ለማስወገድ በሚያስችል የእግዚአብሔር ኃይል ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፣ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን» (ነህ. 2:20)::

ነህምያ ጫና ሳያሳድርባቸው ሕዝቡ ሥራውን ለማከናወን ተነሡ:: ነህምያ መሪያቸው ነበር:: ምንም እንኳን ሰዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ ሊያዝ ቢችልም፣ የመንግሥት ሥልጣኑን ተጠቅሞ ሕዝቡን ለማሠራት አልፈለገም:: አንዳንድ ሰዎች በግንባታው ሥራ ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አለማድረጋቸው ተገልጾአል:: ነህምያ አስገድዶ ለማሠራት መሞከሩን የሚያሳይ መረጃ አልተመለከተም (ነህ. 3:5):: ይልቁንም፣ ነህምያ አብዛኛው ሕዝብ በቅጥር ግንባታው ሥራ ላይ እንዲሰማራ ለማድረግ ችሎ ነበር:: የነህምያን ራእይ እንደ ራሳቸው ራእይ ተቀብለው ለተግባራዊነቱ ተግተው ይሠሩ ጀመር::

መሪዎች ሰዎችን ተጭነው በሚያሠሩበት ጊዜ፣ ሰዎች ክልባቸው ለመሥራት ይቸገራሉ:: ስለሆነም ተቆጣጣሪ በማይኖርበት ጊዜ ሥራውን ያስተጓጉሉታል:: ለእግዚአብሔር የሚሠራ ሰው ብዙ ቁጥጥር አያስፈልገውም:: ነህምያ ገንዘብ



በመስጠትም ሰዎችን ለሥራ ለማነሣሣት አልፈለገም:: ለገንዘብ ብለው የሚሠሩ ሰዎች አንድን ተግባር የሚያከናውኑት የተሻለ ገቢ የሚያገኙበትን መንገድ እስኪያገኙ ድረስ ብቻ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ሥራ በጥሩ ሁኔታ የሚካሄደው ሕዝቡ ራእዩን በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚፈልጉ እንደ ሆነ ነው:: እንደ ነህምያ፣ መሪዎች ሰዎች ራሳቸውንና ያላቸውን ሀብት ለእግዚአብሔር ሥራ ይሰጡ ዘንድ በሚያነሣሣቸው መንገድ ራእዩን ሊያቀርቡላቸው ይገባል::

ሰዎች የእግዚአብሔርን ራእይ ሰመፈጸም እንዲተባበሩ የሚያደርገው ይህ የተግባቦት ክህሎት ነው:: ለእግዚአብሔር ሥራ ራሳቸውን እንዲሰጡና እስከ ሥራው ማብቂያ ድረስ እንዲተጉ የሚያደርገው ይኸው መልካም ተግባቦት ነው::

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- ነህ. 3 አንብብ:: ሀ) በቅጥሩ ላይ እንዲሠሩ ኃላፊነት የተሰጣቸውን የተለያዩ ሰዎች ዘርዝር:: ለ) እያንዳንዳቸው የገነቡት የቅጥሩ ክፍል ምን ያህል ነበር? ሐ) ሁሉም በጅምላ እንዲሠሩ ከማድረግ ይልቅ፣ ነህምያ ሰዎች በክፍል ክፍል እንዲሠሩ ማድረጉ ምን ጥቅም ያለው ይመስልሃል? |

4. ነህምያ ሰዎች በቡድን ቡድን በተለያዩ የቅጥሩ ክፍሎች ላይ እንዲሠሩ ለማድረግ <u>የውክልና</u> እና <u>የቡድን ሥራ</u> ዘዴዎችን ተጠቅሟል:: ነህምያ ሕዝቡን በፍጥነት በማደራጀት እያንዳንዱ ቡድን የሚሠራበትን ስፍራ ነገራቸው:: ሰዎቹ የተነጋገሩት እግዚአብሔር ስለሚፈልጋቸው ነገሮች ወይም ስለ ገጠማቸው ችግር ብቻ አልነበረም:: ራእዩ እውን እንዲሆንም ጭምር ይነጋገሩና ይሠሩ ጀመር:: ነህምያ በሚገባ የተዘጋጀ ዕቅድ ስለ ነበረው፣ ሥራው በፍጥነት ተጀመረ:: ከፍተኛ ተቃውሞ ቢገጥማቸው እንኳን፣ ራእዩ በ52 ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ ቻለ (ነህ. 6:15-6)::

ጥቂት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች ሁሉ የሚያከናውኑት በውክልና ክህሎት እማካኝነት ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ብቻ ሥራውን ለማከናወን

የሚፈልጉ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር ክብር የሚከናወነው ሥራ ብዙ አይሆንም:: ነገር ግን ሕዝቡ በጥንቃቄ ተደራጅተው ለእግዚአብሔር በአንድነት እንዲሠሩ በሚደረግበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ አማካኝነት አስደናቂ ነገሮችን ይሠራል:: አብዛኞቹ አባላት በንቃት እግዚአብሔርን የማያገለግሉ ከሆነ፣ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን በሙሉ አቅሟ እየሠራች አይደለችም::

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ:- ነህ. 5 አንብብ:: ሀ) ነህምያ የተጋፈጣቸውን ፈተናዎች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ ፈተናዎች የራእዩን ፍጻሜ እንዴት ሊገቱ ይችሉ እንደ ነበረ ግለጽ:: ሐ) ሥራውን ለመቀጠል ነህምያ ፈተናዎቹን እንዴት እንደ ተወጣቸው አብራራ:: |

5. ነህምያ ሕዝቡ በቅጥር ግንባታው ላይ ትኩረት ያደርግ ዘንድ በመካከላቸው የሚነሡትን ግጭቶች በፍጥነት ይቀርፍ ነበር (ነህ. 5):: ሰይጣን ሁልጊዜም እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ሥራ ለማደናቀፍ ይፈልጋል:: ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ቡድኖች ወይም ሰዎች መካከል በሚከሰቱ አለመግባባቶች ነው:: እነዚህ አለመስማማቶች እስካሉ ድረስ፣ ሰዎች ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ሥራ ሊሰጡ አይችሉም:: አስተዋይ መሪዎች ሥራው እንዲቀጥል ለማድረግ የግንኙነት ችግሮችንና ሌሎችንም ችግሮች በፍጥነት ይቀርፋሉ:: ሥራው በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት በሚቋረጥበት ጊዜ፣ እንደገና ለመጀመር ችግር ይፈጥራል::

እግዚአብሔር የሕዝቡን መንፈሳዊና አካላዊ ቅጥሮች ለመገንባት ከተጠቀመባቸው የነህምያ ክህሎቶች ጥቂቶቹ እነዚህ ነበሩ:: እግዚአብሔር ለእኛና ለቤተ ክርስቲያናችንም ትልቅ ዕቅድ አለው:: እግዚአብሔር ለክብሩ ታላላቅ አገልግሎቶችን እንድናካሂድ የሚያደርገው ከላይ የተጠቀሱትን በመሳሰሉት ክህሎቶች አማካኝነት ነው:: እነዚህን ነገሮች ለመማር ፈቃደኞች ነን? ክህሎት ያለን መሪዎችና አገልጋዮች ለመሆን ፈቃደኞች ነን?

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ለአንተ ወይም ለቤተ ክርስቲያናችሁ የሚፈልገውን ራእይ ምረጥ:: ለ) የነህምያን ታሪክ በመጠቀም ራእይን እግዚአብሔርን ወደሚያስከብር ተግባር እንዴት ልንለውጥ እንደምንችል ግለጽ:: |



በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናቸው ብዙዎቹ ክህሎቶች ለመረዳት የሚያስቸግሩህ ሊሆኑ ይችላሉ:: አብዛኞቹ አሳቦች የማታውቃቸው ይሆናሉ:: ብዙውን ጊዜ ሥልጠና የሚሰጠን በዚህ መንገድ እንድናስብ አይደለም:: ብዙውን ጊዜ የምናውቀው ከፊታችን ያለውን ነገር ማድረግ ነው፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ራእይና ራእዩን እንዴት እንደምንፈጽም እምብዛም አናስብም:: ለቤተ ክርስቲያን ራእይ ያለው አመራር ከመስጠት ይልቅ፣ ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ይቀልለናል:: እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በሚገባ ለመረዳት በጥንቃቄ ማንበብ ይኖርብሃል:: ከዚያም እነዚህን ክህሎቶች ለመማር ከፈለግክ፣ የተጠቀሱትን አሳቦች መለማመድ ይኖርብሃል:: ተስፋ አትቁረጥ:: መሞከርህን ስትቀጥል፣ በመጨረሻው ላይ እየቀለለ ይመጣል:: እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያናችሁና በማኅበረሰብህ ውስጥ ታላቅ ለውጥ ለማምጣት ይጠቀምብሃል::

መጀመሪያ የምናጠናቸው ሦስት ክህሎቶች እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈልገውን ዓይነት ለውጥ ለመምጣት እንዲችሉ የሚያግዙት ናቸው::

1) ክህሎት አንድ:- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚፈልገውን ግልጽ ራእይ በመስጠት መምራት:: ይህ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ራእይ ሊኖራት እንደሚገባ የመወሰን ክህሎት ነው:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥና አማካኝነት ለክብሩ ሊያደርግ የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው? (ትምህርት ስምንት እና ዘጠኝ)

2) ክህሎት ሁለት:- እግዚአብሔር እንድንፈጽም የሚፈልገውን ራእይ ተግባራዊ እንድናደርግ የሚያግዙንን ጥራት ያላቸው ዕቅዶች ማውጣት:: መንገድ ሰዎችን ከስፍራ ወደ ስፍራ እንደሚያጓጉዝ ሁሉ፣ መልካም ዕቅድም ቤተ ክርስቲያን ካለችበት

ስፍራ ተነሥታ እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ቦታ እንድትደርስ ያግዛታል:: (ትምህርት አሥር)

3) ክህሎት ሦስት - የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች ዕ ቅዶቹን ተግባራዊ ለሚያደርጉ ወገኖች በውክልና መስጠት:: (ትምህርት አሥራ አንድ)

## ክህሎት አንድ:- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚፈልገውን ግልጽ ራእይ በመስጠት መምራት

የቤተ ክርስቲያን መሪ መማር ያለበት የመጀመሪያው ክህሎት አግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ራእይ መረዳት ነው:: ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ግንባታ ሥራ የጀመረው የእግዚአብሔር ስም ይከብር ዘንድ የክተማይቱን ቅጥሮች መልሶ ለመገንባት ካለው ትልቅ ሸክም አንጂ፣ ሊያከናውን ክፈለጋቸው ዝርዝር ጉዳዮች አልነበረም:: ይህ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች መልሶ የመገንባቱ ተግባር አግዚአብሔር ለነህምያ የሰጠው «ራእይ» ነበር፡፡ ይኸውም ነህምያ ሥራውን ወደፊት ለመግፋት ከሚችልበት ግልጽ ግብ ጋር ነበር የተሰጠው:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ማኅበረ ምእመናን ለክብሩ ምን ሊሆንና ሊያደርግ እንደሚገባ የሚያመለክት ራእይ አለው:: እግዚአብሔር ምን ሊያደርጉ እንደሚገባ ማወቅ ክቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ዋና ዋና ተግባራት አንዱ ነው:: ለዚህ ነው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው የእግዚአብሔርን ራእይ የመወሰንን ክህሎት መማር ያለባቸው::

## <ራእይ ባለው መሪ> እና <አስተዳዳሪ> መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ:- ሀ) <መሪ> የሚለውን ቃል ግለጽ:: ለ) <አስተዳዳሪ> የሚለውን ቃል ግለጽ:: ሐ) በእነዚህ ሁለት ቃላት መካከል ያለው የትኩረት አቅጣጫ ልዩነት ምንድን ነው? መ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለቱም ዓይነት መሪዎች ለምን እንደሚያስፈልጉ ግለጽ:: |



ብዙ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን በመምራቱ በኩል የሚገባቸውን ያህል ውጤታማ ከማይሆኑባቸው ምክንያቶች አንዱ በሁለት የተለያዩ ስጦታዎችና የአመራር ትኩረቶች መካከል ያለውን ልዩነት ባለመረዳታቸው ነው፣ እነዚህም የመምራትና የማስተዳደር ስጦታዎች ናቸው:: ብዙውን ጊዜ እነዚህን ሁለት ቃላት እየለዋወጥን እንጠቀምባቸዋለን:: በመሆኑም የቤተ ክርስቲያንን መሪ አስተዳዳሪም መሪም እያልን እንጠራዋለን:: በተወሰኑ ሰዎች ላይ ሥልጣን ያለውን ሰው መሪ ወይም አስተዳዳሪ ብለን እንጠራዋለን::

ነገር ግን የእነዚህን ሁለት ቃላት መሠረታዊ ትርጉሞች በምንመለከትበት ጊዜ፣ ሁለቱ የተለያዩ ሰዎች መሆናቸውን እንረዳለን:: መምራት የሚለው ቃል መሠረታዊ ፍች ሰዎች የሚከተሉትንና እነርሱን ይዞ ወደ አንድ ስፍራ የሚወስዳቸውን ሰው ያሳያል:: ኢየሱስ እንደ መልካም መሪ ሕዝቡን ይመራል:: ያለ እርሱ መሪነት ሊሄዱ ወደማይችሉበት ስፍራ ሕዝቡን በመምራት ከፊታቸው ይሄዳል:: ስለሆነም፡- መሪ ሰዎች የሚከተሉት ሰው ነው ማለት ነው:: እንዲሁም መሪ ሰዎችን ወደ አንድ ቦታ የሚወስድ ሰው ነው:: በሌላ በኩል፣ አስተዳዳሪ ሰዎችን የሚያደራጅና ወይም ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወኑ የሚያደርገውን ሰው ያሳያል:: ሁለቱም የአመራር ስፍራዎች ናቸው:: ነገር ግን የመሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች የአስተዳዳሪነት ስጦታ ካላቸው የተለየ የአገልግሎት ትኩረት አላቸው::

ሁለቱ ክህሎቶች ብዙውን ጊዜ ከሁለት የተለያዩ ባሕርያት የሚመነጩ ናቸው:: በተፈጥሮ መሪዎች የሆኑ አንዳንድ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሌሎች ልጆች አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ በመምራት ያድጋሉ:: በተፈጥሯቸው የአስተዳዳሪነት ችሎታ ያላቸው ሰዎችም እንዲሁ አሉ:: እነዚህ ሰዎች ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ይከናወኑ ዘንድ ማደራጀት ያስደስታቸዋል:: ምንም እንኳን አንድ ሰው ጥሩ መሪ ወይም አስተዳዳሪ እንዲሆን የሚያደርጉ የተለያዩ ባሕርያት ቢኖሩም፣ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን

መሪዎችና አስተዳዳሪዎች በተሻለ ሁኔታ እንዲመሩና እንዲያስተዳደሩ የሚያግዟቸውን ክህሎቶች ሊማሩ ይችላሉ።

ሁለቱም ዓይነት መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊዎች ናቸው። ራእይ ያለው መሪና የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው ሰዎች አብረው የማይሠሩበት የሽማግሌዎች ቦርድ ምሉዕ አይደለም። እያንዳንዱ ስጦታ ለሌላኛው ስጦታ ሚዛናዊነትን ይሰጠዋል፣ እንዲሁም ያቀናጥፈዋል። ይሁን እንጂ፣ ራእይ ያለው መሪ ወይም ራእይ ያላቸው ሽማግሌዎች የሚገኙበት ቦርድ ሊያጎለብት የሚገባው የመጀመሪያው ክህሎት ራእይን ከእግዚአብሔር መቀበልና ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን የሚፈልጉትን ነገር ማወቅ ነው። ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት በማደግ ለእግዚእብሔር ክብርን፣ እንዲሁም ለማኅበረሰቡ ለውጦችን የሚያመጡ አብያተ ክርስቲያናት እንዲኖሩን ከተፈለገ፣ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ወዴት ሊያሳድግ እንደሚፈልግ የመረዳት ስጦታ ያላቸውና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደዚሁ ግብ የመምራት ብቃት ያላቸው መሪዎች ሊኖሯቸው ይገባል።

ይህን አሳብ ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ወደፊት ስለሚወስድ ሰው በምናጠናበት ጊዜ ግለሰቡን «ራእይ ያለው መሪ» ወይም የመሪነት ስጦታ ያለው ብለን እንጠራዋለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቶች ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲካሄዱ የማድረግ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች «አስተዳዳሪዎች» ወይም የማስተዳደር ስጦታ ያላቸው ብለን እንጠራቸዋለን። ከዚህ በታች ራእይ ያለውን መሪ ከአስተዳዳሪ ጋር ስናነጻጽር፣ «መሪ ጥሩ ነው፣ አስተዳዳሪ ደግሞ አላስፈላጊ ነው» የሚል መልእክት ለማስተላለፍ እየሞከርን አለመሆናችን ግልጽ ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር ለሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጣል፣ ጤናማና የምታድግ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር፣ ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው። ነገር ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቦርዶች ላይ በትክክል



መጠቀም እንድንችል የእነዚህን ሁለት ስጦታዎች ልዩነቶች አሳምረን ልናውቅ ይገባል። ራእይ ያለው መሪ ወይም አስተዳዳሪ የሚሆኑት ግለሰቦች ብቻ አይደሉም፣ የሽማግሌዎች ጉባኤዎችም ራሳቸው ወደ አስተዳዳሪነት ወይም ራእይ ወዳለው መሪነት ሊያደሉ ይችላሉ። ከዚህ በታች የአመራርና የአስተዳደር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ልዩነት እናሳያለን። እነዚሁ እውነቶች አንድ የሽማግሌዎች ጉባኤ ወደ መሪነት ወይስ ወደ አስተዳዳሪነት እንደሚያደላ እንድናውቅ ያስችሉናል።

1. ባለ ራእይ መሪ ከአስተዳዳሪ የሚለይባቸው መንገዶች:-

ሀ. ባለ ራእይ መሪዎች ሕዝቡን ወደ ለውጥና ዕድገት ያንቀሳቅሳሉ። አስተዳዳሪዎች ያሉትን አገልግሎቶች በብቃት ያከናውናሉ።

ባለ ራእይ መሪ ሁልጊዜም ሕዝቡ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ወደ ሰጣት ግብ እንዲጓዙ ያደርጋል። አንድ መሪ ሕዝቡን በመረዳትና በተግባር ወደፊት የማያንቀሳቅስ ከሆነ፣ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥና ዕድገት ከሌለ፣ ባለ ራእይ መሪ ሊባል አይችልም። የመሪነት ስጦታ ያለው ሰው ሁልጊዜም፣ «እግዚአብሔር የበለጠ ክብር እንዲያገኝ በቤተ ክርስቲያናችን ምን እንድናደርግ ይፈልጋል? ሰዎች የበለጠ መንፈሳዊ ብስለት ይታይባቸው ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችንን እንዴት ልናደራጅ እንችላለን? በማኅበረሰባችን ውስጥ ወንጌሉ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ከማንሣት አይቦዝንም። ባለ ራእይ መሪ ሁልጊዜም ነገሮች በይበልጥ የእግዚአብሔርን ክብር ሊያመጡ የሚችሉበትን መንገድ ይፈልጋል። ነገሮች የማይለወጡና የማያድጉ ከሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ይህ ችግር መኖሩን እንደሚያሳይ ስለሚያውቅ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት እንዳይስተጓጎል ይፈልጋል። አንድ ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ውድቀት የሚዳረገው ዕድገትን በማቆም ባለው ነገር መርካት ሲጀምር ነው። (ራእይ 3:15-18ን ተመልከት።)

በሌላ በኩል፣ አስተዳዳሪ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ በመርዳቱ በኩል ውጤታማ ስለ መሆኗ ወይም ስላለመሆኗ፣ ወይም ደግሞ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማኅበረሰቡን በወንጌል መድረስ እንደሚቻል በማሰብ አይጨነቅም። ከዚህ ይልቅ፣ ያሉት አገልግሎቶች እንዴት በተሻለ ሁኔታ ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ያስባል። የሚያነሣውም፣ «የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች ተግባራቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ምን ዓይነት መመሪያዎችን ብናዘጋጅ ይሻላል? ፋይሎቻችንን እንዴት ጥሩ አድርገን ልናዘጋጅ እንችላለን? ብዙ ሰዎች ለመምጣት እንዲችሉ የቤተ ክርስቲያናችንን ሕንጻ እንዴት እናስፋፋ?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ነው። አስተዳዳሪ-መሳይ-መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ውጤታማ እንድትሆን የሚያግዙትን አዳዲስ ነገሮች ከመፈለግ ይልቅ፣ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አገልግሎቶች በጥሩ ሁኔታ ስለሚቀጥሉበት መንገድ ያስባሉ። እንዲህ ዓይነት መሪዎች ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመገንባት፣ ውብ የመዘምራን ልብሶች ለመግዛት፣ ጥሩ ኪቦርድ እና የድምጽ ማጉያዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖሩበት ሁኔታ ያስባሉ። መዘምራን ጥሩ አድርገው እንዲዘምሩ፣ ስብሰባው በጊዜው እንዲካሄድ፣ የቤተ ክርስቲያን ገቢ አምሮ እንዲታይ ይጨነቃሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓት በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወን ይፈልጋሉ። የወንጌላውያንና የመጋቢያን የሪፖርት አቀራረብ ትክክል እንዲሆን ይሻሉ።

በመሠረቱ፣ ይህ ለጤናማ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው። አስተዳዳሪ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ የማይከናወኑ ከሆነ፣ ብዙ ገንዘብና ጥረት ይባክናል። ሕንጻ ዎችና የቤተ ክርስቲያን ገቢ በጥሩ ሁኔታ ካልተያዙ፣ የሕዝቡን አምልኮና አገልግሎት እንደሚያደናቅፉ ግልጽ ነው። አስተዳዳሪ-መሳይ-መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን መረጋጋትን ይፈጥራሉ። የእነዚህ መሪዎች ዋንኛ ጥያቄ፣ «ነገሮችን ጥሩ አድርገን



ልናከናውን የምንችለው እንዴት ነው?» የሚል ነው። የእነርሱ ጭንቀት በሥራቸው ቀልጣፋ መሆን ነው። በሌላ በኩል፣ ባለ ራእይ መሪ የሚያነሣው ዋንኛ ጥያቄ፣ «ልናደርጋቸው የሚገቡን ትክክለኛ ነገሮች ምንድን ናቸው?» የሚል ነው።

ለ. ባለ ራእይ መሪዎች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምን እንድትሆን እንደሚፈልግ በመረዳቱ ላይ ሲያተኩሩ፣ አስተዳዳሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮችን በመቅረፉ ላይ ያተኩራሉ።

የመሪነት ስጦታ ያለው ሰው ጉልበቱንና ጊዜውን የሚያጠፋው ቤተ ክርስቲያን የምትጋፈጣቸውን ችግሮች ለማስተካከል በመጣር አይደለም። ከዚህ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ እንዴት እንዲለወጥና እንዲያድግ እንደሚፈልግ ለመረዳት ይጥራል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱን ቢባርክ ምን ሊከሰት እንደሚችል ያስባል። ባለ ራእይ መሪዎች ችግሮች ወይም ነገሮች በፍጥነት እስከመለወጣቸው ተስፋ እንዲያስቆርጧቸው አይፈልጉም። በችግሮች ላይ ለማተኮር አይፈልጉም። ነገር ግን እግዚአብሔር የትኛውንም ችግር በማሸነፍ ስሙን የሚያስከብር ለውጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚፈጥር ያምናሉ። እግዚአብሔር ሊያደርግ በሚችለው ነገር ላይ ልበ ሙሉነትና ብሩኅ ተስፋ አላቸው።

በሌላ በኩል፣ የአስተዳዳሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያን አሁን ባለችበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ጊዜ ያቸውንና ጉልበታቸውን የሚያጠፉት ለቤተ ክርስቲያን ችግሮች መፍትሔዎችን በማፈላለግ ነው። ችግሮችን መፍታቱ አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን ሁልጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች መራቸው አይቀርም። ይህም አስተዳዳሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ለውጦችን ለማምጣትና ክርስቶስ ወደሚፈልጋት ደረጃ እንድትደርስ ለማገዝ በቂ ጊዜ እንዳይራቸው ያደርጋል።

ሐ. ባለ ራእይ መሪዎች ትኩረታቸውን የሚያሳርፉት በወደፊት ላይ ሲሆን፣ አስተዳዳሪዎች ግን በአሁን ላይ ያተኩራሉ።

የአስተዳዳሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች አሁን ያለውን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ስመለወጥና አገልግሎቶች በተቻለ መጠን በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄዱ ለማድረግ ይፈልጋሉ። የመሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ግን ወደፊትን አሻግረው ያያሉ። እንደ ይሳኮር ሰዎች ዘመናቸውንና ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገር ያውቃሉ። (1ኛ ዜና 12:32ን አንብብ።) ባለ ራእይ መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ልታድግ፣ ልትለወጥና በበለጠ ውጤታማ ልትሆን የምትችልባቸውን መንገዶች መፈለጋቸውን ይቀጥላሉ። ሁልጊዜም ሁኔታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለወጣቸውን እንደሚቀጥሉ ይረዳሉ። የወጣቶች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ሲያዩ፣ በአዋቂዎች ላይ ከማተኮር ይልቅ ትኩረታቸውን በወጣቶች ላይ ያደርጋሉ። ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያናቸው የምትገኘው በከተማ ውስጥ ከሆነ፣ የከተማውን ሕዝብ ፍላጎቶች ለማሟላት ይጥራሉ። ይህም ከገጠር ቤተ ክርስቲያን አሠራር የተለየ ነው። እነዚህ ባለ ራእይ መሪዎች ወጣቶች በወንጌላዊነት ለማገልገል እለመፈለጋቸውን በሚረዱበት ጊዜ፣ እንዴት አድርገው ወጣቶችን ወደዚህ አገልግሎት እንደሚያስገቡ ያስባሉ። ባለ ራእይ መሪዎች ሁልጊዜም የበለጠ ፍሬያማ ለመሆን የሚችሉባቸውን መንገዶች ይፈልጋሉ።

መ. ባለ ራእይ መሪዎች እግዚአብሔር ምን ለማድረግ እንደሚፈልግ ለመረዳት ትላልቅ ጉዳዮችን ይመለከታሉ። አስተዳዳሪዎች በአገልግሎት ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

ባለ ራእይ መሪዎች፣ «ሰዎች የተሻሉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው? ወንጌልን ሰምተው የማያውቁትን የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች በወንጌል ልንደርስ የምንችለው እንዴት ነው? ምእመናቻችን ሁሉ እንዲጠነክሩ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ልናስተምራቸው እንችላለን?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያነሣሉ። የማስተዳደር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ግን፣ «የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እንዳይሰረቅ ምን ዓይነት የቁጥጥር ሥርዓት ብንዘረጋ ይሻላል? ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የሚያስችል መምሪያ እንዴት ልናዘጋጅ እንችላለን?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያነሣሉ። ባለ ራእይ መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ሊያደርግ የሚፈልጋቸውን ዓበይት ነገሮች ይመለከታሉ። በአስተዳደር ላይ የሚያተኩሩ መሪዎች ግን ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ እንድትሠራ በሚያስችሉ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።



ሠ. ባለ ራእይ መሪዎች በሰዎች የወደፊት ዕድገት ላይ ሲያተኩሩ፣ አስተዳዳሪዎች ሰዎች አሁን ባሉበት ሁኔታ ከእነርሱ ጋር በመሥራቱ ላይ ያደላሉ።

የመሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ የሚፈልግ መሆኑን ይረዳሉ። ስለሆነም አሁን በሕዝቡ ላይ በሚታዩ ድክመቶች ላይ አያተኩሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ በሚሠራበት ጊዜ ሰዎች ወደፊት ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስባሉ። ጥቅም ላይ ያልዋሉ ስጦታዎችን ያዩና እግዚአብሔር እነዛን ስጦታዎች ለራሱ ክብር እንዴት ሊጠቀምባቸው እንደሚችል ያያሉ። (ለምሳሌ ያህል፣ ኢየሱስ ጴጥሮስን የተመለከተው እንደ ዓሣ አጥማጅ ሳይሆን፣ ሰዎችን እንደሚያጠምድና አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ታላቅ ንቅናቄ ታላቅ መሪ እንደሚሆን ነበር። ማቴ. 16:17-19።) እግዚአብሔር የሚፈልገው ከሚሠሩት ሥራ በላይ የሰዎችን መንፈሳዊ ዕድገት መሆኑን ይገነዘባሉ።

አስተዳዳሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮችን በጥሩ ሁኔታ በማከናወን ላይ ትኩረት ስለሚያደርጉ፣ አሁን ባለው የሰዎች ችሎታ ላይ ወደ ማተኮሩ ያዘነብላሉ። በአሁኑ ጊዜ አንድን ተግባር ለማከናወን ከፍተኛ ብቃት ያለውን ሰው ይፈልጋሉ። ችግሮችን በመፍታትና አገልግሎቶችን በመቆጣጠር ደፋ ቀና ስለሚሉ፣ አባላት እንዲያድጉ ለማገዝ የሚያስችል ጊዜ የላቸውም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የድርጅቱ ትልቁ ሀብት መሆናቸው ይረሳና ሥራውን ለማከናወን የሚያግዙ መሣሪያዎች ብቻ ተደርገው ይቆጠራሉ። የአስተዳዳሪዎች አንዱ አደጋ ሰዎችን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ መርሳታቸው ነው።

ሯ. ባለ ራእይ መሪዎች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድትለወጥ የሚፈልግ መሆኑን ባሙኑ ጊዜ አደጋን በመጋፈጥ ነገሮችን ለመለወጥ ይፈቅዳሉ:: አስተዳዳሪዎች ግን ብዙውን ጊዜ አደጋን በመጋፈጥ ነገሮች አሁን ያሉበትን ሁኔታ ለመለወጥ አይፈልጉም::

የመሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሌሎች የማያደርጓቸውን ነገሮች ለማድረግ አደጋዎችን ለመጋፈጥ ፈቃደኞች ናቸው:: ለውጥ ካልተደረገ ከፍተኛ ዕድገት ሊመጣ እንደማይችል ይገነዘባሉ:: አደጋን ሳይጋፈጡ የሚመጣ ለውጥ እንደሌለም ያውቁታል:: ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዕድገታቸው እንዲቀጥሉ የሚያስፈልጉትን ለውጦች እንዲያደርግ እግዚአብሔር እንደሚመራው ያምናል:: የማስተዳደር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ዘና የሚሉት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ሳይደረግ ሲቀር ነው:: ዓበይት ለውጦችን ከማካሄድ ይልቅ አሁን ያሉት አገልግሎቶች በተ ሻለ ሁኔታ እንዲካሄዱ ለማድረግ ይጥራሉ::

> 14ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ በቀረበው ማብራሪያ መሠረት፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚገኙት እብዛኞቹ ሽማግሌዎች መሪዎች ናቸው ወይስ አስተዳዳሪዎች? መልስህን አብራራ:: ለ) ቤተ ክርስቲያን ባለ ራእይ መሪ ሳይኖራት በማስተዳደሩ ሥራ ስትጠመድ ምን የሚከሰት ይመስልሃል? ሐ) ሁሉም ሽማግሌዎች ባለ ራእይ መሪዎች በመሆናቸው ምክንያት ነገሮችን የማስተዳደር ችግር ባለባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ችግሮች ይከሰታሉ? መ) ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ክብር ታድግ ዘንድ ሁለቱም ዓይነት አመራሮች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?

2. ቤተ ክርስቲያን ጤናማ እንድትሆን ከተፈለገ ባለ ራእይ መሪ ዎችና አስተዳዳሪዎች ያስፈልጓታል::

ምግብ ጣፍጦ እንዲበላ እንጀራና ወጥ አንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለቱም ስጦታዎች አስፈላጊዎች ናቸው:: ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ስለሚሰጠው ስጦታ ባስተማረበት ክፍል ውስጥ እንደ ገለጸው፣ አንዳንዶች የመሪነት ስጦታ ተሰጥቷቸዋል:: (ኤፌ. 4:11-12 አንብብ - ሐዋርያት፣



ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ አስተማሪዎች::) እንዲሁም ደግሞ ለሌሎች የማስተዳደር ስጦታ እንደ ተሰጣቸው ገልጾአል:: ይህም ከመሪነት የተለየ ስጦታ ነው:: (1ኛ ቆሮ. 12:18ን አንብብ:: በዚህ ቦታ ጳውሎስ የአስተዳደርን ስጦታዎች ከአመራር ስጦታዎች ነጥሏል::)

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የት ጋ መለወጥና ማደግ እንዳለባት የሚያውቁ ባለ ራእይ መሪዎች ከሌሉባት ቤተ ክርስቲያን ልታድግ አትችልም:: ባለ ራእይ መሪዎች ከሌሉ፣ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት በመርገጥ በቀላሉ ልትጠወልግ ትችላለች:: ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው መስመር እንድትጓዝ አቅጣጫ የሚያስይዙ መሪዎች መኖራቸው ወሳኝ ነው::

ይሁንና፣ ባለ ራእይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥን መፈለግ ያለባቸው ለለውጥ ያህል ብቻ መሆን የለበትም:: ለውጡ የቤተ ክርስቲያን አባላትና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን እንዲሆኑ የሚያግዝ መሆን አለበት:: የተፈለገው ዕድገት ወደታለመው ራእይ የሚመራቸው እንጂ፣ እንዲሁ ለውጥና ዕድገት ብቻ መሆን የለበትም::

በሌላ በኩል፣ ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያንን ለመለወጥ የሚያስችሉ መልካም አሳቦች ኖረዋቸው እነዚህኑ አሳቦች ወደ ጥሩ ዕቅዶች ለመለወጥ የሚቸገሩ ከሆነ፣ ብዙ ውጤት ሊገኝ አይችልም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ የማይካሄዱ ከሆነ፣ የገንዘብና የጉልበት ብክነት ይፈጠርና የሰዎች ልብ ያዝናል:: በመሆኑም፣ ዝርዝር ዕቅዶችን በማውጣት አገልግሎቶችን የሚያደራጁ አስተዳዳሪዎች አብያተ ክርስቲያናት ያለ ብዙ ውጣ ው ረድ ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ ያስችሏቸዋል::

3. ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይኖሩ የማስተዳደር ስጦታ ብቻ ባላቸው ሰዎች መመራቱ አደገኛ ነው::

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲቀጥል ለማድረግ ወዲያ ወዲህ ስለሚሯሯጡ፣

ሥራ ይበዛባቸዋል፡፡ አገልግሎቶቹ በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄዱ ለማድረግ ስለሚሯሯጡ እምብዛም፣ «እንደ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ ያለብን ነገር ምንድን ነው? በማኅበረሰባችን ውስጥ ብርሃን እንድንሆን እግዚአብሔር ምን ይጠብቅብናል? ከእነዚህ ሁሉ የአገልግሎት በሮችና ካሉን ውስን ሀብት አንጻር እግዚአብሔር በምን ላይ ትኩረት እንድናደርግ ይፈልጋል?» ብለው አይጠይቁም፡፡ እነዚህ ራእይ ያለው አመራር የሚያነሣቸው እንጂ የአስተዳደር ጥያቄዎች አይደሉም፡፡ ምናልባትም ቤተ ክርስቲያኖቻችን ደካማና ውጤታማ ከማይሆኑባቸው ምክንያቶች አንዱ ራእይ ያለው አመራር የሚሰጡ ሽማግሌዎች በብዛት አለመኖራቸው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ራእይ ያለው መሪ (ወይም ራእይ ያለው የሽማግሌዎች አካል) ሕዝቡን ወደ አንድ ግብ የሚመራ መሆኑን አስታውስ፡፡ ይህም ለውጥና ዕድገት የሚያመጣ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሽማግሌዎች ከአመራር ይልቅ በአስተዳደር ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ማደጓን ታቆምና ትሞታለች፡፡ (ማስታወሻ - የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአስተዳደርን ሚና አሳንሰው የሚያዩ ከሆነም አደገኛ ሁኔታዎች መፈጠራቸው የማይቀር ነው፡፡ መሪዎች ታላላቅ ራእዮች ኖረዋቸው በቤተ ክርስቲያን ጥሩ የአሠራር ዘዴዎችን ሳይገነቡ ሲቀሩ ወይም በቤተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል ያሉት ተግባቦቶች ሲዳከሙም ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ ዋናው ነገር ሁለቱም ዓይነት መሪዎች ለእግዚአብሔር ክብር አብረው መሥራታቸው ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በቀዳሚነት በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የመሥራቱን ፈተና መቋቋም አለባቸው፡፡ እነዚህም በሰዎች መካከል ያሉትን ክፍፍሎች እንደ መቅረፍ፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎቻችን የማያምኑ ሰዎችን የሚስቡ ማራኪ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የሠራተኛ ቅጥር፣ በጀት ማጽደቅ፣ ወዘተ . . . ያሉ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች ቢሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ ላይ ካተኮሩ፣ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ጥልቀትና ውጤታማ አገልግሎት ልታድግ አትችልም፡፡



ከዚህም የተነሣ፣ ለማኅበረሰቡ ወንጌሉን ለማዳረስና አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማስቻል ጥሩ መሣሪያ ሳትሆን ትቀራለች፡፡ በመጨረሻም፣ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ይዳፈንና እግዚአብሔር ራእዩን ለመስወጥና ለማደግ ለምትፈልግ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሰጣል፡፡ በሚገባ የተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ብትኖረንና ዳሩ ግን በመንፈሳዊ ብስለትና በአገልግሎት እያደገች የማትሄድ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በዚህች ቤተ ክርስቲያን አይደሰትም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚፈልጋትን ዓይነት ሆና ለመኖር ሁልጊዜም በመንፈሳዊ ብስለትና በአገልግሎት ማደግ እንጂ ባለችበት መርገጥ የለባትም፡፡ ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ሥራዎች ማስተዳደር ብቻ ባይሆን፣ ራእይ ያለው አመራር መስጠት እንዳለባቸው መጠንቀቅ አለባቸው፡፡

4. የቤተ ክርስቲያን አባላት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ ወዳለው ግብ ካልተመሩ፣ ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ ዕድገታቸውን በማቆምና ራስ ወዳድ በመሆን እርስ በርሳቸው መጣላት ይጀምራሉ፡፡

15ኛ ጥያቄ፡- ምሳሌ 29፡18ን አንብብ፡፡ ሀ) ሰሎሞን ራእይ በማይኖር ጊዜ ምን ይከሰታል ሲል አስጠነቀቀ? ለ) መሪን የሚለው ቃል ምንን ያሳያል? ሐ) ይህ ጥቅስ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እውነት ሲሆን ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ምሳሌ 29፡18ን ሲገልጽ፣ «ራእይ ከሌለ ሕዝብ ይጠፋል» ይላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደየትኛው ግብ ለማድረስ እንደሚፈልግ ካላወቁ፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይጠወልጉና ቤተ ክርስቲያን ትሞታለች፡፡ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ወዴት ሊመራት እንደሚፈልግ ካልታወቀ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች መበላሸት ይጀምራሉ፡፡ ሌላው የምሳሌ 29፡18 ትርጉም እንደሚነግረን፣ «ራእይ በማይኖርበት ጊዜ ሕዝቡ ልቅ ይሆናሉ፡፡» ያለ ራእይ ሕዝቡን አንድ ማድረግ ከባድ ነው፡፡

ራስን በአምልኮ ደስ ከማሰኘት ያለፈ ትልቅ ራእይ ከሌለ፣ ሰዎች ራስ ወዳዶች ይሆኑና እርስ በርሳቸው ጸብ ይጀምራሉ። ነገር ግን ሁሉንም ሰው የሚያስማማ ራእይ በሚኖርበት ጊዜ፣ ሁሉም ያንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲጥር አንድነት ይፈጠራል። ምእመናን እግዚአብሔር በመካከላቸው ሲሠራና ሕዝቡ ሲለወጥ ሲያዩ ደስተ ኞች ይሆናሉ።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ግንባታ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላት የተሻለ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መገንባት እንዳለባቸው በሚስማሙበት ጊዜ ደስ ይላቸዋል። ገንዘባቸውን፣ ጌጣ ጌጦቻቸውን፣ ልብሶቻቸውን፣ ወዘተ. . . ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ በደስታ ይሰጣሉ። በየሳምንቱ ወደዚያው በመሄድ የተ ሠሩትን አዳዲስ ነገሮች ያያሉ። መሪዎች ፈቃደኞች የሆኑ ሰዎች መጥተው በግንባታው ላይ እንዲሠሩ ጥያቄ ቢያቀርቡ፣ አባላት በደስታ መጥተው ይሠራሉ። በሚያስገርም ሁኔታ፣ በዚህ ጊዜ በመሪዎችና በምእመናን መካከል የሚከሰተው ጸብ ይቀንሳል። ለሁሉም ሰው ሊታይ የሚችል ዕድገት በግንባታው ላይ እስከ ታየ ድረስ፣ ይህ የዓላማ አንድነት ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ ሥራዋን እንድታከናውን ያስችላታል። የቤተ ክርስቲያን ግንባታው ሲጠናቀቅ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ላከናወነው ተግባር ያመሰግኑታል።

ነገር ግን፣ የግንባታው ሥራ ቢቋረጥ፣ ወዲያውኑ አለመግባባቶች ይፈጠራሉ፣ ሽማግሌዎችና ሕዝቡ መጣላት ይጀምራሉ። ወይም ደግሞ የሕንጻው ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሕዝቡን ትኩረት፣ ጸሎትና ጉልበት የሚስብ ራእይ በማይኖርበት ጊዜ፣ ምእመናኑ ተስፋ መቁረጥና በራሳቸው ላይ ማተኮር ይጀምራሉ። በመሆኑም፣ መሪዎች ሕዝቡን እግዚአብሔር ወዳሰበው ራእይ መምራታቸው ወሳኝ ነገር ነው።

በመሆኑም፣ ራእይ ያለው አመራር ሕዝቡን ወደ አንድ ግብ መምራት ነው። ራእይ ያለው መሪ ሁልጊዜም ራሱንና ሕዝቡን መጠየቅ ያለበት ትልቁ ጥያቄ፣ «ትክክለኛ ነገሮችን እያደረግን ነው



ወይ? እግዚአብሔር እንድናከናውን የሚፈልጋቸውን ነገሮች እያከናወንን ነው?» የሚል ነው። እንዲህ ዓይነቱ መሪ ቤተ ክርስቲያን በምታከናውናቸው ተግባራት ሁሉ ውጤታማ እንድትሆን ይፈልጋል።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የቤተ ክርስቲያን አባላት አንድን ግልጽ ዓላማ ለማሳካት ሲተባበሩ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ሕዝቡ ተባብረው የሚፈጽሙት ግልጽ ዓላማ በማይኖርበት ጊዜ ራስ ወዳድ ሲሆኑ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። |

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ባለው ትልቅ ዓላማ ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው።

ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እንድትፈጽም ራእይ ያላቸው መሪዎችም ስጦታ ያላቸው አስተዳዳሪዎችም ያስፈልጓታል። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን፣ ራእይ ያላቸውም ሊሆኑ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን «በአስተዳዳሪዎች» የምትመራ ከሆነ፣ ሁኔታው ጎማ የሌለው አዲስ መኪና እንዳለው ሰው ነው። መኪናው ለማየት ደስ ቢያሰኝም፣ የትም አይሄድም። ዛሬ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የአስተዳዳሪዎችን ሚና በመጫወት ቤተ ክርስቲያን ውብና ለሌሎች ደስ የምታሰኝ እንድትሆን ይጣደፋሉ። ነገር ግን ራእይ ያለው አመራር ስለማይሰጥ፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እያደጉም ወይም ለእግዚአብሔር ውጤታማ አገልግሎት እያበረከቱም። ዛሬ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እናድግ ዘንድ እርሱ የሚፈልገውን ነገር የሚረዱ ራእይ ያላቸው መሪዎች ያስፈልጉናል። እግዚአብሔር ሥራውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ብዙ ብቃት ያላቸው አስተዳዳሪዎች ቢሰጠን መልካም ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ የሚረዱና ቤተ ክርስቲያንን እሁን ካለችበት እግዚአብሔር ወደሚፈልጋት ስፍራ የሚያደርሱ ብዙ መሪዎችንም ይስጠን። ይህንን ለምን ከዋና ዋና የጸሎት ጥያቄዎችህ አንዱ አታደርገውም? እግዚአብሔር በዘመናችን ሰዎችን ወደ ራሱ ራእይ የሚመሩትን ወንዶችና ሴቶች እንዲያስነሣ ልንጸልይ ይገባል።

እንዲህ ዓይነት ሰዎች ከሌሉን፣ ነቢዩ እንዳለው፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሰዎች የወንጌሉን ቃል ሳያሰሙ ይጠፋሉ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላትም ደካሞችና ውጤታማነት የራቃቸው ይሆናሉ::

በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ በሚያተኩረው ሁለተኛ መጽሐፋችን ውስጥ ራእይ ያለው አመራርና አስተዳደር የሚያሳድጉትን ክህሎቶች እንማራለን:: የምንጀምረው የአመራር ክህሎት በሆነው ራእይ ይሆናል:: ይህም እግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ የማወቅ ክህሎት ነው:: አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ትላልቅ ነገሮች ያስባሉ:: ይህም «እግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን ለእኛ ያለው ራእይ ምንድን ነው?» የሚል ዓይነት ነው:: ሌሎች ደግሞ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን አያስቡም፤ ቤተ ክርስቲያን እንደ ወትሮው እንድታዘግም ብቻ ይሻሉ:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራእይን መፍጠር ሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ሊማሩት የሚችሉት ነገር ነው:: ይህ ለአንዳንዶች ከሌሎች የበለጠ ጥረት ይጠይቃል እንጂ፣ በፍጹም የማይቻል አይደለም::

> *17ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች ትኩረት የሚያደርጉት በአስተዳደር ላይ ነው ወይስ በራእይ ሕዝቡን በመምራት ላይ ነው? መልስህን አብራራ:: ለ) መሪዎች ከአስተዳደር ይልቅ በራእይ ሕዝቡን ለመምራት እንዲችሉ ከግንዛቤአቸው ውስጥ መለወጥ ያለበት ምንድን ነው?*

## ሦስተኛ ቀን

አባተ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የእውራጃ ሽማግሌ ነው:: አዲስና ከዚህ በፊት የአውራጃው አመራር አካል ያልነበረ ሰው በመሆኑ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ከቃለ ጉባኤዎች ውስጥ ማንበብ ጀመረ:: የአውራጃው ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ክብር ምን ለማድረግ እየሞከረ እንዳለ ለመረዳት ፈለገ:: ቃለ ጉባኤዎችን በሚያነብበት ጊዜ፣ አብዛኞቹ ውሳኔዎች እንደ የወንጌላውያን ደመወዝ፣ አዲስ



የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ስለ መገንባት ወይም ስላለመገንባት፣ በቤተ ክርስቲያን የሥራ ቀኖችን ስለ መወሰን፣ የተጣሉ ሁለት ቤተሰቦችን ስለ ማስታረቅ፣ ወዘተ . . . የሚናገሩ መሆናቸውን ተረዳ:: ነገር ግን የአውራጃዋ ቤተ ክርስቲያን ወንጌሉን በአውራጃው ሁሉ ለመዳረስ ወይም የአማኞችን መንፈሳዊ ዕድገት ለማሳደግ ጥረት ማድረጉን የሚያሳይ ነገር በቃለ ጉባኤዎቹ ውስጥ እንዳልተጠቀሰ አስተዋለ::

በቀጣዩ የቦርድ ስብሰባ ላይ ያዘጋጃቸውን መጠይቆች አቀረበ:: በቀጣዩ የቦርድ ስብሰባ ላይ አሁን ያሉትን ችግሮች ከመፍታት ይልቅ፣ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ መነጋገር እንዳለባቸው አሳሰበ:: እርሱ ያዘጋጃቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ:- «ባለፉት ሁለት ዓመታት የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዴት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሲያድጉ እንደ ተመለከትክ ግለጽ:: ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ ውጤታማ የወንጌል አገልግሎት ስትሰጥ ያየኸው እንዴት ነው? ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በብስለት እንዲያድጉ ለማገዝ ልናደርጋቸው የሚገቡንን አምስት ነገሮች ዘርዝር:: ለማኅበረሰባችን መልካሙን የምሥራች ለማዳረስ ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?»

> *18ኛ ጥያቄ:- የአውራጃ ቦርድ ስብሰባውን ሁለት አቀጣጫዎች አነጻጽር:: አብዛኞቹ የቦርድ ስብሰባዎች ቦርዱ ቀደም ሲል ያደርግ ከነበረው ይልቅ አባተ ያነሣቸውን ዓይነት ጥያቄዎች የሚያስተናግድ ቢሆን ምን ዓይነት ለውጦች ይከስታሉ ብለህ ታስባለህ?*
>
> *19ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው ለአንድ አገልግሎት «ራእይ» አለው ስንል ምን ማለታችን ነው? ለ) አንድ ሰው ለአንድ አገልግሎት ራእይ የሚያገኘው እንዴት ነው? አንድ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ፈልግና የአገልግሎት ራእያቸውን እንዴት እንዳገኙ ጠይቃቸው:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ራእይ መንደፋቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል?*

## ለአገልግሎት ራእይ መንደፍ ማለት ምን ማለት ነው?

«ራእይ» የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ በተለያዩ መንገዶች ያገለግላል። ስለዚህ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንጠቀምበትን መንገድ ማወቁ አስፈላጊ ይሆናል። «ራእይ» የሚለው ቃል በሁለት ዓበይት መንገዶች ያገለግላል።

1. ትንቢታዊ «ራእይ» እግዚአብሔር ዕቅዶቹን ለአንድ ግለሰብ በሕልም ወይም የሆነ መንፈሳዊ እውነታ ባለው አስተሳሰብ የሚለጥበት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው የመጨረሻው መጽሐፍ «የዮሐንስ ራእይ» በመባል ይታወቃል። ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር ለዮሐንስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆነው ነገር የገለጸለት መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ዛሬም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕቅዶቹን በዚህ መንገድ ሊያሳውቅ ይችላል። ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «ራእይ» የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በዚህ መንገድ አይደለም። ስለ አገልግሎት ራእይ በምንነጋገርበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች የነቢያትን ዓይነት ተሞክሮ፣ ማለትም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድታደርግ የሚፈልገውን ነገር በሕልም ሊያሳያቸው ይገባል ማለታችን አይደለም።

2. በአገልግሎታችን ልናከናውን የምንፈልገውንም ነገር ለመግለጽ «ራእይ» የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የሚወጡ አዳዲስ ምሩቃንን፣ «ስትመረቅ ራእይህ ምን ይሆናል?» ብለን እንጠይቃለን። እነርሱም፣ «ወንጌሉን ወዳልደረሰበት ስፍራ እወስደዋለሁ።» ወይም «አገልጋዮችን ለቤተ ክርስቲያኔ ለማዘጋጀት ስለምፈልግ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ አስተምራለሁ» በማለት ይመልሳሉ። ለአንድ ሽማግሌ ለቤተ ክርስቲያኑ ምን ራእይ እንዳለው ብንጠይቅ ደግሞ፣ «ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የወንጌል ስርጭት ተግባር እንድታከናውን እፈልጋለሁ፣» ወይም «ቤተ ክርስቲያናችን በማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉትን ድሆች እንድትረዳ እፈልጋለሁ፣» ብሎ ሊመልስ ይችላል። በግልጽ ራእይ ስለ መምራት በምንነጋገርበት ጊዜ፣ «ራእይ» የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በዚህ መንገድ ነው።



እንግዲህ መሪዎች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ሊያደርግ የሚፈልገው ሥራ ራእይ ሊኖራቸው ይገባል ስንል ምን ማለታችን ነው? ራእይ እግዚአብሔር በአገልግሎት ወይም በሥራ ማከናወን ስላለብን ተግባር የሚሰጠን ግልጽ የአእምሮ ምስል ነው። ከዚህ ፍች፣ ስለ አገልግሎት ራእይ አያሌ ጠቃሚ ነገሮችን ልንመለከት እንችላለን።

ሀ. ራእይ የሚመጣው <u>ከእግዚአብሔር</u> ዘንድ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ እንዳልሆነች ማወቅ አለባቸው። ለቤተ ክርስቲያን የራሳችንን ዕቅዶች በማውጣት ሰዎችን እንዲታዘዙን ለማድረግ መጣር የለብንም። የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ነው። (ቈላ. 1:18ን አንብብ።) መሪዎችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ መረዳት የመሪዎችና የምእመናን ኃላፊነት ነው። እግዚአብሔር ዕቅዱን ለቤተ ክርስቲያን በሚገልጽበት ጊዜ፣ ያ የቤተ ክርስቲያን ራእይ ይሆናል። በአገልግሎቷ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ ትጥራለች።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፈቃድ ከመፈለግ ይልቅ በራሳቸው ራእይና ዕቅዶች ላይ ትኩረት ሲያደርጉ የተመለከትካቸውን ሁኔታዎች አብራራ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ዕቅድ ማወቃቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊያውቁ የሚችሉት እንዴት ነው? ምእመናን ከመሪዎች ጋር ስቤተ ክርስቲያናቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚኖራቸው ሚና ምንድን ነው? |

ለ. ራእይ በሥራችን አማካኝነት ለመፈጸም የምንሞክረው <u>እሳብ</u> ነው። እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠር ከመጀመሩ በፊት ግሩም ፍጥረት የማምጣት ራእይ ነበረው። እግዚአብሔር አብርሃምን ከመጥራቱ በፊት ዓለምን የሚባርክበትን ቅዱስ ሕዝብ የማምጣት ራእይ ነበረው። እግዚአብሔር የአሕዛብ ሐዋርያ የሆነውን ጳውሎስን ከመጥራቱ በፊት የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች

በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ይቅርታ አግኝተው በእኩልነት ማምለካቸው ራእዩ ነበር:: ስለሆነም፣ ለአንድ አገልግሎት ያለን ራእይ ተግባራዊ ልናደርግ ስለምንፈልገው ነገር በአእምሯችን ውስጥ ያለው ግብ ነው::

ሐ. ሦስተኛ፣ ራእይ ወደፊት የሚከሰትን ነገር ያመለክታል:: እየተፈጸመ ያለውን ነገር አያመለክትም:: ለአንድ አገልግሎት ራእይ አለን ማለት፣ ያ አገልግሎት አልተጀመረም ወይም ከምንፈልገው ደረጃ ላይ አልደረሰም ማለት ነው:: ለምሳሌ፣ ሰዎች አልፎ አልፎ የሚሰባሰቡበት የሰንበት ትምህርት አገልግሎት አለን እንበል:: በዚህ ጊዜ «ራእያችን» የሚሆነው የሰንበት ትምህርት መጀመር ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያናችንም ሆነ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሁሉም ዕድሜ ክልል ልጆች በየእሑዱ የእግዚአብሔርን ቃል የሚማሩበት የሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲኖረን ይሆናል:: ይህ ገና እውን እንዳልሆነ እናውቃለን:: ነገር ግን ወደፊት እንዲፈጸም ተስፋ የምናደርገውና የምናልመው ነገር ነው:: ራእይ ገና እውን ያልሆነና የተወሰኑ ነገሮች ካደረግን ወደፊት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የአእምሮ ሥዕል ነው::

መ. ራእይ በመጨረሻ ውጤቶች ላይ ወይም አንድ ነገር በሚፈጸምበት ጊዜ ለማየት በምንፈልገው ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ራእይ በሚቀጥለው ዓመት እንዲከናወኑ የምንፈልጋቸው ዕቅዶች ዝርዝር አይደለም:: ይልቁንም፣ ራእይ ለማከናወን የምንፈልገውን ተግባር ግብ መረዳት ነው:: ስለዚህ «ራእይ» ከቤተ ክርስቲያናችን ሁለት ወንጌላውያንን መላክ አይደለም:: ራእይ ሊሆን የሚችለው ጠንካራ የወንጌል ስርጭት የምታከናውን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ነው:: ሁለት ወንጌላውያንን መላክ የጠንካራ የወንጌል ስርጭት አንድ አካል ብቻ ነው::

ሠ. ራእይ ቢያንስ በከፊል በእግዚአብሔር ርዳታ የሚፈጸም ነው:: ይህ ሊሆን የማይችል ምኞት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ኃይል ራሳችን ልንፈጽም የምንችለው ነው:: ስለዚህ የአጥቢያ ቤተ



ክርስቲያን ራእይ በዓለም ላይ ያሉትን ሰዎች ሁሉ በወንጌል መድረስ ሊሆን አይችልም:: አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ልታደርግ አትችልም:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራእይ ወንጌልን በዓለም ውስጥ ማሰራጨት ሊሆን ይችላል:: የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ ይህንን ልናደርግ እንችላለን::

## ራእይ እግዚአብሔር እኛንና ቤተ ክርስቲያቻችንን የሚጠቀምበትን ሁኔታ ያቀላጥፋል::

ሕይወታችንን ለመለወጥ ወይም ቤተ ክርስቲያኖቻችንን ከውጤት-አልባነት ወደ ውጤታማነት ለመቀየር ልንጠቀም ከምንችላቸው እጅግ ኃይለኛ ነገሮች አንዱ ራእይ ነው:: ብዙዎቻችን ግላዊ ዕድገት ከማናሳይባቸውና ቤተ ክርስቲያኖቻችን ስኬታማ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከሚቸገሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ልንፈጽም ስለምንፈልጋቸው ነገሮች ግልጽ ራእዮች ስለሌሉን ነው:: ለግል ሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለመፈጸም ለምንፈልጋቸው የአጭር ጊዜ ተግባራትና ለቤተ ክርስቲያናችን የረዥም ጊዜ ዕድገት ግልጽ ራእይ ወይም ግብ መኖሩ የስኬት ቁልፍ በመሆን ያገለግላል:: ግልጽ ራእይ በግል ሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ከዚህ በታች ካሉት ምሳሌዎች ተመልከት::

1. ግላዊ ራእይ:-

ሀ. ሕይወት ያለ ራእይ:- አብዛኞቹ ሰዎች ለመሆን ወይም ለማድረግ ስለሚፈልጉት ነገር ግልጽ ራእይ የላቸውም:: በጠዋት ተነሥተው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፣ ወደ ቤት ይመለሳሉ፣ ይጫወታሉ፣ ይመገባሉ፣ ከዚያም ይተኛሉ:: ጠንካራ ራእይ ስለሌላቸው፣ በሚገባ ሳያጠኑ ጊዜያቸውን ያባክናሉ:: በመሆኑም፣ አያድጉም፣ ከፍተኛ ትምህርት አግኝተው ትልቅ ደመወዝ የሚያገኙበትን ዕድልም ያጣሉ:: በመሆኑም፣ ከወላጆቻቸው የተሻለ ሕይወት ለመኖር አይችሉም:: ዕድገት እንኳን

ቢመጣ፣ ይህ በ«አጋጣሚ» የሚገኝ እንጂ የግልጽ ራእይና ዕቅድ ውጤት አይሆንም::

ለ. ሕይወት ያለ ግልጽ ራእይ:- ያለን ራእይ «መማር እፈልጋለሁ» የሚል ሊሆን ይችላል:: ይህ ካለ ምንም ራእይ ይሻላል:: ቢያንስ የሕይወት ግብ አለን፣ ይህም መማር ነው:: አሁን ጊዜያችንን ተጠቅመን ልናጠና እንችላለን:: ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ የሚያስችል ገንዘብ እንዲኖረንም ማጠራቀም እንጀምራለን:: ግልጽ ያልሆነ ራእይ ራእይ-አልባ ከመሆን ይሻላል:: ምክንያቱም ይህ የምንሄድበትን አንድ አቅጣጫ ያሳየናል:: ብዙውን ጊዜ በትምህርቱ የሚገፋው ተማሪ ከማይገፋው የሚለየው፣ በትምህርቱ የሚገፋው ግላዊ ራእይ ሲኖረው፣ የማይገፋው ግን ራእይ የሌለው መሆኑ ነው:: ለሕይወታቸው «ራእይ» ያላቸው አብዛኞቹ ሰዎች ስለሚፈልጉት ነገር ያላቸው አሳብ ደብዛዛ ነው:: እነዚህ ሰዎች እያደጉ ቢሄዱም፣ ከግባቸው አይደርሱም::

ሐ. ግልጽ ራእይ ያለው ሕይወት:- «የሕዝቤን የጤና ችግር ለመፍታት የሚችል ዶክተር ለመሆን እፈልጋለሁ፣» የሚለው ግልጽ ራእይ ሊሆን ይችላል:: እግዚአብሔር አንድን ነገር እውን ለማድረግ ራእይን የሚጠቀምበት መንገድ አስገራሚ ነው:: ይህ ግልጽ ራእይ ግለሰቡን እንዴት እንደሚረዳው አስብ:: በመጀመሪያ፣ ዶክተር ለመሆን በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት እንዳለበት ያውቃል:: ስለዚህ፣ ከመጫወት ይልቅ ያለውን ጊዜ ሁሉ ተጠቅሞ ያጠናል:: ሁለተኛ፣ ከዚህ ግብ ለመድረስ ብዙ ነገሮችን መሠዋት እንዳለበት ያውቃል፣ የሚኖርበትን አካባቢ ትቶ የተሻለ ትምህርት ወደሚሰጥበት አካባቢ መሄድ ይኖርበታል:: የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታውን ለማሻሻል ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል:: ሦስተኛ፣ ጥሩ ሊሆኑ የሚችሉና ነገር ግን ሕልሙን እውን ለማድ ረግ የማያግዙትን ነገሮች መተው አለበት:: ስለዚህ አንድ ሰው፣ «ወደዚህ ኮሌጅ ግባና የምሕንድስና ዲግሪ ያዝ፣» ቢለው፣ ይህ እርሱ የሚፈልገው ነገር እንዳልሆነ ስለሚያውቅ፣ የሕክምና ዶክተ ር ለመሆን የሚያስችለውን መስመር ይዞ መጓዙን ይቀጥላል::



አራተኛ፣ ሕይወቱን ትርፋማ ሊያደርግ የሚፈልግበትን ቦታ እንዲያውቅ ይረዳዋል:: ራእዩ ያደገበትን አካባቢ ሕዝብ ማገልገል ከሆነ፣ በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ሄዶ እንዲሠራ የሚቀርቡለትን አጋጣሚዎች አይቀበልም:: ይህንንም የሚያደርገው በአካባቢው የሕክምና አገልግሎት መስጠት ስላለበት ነው:: ለእርሱ አስፈላጊው ነገር ገንዘብ ወይም ጥሩ ሕይወት ሳይሆን፣ ሕዝቡን መርዳቱ ይሆናል:: በመሆኑም፣ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አንዳንድ ምቾቶችን ለመሠዋት ፈቃደኛ ይሆናል:: እግዚአብሔር በሕይወታችን ምን እንድናደርግለት እንደሚፈልግ ግልጽ የሆነ ራእይ በኖረን መጠን፣ ያንን ራእይ እውን ለማድረግ የምናከናውነው ተግባር ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል:: ይህም ለእግዚአብሔር በምንሰጠው አገልግሎት በበለጠ ስኬታማ እንድንሆን ያስችለናል::

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ ከተሰጠው ምሳሌ፣ ራእይ ያለው ሕይወት ምን ጥቅም የሚያስገኝ ይመስልሃል? ለ) ራስህን እንዴት ለመጠቀም እንደምትፈልግ የሚያሳይ የግል ራእይህን ግለጽ:: ሐ) አሳቦችህ ጥርት ካላሉ፣ ምርጫዎችህን የሚመራ ግልጽ ራእይ ለማግኘት ምን ልታደርግ ትችላለህ?

**2. የአጭር ጊዜ ራእይ ለቤተ ክርስቲያን:-**

ሀ. የአጭር ጊዜ ራእይ የሌላት ቤተ ክርስቲያን:- አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔርን ለማስከበር ሊያደርጉ ስለሚፈልጓቸው ነገሮች ራእይ ስለሌላቸው፣ ሽማግሌዎች ውሳኔ ዎችን የሚሰጡት እንደ ሁኔታው አስገዳጅነት ነው:: ሕዝቡ፣ «የመዘምራን ልብስ ያስፈልገናል» ካለ፣ ከዚህ አሳብ ጋር በመስማማት ያላቸውን ገንዘብ ለዚሁ አገልግሎት ያውላሉ:: አንድ ሰው ከአውራጃው ቢሮ መጥቶ፣ «ለወንጌል ስርጭት የገንዘብ ድጋፍ አድርጉ» ቢላቸው፣ ሽማግሌዎቹ የመዘምራን ልብስ ከገዙ በኋላ የተረፈውን ገንዘብ ሊሰጡ ይችላሉ:: ከዚያ በኋላ ሌላ ሰው መጥቶ ገንዘብ እስኪጠይቃቸው ድረስ የወንጌል ስርጭት ጉዳይ ትዝ ላይላቸው ይችላል:: ራእይ የሌላት ቤተ ክርስቲያን እርምጃ

ዎችን የምትወስደው እስቀድማ ሳታቅድና የእግዚእብሔርን ገንዘብ በአግባቡ እየተጠቀመች መሆኗን ከግንዛቤ ውስጥ ሳታስገባ ሁኔታ ዎችን እንደ አመጣጣቸው ለመቀበል ትገደዳለች:: እንዲህ ዓይነቷ ቤተ ክርስቲያን ከዓመት እስከ ዓመት እምብዛም ዕድገት ሳታሳይ ትቆያለች::

ለ. ግልጽ ያልሆነ የአጭር ጊዜ ራእይ ያላት ቤተ ክርስቲያን:- ሽማግሌዎች፣ «የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መክፈት እንፈልጋለን» ይላሉ:: ከዚያም ከቤተ ክርስቲያን የእውራጃ ጽ/ቤት ለትምህርት ቤቱ ሕንጻ ማሠሪያ ገንዘብ ይጠይቃሉ:: ሕንጻው ተሠርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ እስተማሪዎች ይፈልጋሉ:: በመቀጠልም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር ፍላጎቱና ጊዜው ያላቸው ለዎች መጥተው እንዲማሩ ማስታወቂያ ይናገራሉ:: ብዙ ተማሪዎች ይመጡና ትምህርት ቤቱ በጥሩ ሁኔታ ሥራውን ይጀምራል:: ከሁለት ዓመታት ሥልጠና በኋላ ተማሪዎቹ ይመረቃሉ:: ይህ ደብዛዛ ራእይ ራእይ-አልባ ከመሆን እንደሚሻል ግልጽ ነው:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም በራእያቸው ውጤት ደስተኞች ናቸው:: ነገር ግን ራእዩ ግልጽ ባለመሆኑ ምክንያት በቤተ ክርሰቲያን ላይ የሚያመጣው ለውጥ ውስን ነው::

ሐ. ግልጽ የአጭር ጊዜ ራእይ ያላት ቤተ ክርሰቲያን:- የቤተ ክርሰቲያኒቱ የእውራጃ መሪዎች፣ «በእያንዳንዱ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን መጋቢዎችን የሚያዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ያስፈልጉናል» ይላሉ:: እነዚህ መሪዎች ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶቻቸው ግልጽ ራእዮች አሏቸው:: ዓላማው መጋቢዎችን ማዘጋጀት እንጂ፣ ወንጌላውያንን ወይም የቤተ ክርሰቲያን ሽማግሌዎችን ማዘጋጀት እይደለም:: ለሕዝቡ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት መስጠትም ብቻ በቂ አይሆንም:: ስለዚህ ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚያዘጋጁት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለመሆን የሚያስችል እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው በሚያግዝ መልኩ ይሆናል:: አስተማሪዎቹም የመጋቢነት ልምድ ያላቸውና ይህን ልዩ አገልግሎት ለማካሄድ



ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋሉ:: ወንጌላውያኖቻቸው ይህን የማስተማር ተግባር እንዲያከናውኑ አያደርጉም:: ምክንያቱም ወንጌላውያኑ ይህ ልዩ ሥልጠና እንደሌላቸው ያውቃሉ:: መሪዎቹ ሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር በመጋቢነት እንዲያገለግል የሚፈልጋቸውን ሰዎች በጸሎት እንዲመርጡና ለሥልጠና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲልኳቸው ይጠይቃሉ:: ተማሪዎቹ «መማር» የሚፈልጉ ብቻ ሳይሆኑ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ተመልሰው በመጋቢነት ለማገልገል የወሰኑ ይሆናሉ:: ይህ ግልጽ «ራእይ» የእውራጃው ቤተ ክርሰቲያን መሪ ዎች በየአጥቢያ ቤተ ክርሰቲያኑ መጋቢዎችን ለማዘጋጀት የወጠኑትን ዕቅድ በተሻለ ሁኔታ እንደሚያሟላ ግልጽ ነው:: ራእዩ ግልጽ በሆነ መጠን፣ መሪዎች የሚፈልጉትን ተግባር በፍጥነት ለማሟላት ይችላሉ:: በአንጻሩ፣ ራእዩ ግልጽነት በጎደለው መጠን ቤተ ክርሰቲያን ለውጥ ለማምጣት የሚያስፈልጋትን ተግባር እውን ለማድረግ ትቸገራለች::

> 22ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርሰቲያን ውሰጥ ግልጽ የአጭር ጊዜ ራእይ ማዘጋጀት ምን ምን ጥቅሞች አሉት? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ያላትን «ደብዛዛ» ራእይ ግለጽ:: ቤተ ክርስቲያን ያንን ራእይ ምን ያህል በአጥጋቢ ሁኔታ ተግባራዊ እያደረገች ነው? ሐ) መሪዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለሚፈልጉት ነገር ግልጽ ራእይ ቢኖራቸው ምን ለውጥ እንደሚገኝ ግለጽ::

በወደቀና መንፈሳዊ ጨለማ በነገሠበት ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል በዓለም ውስጥ እንድታበራ ጠርቷታል:: ብርሃናችንን የምንፈነጥቅበት መንገድ የሚወሰነው እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንዴት እንድናገለግል እንደሚፈልግ ባላት መረዳት ላይ ነው:: ቤተ ክርሰቲያን ራእይ ከሌላት፣ ለእግዚአብሔር ታላቅ ተግባር ልታከናውን አትችልም:: ስለሆነም፣ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን፣ በተለይም መሪዎች፣ እግዚአብሔር ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሰጣቸውን አጠቃላይ ራእይና ለእያንዳንዷ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸውን የተወሰኑ ራእዮች ማወቅ

ይኖርባቸዋል። ለመሆኑ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን የተወሰነ ራእይ የሚያውቁት እንዴት ነው? በቀጣዩ ሳምንት ትምህርት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለእርሷ ያለውን ራእይ ለመረዳት ምን ልታደርግ እንደሚገባ በጥልቀት እንመረምራለን። ዛሬ ግን ለቤተ ክርስቲያኖቻችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉንን አንዳንድ መሠረታዊ እውነቶች እንመለከታለን።

## ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን ለምትፈልገው ተግባር ግልጽ ራእይ የማግኘት አስፈላጊነት

1. *ዘለቄታ ያላቸው ነገሮች ሁሉ ሁለት ጊዜ የተፈጠሩ ናቸው፣ መጀመሪያ በአእምሮ ውስጥ ከዚያም በሰዎች ሥራ ውስጥ።*

ዘላቂ የሆነ ነገር ሁሉ «ሁለት ጊዜ» መገንባት አለበት። መጀመሪያ አንድ ሰው ለማከናወን የሚፈልገውን ተግባር በሚያስብበት ጊዜ በልቡና በአእምሮው (በስሜቱ) ውስጥ ይሠራል። ግለሰቡ ለመፈጸም የሚፈልገውን ነገር በማወቅ እውን ለማድረግ መጣር አለበት። ራእዩን እውን ለማድረግ በሚጥርበት ጊዜ በተግባርም መገንባት አለበት።

ለብዙ መቶ ዓመታት የሚቆዩ ትላልቅ ሕንጻዎች በሚሠሩበት ጊዜ ይህንን እውነት እንመለከታለን። መሠረቱ ከመጣሉ፣ ጡቦቹ ከመያያዛቸውና ጣሪያው ከመሠራቱ በፊት ሕንጻው ተሠርቶ ማለቅ አለበት። የት ነው የሚሠራው? በሕንጻ ጥበብ ባለሙያው (በአርክቴክቱ) ጭንቅላት ውስጥ። ግሩም ሕንጻ ለመገንባት የሚፈልግ ሰው የሚያደርገው የመጀመሪያው ተግባር ለአርክቴክቱ ምን ዓይነት ቤት መሥራት እንደሚፈልግ የሚያመለክት ጠቅለል ያለ አሳብ መናገር ይሆናል። ከዚያም አርክቴክቱ ሕንጻው ተሠርቶ ሲያልቅ ምን መምሰል እንዳለበት ለሰዓታት ሲያሰላስል ይቆያል። በአእምሮው ውስጥ ያለውን የሕንጻ ንድፍ በወረቀት ላይ ይሥላል። ምናልባትም ውብ ሕንጻ ለመሥራት ወሳኙ እርምጃ ሕንጻው ተሠርቶ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ምን እንደሚመስል



በጥንቃቄ ንድፍ ማውጣቱ ሳይሆን አይቀርም። አሳቡ በአርክቴክቱ አእምሮ ውስጥ ይበልጥ ግልጽ ሲሆንና በአእምሮው ውስጥ ያለውንም አሳብ በሚገባ በሥዕላዊ መግለጫ (ንድፍ/ፕላን) አማካኝነት ሲገልጽ፣ የሚሠራው ሕንጻ የበለጠ ቆንጆ የመሆን ዕድል ይኖረዋል።

ይህ ሕንጻው ተሠርቶ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ምን እንደሚመስል የሚያሳየውን የመጀመሪያውን ግልጽ ንድፍ የመሥራቱ ተግባር በጥሩ ሁኔታ ካልተሠራ፣ ምናልባትም ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ። በመጀመሪያ፣ ሕንጻው ያን ያህል ቆንጆ ላይሆን ይችላል። የሕንጻው ሠራተኞች ሕንጻው ተሠርቶ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ምን እንደሚመስል በደንብ ስለማያውቁ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ንድፉን እየለወጡት ይሄዳሉ። ከዚህም የተነሣ አንደኛው የሕንጻው ክፍል ከሌላኛው የተለየ ሊሆን ይችላል። አንድ ዓይነት ስለማይሆንም ውበት ይጎድለዋል። ሁለተኛ፣ ብዙ ገንዘብ ይባክናል። ብዙውን ጊዜ በመጀመሪያው ላይ ዕቅዱ በጥሩ ሁኔታ ካልተነደፈ፣ ሲገነባና ሲናድ ብዙ ገንዘብ ይባክናል። ወይም ደግሞ ከሚፈልገው በላይ ሲሚንቶ፣ አሸዋ ወይም ቆርቆሮ ስለሚሸመት፣ የገንዘብ ብክነት ይከተላል።

የቤተ ክርስቲያን አመራርም እንዲሁ ነው። ቤተ ክርስቲያን ልታከናውን ስለምትፈልገው ነገር ግልጽ አሳብ ወይም ራእይ ካላት፣ ለእግዚአብሔር ክብር ያማረ ነገር ልትሠራ ትችላለች። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሕዝቡን ጥረቶችና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሀብት ሳያባክኑ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማድረግ እንዲችሉ ግልጽ ራእይ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም፣ በአመራር ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ለማከናወን ስለምንፈልገው ነገር ግልጽ ራእይ መያዝ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምንም ዓይነት አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ጥርት ያለ የአእምሮ ምስል ሊኖራቸው ይገባል። ሰዎች ዕቅዶቻችን በሚጠናቀቁበት ጊዜ ውጤቱ ምን እንደሚመስል በጥንቃቄ ማሰብን *«ፍጻሜው ምን ሊመስል እንደሚችል በማሰብ መጀመር»* ሲሉ

ይጠራሉ:: ለማከናወን የምንፈልገውን ነገር በደንብ ስናውቅ፣ ግባችንን ገንቢ በሆነ መንገድ ልንፈጽም እንችላለን::

ይህ ማለት ኮንፈረንስ ከማዘጋጀታችን በፊት፣ ስለ ኮንፈረንሱ ዓላማና እግዚአብሔር ኮንፈረንሱ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ሊፈጽም ስለሚፈልገው ተግባር ማሰብ አለብን ማለት ነው:: የኮንፈረንሱ ዓላማ የታመሙትን መፈወስ ነው? ሰዎች ለወንጌል ስርጭት ድጋፍ እንዲሰጡ ለማበረታታት ነው? ወይስ ለአማኞች ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመስጠት? ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ የኮንፈረንሱን ተናጋሪ ማን እንደ ሆነ፣ ወዘተ . . . ለመወሰን ያስችለናል:: ወይም ደግሞ የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ብንጀምር፣ ይህ ፕሮግራም በጥሩ ሁኔታ በሚካሄድበት ወቅት ምን እንደሚያደርግ በግልጽ ማወቅ አለብን:: ፕሮግራሙ የተነደፈው ለወጣቶች ነው፣ ወይስ ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን ምእመናን? ወይም ወንጌላውያንን ብንልክ የት ቦታና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሠሩ፣ እንዲሁም ምን ተግባር እንደሚያከናውኑ በጥንቃቄ ማሰብ አለብን:: ሥራው ሲጠናቀቅ ምን እንደሚመስል በማሰብ መጀመር ማለት ከዕቅዶቻችን አንዱንም ተግባራዊ ማድረግ ከመጀመራችን በፊት ምን ለማድረግ እንደምንፈልግ በቅጡ እናስባለን ማለት ነው::

> 23ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ለማከናወን የምትሞክራቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ለ) ሽማግሌዎች በእነዚያ ፕሮግራሞች ለማከናወን የሚፈልጓቸውን ነገሮች በትክክል የሚያውቁት ይመስልሃል? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚካሄዱትን ፕሮግራሞች ዘርዝርና ከእያንዳንዱ ፕሮግራም አጠገብ በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት ስእግዚአብሔር ክብር ምን ሊከናወን እንደ ታሰበ የተረዳኸውን አሳብ ጻፍ:: ያማረው «ፍጻሜ» ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?

**2. እግዚአብሔር የሚሠራው ለማከናወን የሚፈልጋቸውን ነገሮች ራእይ በማዘጋጀትና ቀጥሎም ወደ ተግባር በመለወጥ ነው::**



እግዚአብሔርም እንኳን አንድን ውብ ነገር የሚሠራው መጀመሪያ ሊያከናውን ስለሚፈልገው ነገር ራእይ በመንደፍ ነው:: ለምሳሌ:-

ሀ. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ የመጀመሪያውን «ይሁን» ከመናገሩ በፊት ሊሠራ ስለ ፈለገው ነገር በአእምሮው ውስጥ አንድ ምስል ነበረ:: የተጠናቀቀው ፍጥረት ምን እንደሚመስል ያውቅ ነበር:: ለዚህ ነው በፍጥረት ውስጥ ሁሉም ነገር በግሩም ሁኔታ የሚገጥመውና አንድን ወጥ ነገር የሚፈጥረው:: በፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮች ያልወደደውና መልሶ መሥራት እንዳስፈለገው የሚያመለክት ነገር የለም:: እግዚአብሔር አንድን ነገር ዘንግቶ በኋላ እንዳከናወነው የሚያሳይም ነገር የለም:: እግዚአብሔር ፍጥረትን እውን ከማድረጉ በፊት ሥራው ሲጠናቀቅ ምን እንደሚመስል ያውቅ ነበር::

ለ. እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን በሠራ ጊዜ፣ ማንም ሰው ምንም ከመሥራቱ በፊት እግዚአብሔር የጀመረው በዕቅድ ነበር:: በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ የመገናኛውን ድንኳን ራእይ ወይም ምስል አሳየው:: (ዘጸአ. 25:8-9ን አንብብ::) ከዚያም ሙሴ ያየውን ምሳሌ ተከትሎ ድንኳኑን እንዲሠራ ነገ ረው:: የመገናኛው ድንኳን በሚሠራበት ጊዜ ያየው ራእይ እውን እንዲሆን ሠራተኞቹን መምራት የሙሴ ኃላፊነት ነበር:: ይህም ውቡ የመገናኛ ድንኳን ሁለት ጊዜ እንደ ተሠራ ያሳየናል:: መጀመሪያ እግዚአብሔር የተጠናቀቀው የመገናኛ ድንኳን ምን እንደሚስል ለሙሴ ራእያዊ ምስል ባሳየው ጊዜ፤ እና ሁለተኛ፣ ጥበበኛ አናጺዎች ሥራውን ባጠናቀቁት ጊዜ::

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንዲሞትና ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ ወንጌልን እንድትሰብክ እግዚአብሔር የወጠነው ታላቅ የማዳን ዕቅድ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ በአሳብ ደረጃ ነበር የተጀመረው:: ከዓለም ፍጥረት በፊት፣ እግዚአብሔር ጠቅላላው ዓለም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ መሪነት አንድ ስለሚሆንበት ሁኔታ የአእምሮ ምስል ነበረው (ኤፌ. 1:9-

10):: እግዚአብሔር ያንን ታላቅ ራእይ በመያዝ ከአዳምና ሔዋን መፈጠር ጀምሮ እስከ የኃጢአት ውድቀት፣ የእስራኤል መመረጥ፣ የሕግ መስጠት፣ የኢየሱስ ልደትና ሞት፣ የወንጌል መስበክ፣ የቤተ ክርስቲያን መመሥረት ድረስ ያለውን ታሪክ ተቆጣጠረ:: ይህንንም ያደረገው ራእዩን እውን ለማድረግ ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ ታሪክ እግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅዱን በኢየሱስ ክርስቶስ አመራር ሥር ለማድረግ የተጠቀመበት እርምጃ ነበር::

በተመሳሳይ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች በሥራቸው ወደ ተግባር ከመለወጣቸው በፊት የአእምሮ ምስል እንደ ነበራቸው የሚያሳዩ ምሳሌዎች አሉ::

ሀ. የቤተ መቅደስ ግንባታ:- ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የመሥራት ዕቅድ ነበረው:: እግዚአብሔር ግን ይህንን እንዲያደርግ አልፈቀደለትም:: ስለዚህ ዳዊት የቤተ መቅደሱን «የመጀመሪያ» የአእምሮ ምስል ተመለከተ:: ንድፉን በማውጣት ለሥራው የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች አዘጋጀ:: ሰሎሞን እውነተኛውን «ሁለተኛውን» ቤተ መቅደስ አሠራ:: ነገር ግን የግንባታው ራእይ የተጀመረው በንጉሥ ዳዊት ነበር (1ኛ ዜና 28-29)::

ለ. የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ግንባታ:: በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ እንደ ተመለከትነው፣ ነህምያ የፈራረሱትን የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ከመመልከቱ በፊት ለእግዚአብሔር ክብር የተገነቡ ቅጥሮች ስላሏት ከተማ ራእይ ነበረው:: በዚያ «ራእይ» ላይ በመመሥረት ግልጽ ዕቅዶችን አወጣ:: ንጉሡ ቅጥሮቹን ለመሥራት ምን እንደሚፈልግ በጠየቀው ጊዜ፣ ነህምያ ጥርት ያለ ምላሽ ለመስጠት ችሎ ነበር:: ይህም ሊሆን የቻለው ሥራውን የሚያከናውንበትን ዕቅድ ስለ ነደፈ ነበር:: በመሆኑም፣ ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣ «ምን ልሥራ?» እያለ በማሰብ ያባከነው ጊዜ አልነበረም:: እግዚአብሔር ቅጥሮችን የመገንባት ኃላፊነት እንደ ሰጠው ያውቅ ነበር፣ ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግም ዝርዝር ዕቅድ ነበረው:: የከተማይቱ ቅጥሮች በ52 ቀናት ውስጥ ተሠርተው



የመጠናቀቃቸው አስገራሚ እውነታ የሚያሳየው (ነህ. 6:15-16)፣ የነህምያ ራእይና የድርጊት ዕቅድ ውጤታማ መሆኑን ነው::

ሐ. ጳውሎስ የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት የመገንባት ዕቅድ ነበረው:: ጳውሎስ ለኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር ስለ ነበረው ከየነገዱ ሰዎችን «ያለ ነቀፋ» (በቅድስና) ለክርስቶስ ለማቅረብ ይተጋ ነበር:: (2ኛ ቆሮ. 11:2ን አንብብ::) ጳውሎስ ይህ ራእይ ስለ ነበረው፣ ራእዩን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር:: ከተለያዩ ነገዶች የመጡ ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ መሰከረላቸው:: ነገር ግን ራእዩ የሰዎችን መዳን ብቻ ሳይሆን «ነቀፋ የሌላቸው» እንዲሆኑ ጭምር በመሆኑ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወታቸውን ለውጠው በቅድስና እንዲኖሩ ያስተምራቸው ነበር:: (የሐዋ. 20:20-21፤ 26-27፤ ቈላ. 1:28-29ን ተመልከቱ::) ጳውሎስ እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ለመፈጸም በሚጥርበት ጊዜ በግሉ መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11:21-29):: በመታሰሩም እንኳን ደስተኛ ነበር:: ምክንያቱም መታሰሩ ሰዎች በበለጠ ድፍረት ሳልዳኑት የሚመሰክሩበትን አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸው ነበር:: (ፊልጵ. 1:12-18ን አንብብ::)

እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እኛም ተመሳሳይ መንገድ መከተል አለብን:: እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያኖቻችን እንዲሆኑና እንዲያደርጉ ስለሚፈልገው ነገር ራእይ ለመንደፍ ተግተን መሥራት አለብን:: የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በዚህ እጅግ አስፈላጊ በሆነው የእግዚአብሔር ሥራ ላይ ብዙ ጊዜ ባጠፉ መጠን፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ በበለጠ ግሩም እድርገው ሊያከናውኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን የወጠነውን ዕቅድ ተግባራዊ ልናደርግ የምንችለው ልናደርግ የምንፈልገው ምን እንደ ሆነ ስናውቅ ብቻ ነው::

24ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም ቤተ እምነታችሁ ለክብሩ እንድታከናውን ያስቻላትን ዋና ዋና ነገሮች ዘርዝር:: ለ) ራእዩ የተጀመረው እንዴት ነበር? ሥራው መጀመሪያ

በአእምሮ ውስጥ፣ ከዚያም በተግባር እንዴት ሁለት ጊዜ ሊሠራ እንደ ቻለ አብራራ::

3. በዓለም ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ታላላቅ ነገሮች የተከናወኑት አንድ ሰው አንድን ታላቅ ተግባር ለመፈጸም ካለው ራእይ በመነሣት ነው:: ከዚያም ሰውየው ሕይወቱን ለዚያ ራእይ ይሰጣል::

ታሪክ ለዚህ ምሳሌ በሚሆኑ ነገሮች የተሞላ ነው:: በእንግሊዝ አገር የባሪያ ፍንገላ ሕጋዊነት የተሻረው በአንድ ሰው ጥረት ነበር:: ይህ ሰው የሕይወት ዘመኑን አብዛኛውን ክፍል ያሳለፈው ባሪያ ፍንገላን የሚደግፈውን ሕግ በመቃወም ነበር:: በመጨረሻም፣ ግለሰቡ በሞተበት ዓመት መንግሥት የባሪያ አሳዳሪነትን ሕጋ-ወጥነት ደነገገ:: ኮሎምበስ የተባለ ሰው ብዙ ሀብት አለ ብሎ ወደሚያስብበት የሕንድ አገር ለመሄድ (ከአውሮፓ) ሌላ መንገድ የማግኘት ራእይ ነበረው:: ብዙ ጊዜ ሲሞክር አልተሳካለትም ነበር:: የኋላ ኋላ ግን አሜሪካን አገኘ:: ኮምፒዩተሮችን ለሰዎች የማዳረስ ዓላማ የነበራቸው ሁለት ሰዎች ነበሩ የአነስተኛ ኮምፒዩተሮችን ቴክኖሎጂ የጀመሩት:: ከቤታቸው ጋር በተያያዘው አነስተኛ ክፍል ውስጥ ኮምፒዩተሮችን በመሥራት የጀመሩት እነዚህ ሰዎች ዛሬ በዓለም ውስጥ ከሚገኙ ታላላቅ የኮምፒዩተር አምራች ኩባንያዎች አንዱ ለመሆን ችለዋል:: በዓለም ላይ ቁጥር አንድ ከበርቴ የሆነው ቢል ጌትስ ለዚህ የበቃው ተራ ሰዎች ኮምፒዩተሮችን እንዲረዱ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን የመጻፍ ግላዊ ሕልም ስለ ነበረው ነው:: የኢትዮጵያ ኢቫንጄሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ የተጀመረው አንድ ወይም ሁለት ሚሲዮናውያን እግዚአብሔር የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዲግሪ ደረጃ የሚሰጥ ብቃት ያለው የሥነ-መለኮት ትምህርት እንዲደርሳቸው ይፈልጋል የሚል ራእይ ስለ ነበራቸው ነው:: የመቅሀማ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተጀመ ረው እግዚአብሔር በአንዲት ሚሲዮናዊት ሴት ልብ ውስጥ ሸክም ስላስቀመጠ ነው:: ይህች ሴት ከአሥር ዓመታት ለሚበልጡ ጊዜ ያት የጥናት መጻሕፍት ስትጽፍ፣ የሥልጠና ፕሮግራሞችን



ስታዘጋጅ ነበር የቆየችው:: አሁን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በኢትዮጵያ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ላይ ናቸው::

25ኛ ጥያቄ:- ሀ) የምታውቃቸው ሰዎች የነበሯቸውን ራእዮች ዘርዝር:: ለ) ከእነዚህ ራእዮች የተነሣ ምን ሊያከናውኑ እንደ ቻሉ ግለጽ::

ሰዎች ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርጉ የሚያነሣሣቸው ምንድን ነው? የሚያነሣሣቸው ታላቅ ራእይ መያዝና እግዚአብሔር ይህንን ራእይ ለመፈጸም እንደሚረዳቸው መተማመን ነው:: ብዙ ሰዎች የግል ራእዮች አሏቸው:: ትምህርት ለማግኘት ይፈልጉና በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ይጓዛሉ:: የሚፈልጉትን ትምህርት ለማግኘት እንዲችሉ ስደተኞች ሆነው ከአገራቸው ውጭ ይኖራሉ:: ወይም ሀብታም ለመሆን ይፈልጉና ዝቅ ያለ ኑሮ እየኖሩ ተግተው በመሥራትና ያገኙትን ገንዘብ በማጠራቀም ከፈለጉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: ብዙ ሰዎች የግል ራእያቸውን ከዳር ለማድረስ ብዙ ነገሮችን በመሠዋታቸው ዛሬ ሀብታሞች ለመሆን በቅተዋል:: የግል ራእያችን ራሳችንን በመጥቀም ላይ ያተኮረ በመሆኑ ራስ ወዳድነት የጎላበት ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ የግል ራእያችን ሌሎችን ለማገልገል የሚያስችለን ከራስ ወዳድነት የጸዳ ሊሆን ይችላል:: አንዳንድ ወንጌላውያን ወንጌሉን እጅግ ርቀው ለሚኖሩ ዘላኖች የማድረስ ራእይ አላቸው - ምንም እንኳን ይህ ከባድ ተግባር ቢሆንም:: ማዘር ተሬዛ በሕንድ ጎዳናዎች ላይ የሚኖሩትን ድሆች ለመርዳት ሲሉ ሕይወታቸውን ለዚሁ ተ ግባር አሳልፈው ሰጥተዋል:: በአሁኑ ሰዓት የማዘር ተሬዛ የመነኮ ሳት ሴቶች ማኅበር በዓለም ዙሪያ ድሆችን በመርዳት ላይ ይገኛል::

እንደ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ቡድኖችም ታላላቅ ነገሮችን ለመፈጸም ራእዮችን ሊነድፉ ይችላሉ:: በቻይና የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ወንጌሉን መልሶ ወደ ኢየሩሳሌም የመውሰድ ራእይ አላቸው:: ከቻይና ጀምረው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚሲዮናውያንን ወደ ምዕራባውያን አገሮች በመላክ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ በመጣር ላይ ናቸው:: እንደ ኮምፓሽን ያሉ ድርጅቶች የተጀመሩት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ፣ ሥራ ለማግኘትና ከድ-

ህነት ቀለበት ውስጥ ለመውጣት ምንም ዓይነት ዕድል የሌላቸውን ድሀ ልጆች ለመርዳት ለዎች ራእይ ስለ ነበራቸው ነው። ዛሬ ይህ ድርጅት በብዙ አገሮች ውስጥ ያሉትን ልጆች ለመርዳት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ያወጣል።

እነዚህ ምሳሌዎች እንደ ግለሰቦችና እንደ ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ታላቅ ተግባር ለማድረግ ከፈለግን፣ ልናደርግ ስለምንፈልገው ነገር ታላቅ ራእይ ሊኖረን እንደሚገባ ያሳያሉ። *እግዘአብሔር በእኛ በኩል ሊያከናውን ስለሚፈልገው ነገር ያለን ራእይ ትልቅ እየሆነ ሲሄድ፣ ለእግዚአብሔር የምናከናውነው ሥራም እንዲሁ ትልቅ ይሆናል። ነገር ግን ራእያችን ትንሽ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር የምናከናውነው ተግባርም ከራእያችን ያለፈ ሊሆን አይችልምና ትንሽ ይሆናል።*

**4.** እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ትልቅ ተግባር የማከናወን ራእይ የሚሰጠው ለግለሰቦች ወይም ለጥቂት ሰዎች እንጂ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን ወይም መንግሥት ላለ ትልቅ ቡድን አይደለም።

አንድ ግለሰብ ወይም ጥቂት ሰዎች አንድን ነገር የማድረግ ራእይ ሲኖራቸውና ራእዩ እውን ሲሆን ለማየት ተግተው ሲሠሩ ምን እንደሚከሰት ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች ያሳያሉ። በመንግሥት ወይም በኮሚቴ ራእይ ምክንያት እምብዛም ታላላቅ ለውጦች አይከሰቱም። ኮሚቴዎች፣ መንግሥት ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ራእዮች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ ሊያደርጉ ቢችሉም፣ ብዙ ጊዜ የራእይ ምንጭ አይሆኑም። አብዛኞቹ ታላላቅ ራእዮች የሚመነጩት ከግለሰቦች ወይም ከጥቂት ግለሰቦች ልብ ነው።

ይህንን እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ዓለምን ለመለወጥ በመሣሪያነት የሚጠቀምበትን ሕዝብ ለመፍጠር አንዱን ሰው አብርሃምን ነበር የጠራው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ነጻነት ለመምራት አንዱን ሰው ሙሴን ጠራው፤ የዓለምን ታሪክ የቀየሩትን ሕግጋትንም ለዚሁ ሰው ሰጠ።



እግዚአብሔር ደኅንነትን ለማምጣት ኢየሱስን ላከ። ወንጌሉን ለአሕዛብ ያዳርስ ዘንድ ጳውሎስን ጠራ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሁላችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነን ከብሉይ ኪዳን አይሁዶች እኩል እግዚአብሔርን የምናመልከው እግዚአብሔር ለጳውሎስ ራእይ በመስጠቱና ይህንኑ ራእይ በመፈጸሙ ነው። ስለሆነም፣ በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰቡ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ፣ ይህ ለውጥ እግዚአብሔር በመረጠው ግለሰብ ልብና አእምሮ ውስጥ መጀመር አለበት። ያ ግለሰብ ራእዩን ለመፈጸም ራሱን መስጠት አለበት።

ይህ ዛሬም እውነት ነው። እንደ ወርልድ ቪዥን ያሉ ትላልቅ ድርጅቶች ሳይቀር የተመሠረቱት በአንድ ሰው ራእይ ነው። ወርልድ ቪዥን የተጀመረው በእስያ ረሃብ በተከሰተ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንድረዳ ጠርቶኛል የሚል እምነት በነበረው አንድ ሰው ነበር። ይህ ሰው ድሆችን ለመርዳት ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ብዙም ሳይቆይ ግለሰባዊ ጥረቱ ወደ ትልቅ ድርጅትነት ተ ቀየረ። ብዙ የሚሊዮን ድርጅቶች የተጀመሩት በአንድ ወይም በሁለት ግለሰቦች ነው። ኤስ አይ ኤም የተጀመረው ሦስት ሰዎች ከሰሃራ በረሃ በስተ ደቡብ ባለው የአፍሪካ ክፍል ወንጌሉን ለማዳረስ በመፈለጋቸው ነው። በዚህ ስፍራ በጊዜው ምንም አማኞች አልነበሩም። አፍሪካ ከደረሱ በኋላ ከሦስቱ ሰዎች ሁለቱ ሞቱ። ነገር ግን ራእያቸው ባለመሞቱ፣ ዛሬ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አማኞች የሚገኙባቸው በሺዎች የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ሊመሠረቱ ችለዋል።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ ታላቅ ራእይ ያላቸውንና እግዚአብሔር በከፍተኛ ደ ረጃ የሚጠቀምባቸውን ኢትዮጵያውያን ስም ዘርዝር። ለ) ለሕይወትህ ምን ራእይ አለህ? ይህን ጥያቄ መመለስ ከከበደህ፣ አሁኑኑ ጊዜ ውሰድና እግዚአብሔር ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ ራእይ እንዲሰጥህ ጸልይ። |

ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የአገልግሎት ራእይን የሚሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ ነው ብለው እንዳያስቡ ማስጠንቀቂያ ሊሆናቸው ይገባል። ይልቁንም፣

ምእመናን እግዚአብሔር የሚናገራቸውን ነገር ለምተው በእምነት ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ ማበረታታት አለብን:: እንደ መሪዎች የግለሰቦችን ራእይ በመምራትና ከፍተኛ ውጤት ይኖረው ዘንድ በመሞረድ ልናግዛቸው ይገባል:: እግዚአብሔር ለግለሰቦች የሚሰጠውን ራእይ ለማዳፈን መጣር ግን የለብንም:: ቢሮክራሲያዊ አሠራራችን ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምተው ተግባራዊ እርምጃ እንዳይወስዱ ነጻነታቸውን እንዲገድብ ማድረግ የለብንም::

ሁለት ሴቶች ወንጌሉን ለማዳረስ የወጠኑት ራእይ ቀደም ሲል ሴትኛ አዳሪዎች የነበሩ ብዙ ወጣት ሴቶች ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ያደረገበትን ሁኔታ ተመልክቻለሁ:: እንዲሁም እግዚአብሔር ሁለት ወንዶች ለስፖርት የነበራቸውን ፍቅር ተጠቅመው የማያምኑ ወጣቶችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አገልግሎቶችን እንዲጀምሩ ራእይ ሰጥቷቸዋል:: ወንጌልን የሚቃወሙ ሰዎች ባሉባቸው አካባቢዎች እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ራእይ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት እንዲመሠረቱ አድርጓል:: ሌላው ግለሰብ ደግሞ ምንም እማኝ በሌለበት ሩቅ ስፍራ የሚገኝ አንድ ጎሳ በወንጌል እንዲደርስ ሸክም ተሰጥቶት ነበር:: ከፍተኛ ግላዊና ቤተሰባዊ ዋጋ ከፍሎ ወደዚያ ከሄደ በኋላ ዛሬ በሺዎች የሚቆጠሩ አማኞችን ሲያፈራ ችሏል:: እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ራእይ ሲሰጥ፣ እና ግለሰቡም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራእዩን እውን ለማድረግ ሲጥር፣ ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮች ይከናወናሉ::

በሌላ በኩል፣ ኮሚቴዎች አንድን ነገር ለማከናወን ዕቅድ ያወጡበትን ሁኔታ ተመልክቻለሁ:: ነገር ግን ለራእዩ ራሱን የሚሰጥ ሰው ስላልነበረ፣ ሥራው የተሠራው ለአንድ ሰው ጥሩ ደመወዝ እስከ ተከፈለው ድረስ ብቻ ነበር:: ሰዎች የግል ራእይ ከሌላቸው፣ የተሻለ ደመወዝ የሚያስገኝ ሌላ ሥራ ወይም የትምህርት ዕድል ካገኙ ጥለውት ይሄዳሉ:: እግዚአብሔር ለሚሠራው ነገር አንድ ሰው የግል ራእይ ከሌለው፣ በግማሽ ልቡ



ወደ መሥራቱ ያዘነብላል:: እንደዚሁም ራእይ ያላቸው ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልግሎቱን ሥራ እስቺጋሪ ስላደረጉባቸው ተስፋ ቆርጠው ሲተዉት አይቻለሁ::

ስለሆነም፣ እግዚአብሔር የሚሠራበትን መንገድ ማክበሩ ለሁላችንም አስፈላጊ ነገር ነው:: ወጣቶቻችን እግዚአብሔርን ለማገልገል ታላላቅ ሕልሞችን እንዲያልሙ፣ እና እነዚያንም ሕልሞች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማበረታታት አለብን:: እንዲሁም ደግሞ በዓበይት የአገልግሎት ስፍራዎች ላይ የሚቀመጡ ሰዎች የሚመረጡት በትምህርታቸው፣ ወይም ሥራ ለመያዝ ባላቸው ፍላጎት ሳይሆን፣ በዚያ አገልግሎት በኩል እግዚአብሔር እንዴት ሊጠቀምባቸው እንደሚችል ባላቸው ራእይ መሆን አለበት:: ይህ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያናችንንና አገራችንን ለእግዚአብሔር ክብር ለመለወጥ የምንችልበት ትልቅ እቅም ይፈጠራል::

> **27ኛ** ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ለአንድ ሰው የሰጠው ራእይ እንዴት ታላቅ ውጤት በማምጣት ስሙን እንዳስከበረ ግለጽ:: ለ) እግዚአብሔር ለአንድ ሰው የሰጠውን ራእይ መንግሥት ወይም ሽማግሌዎች እንዴት ሲያደናቅፉ ወይም ሲወስኑ እንደ ተመለከትክ ግለጽ:: ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ግላዊ ራእይ በማይኖራቸው ጊዜ ምን እንደሚከሰት ግለጽ:: ራእይ የሌላቸው ሰዎች ለአንድ አገልግሎት ጠንክረው ለመሥራት የሚቸገሩት እንዴት ነው? መ) እግዚአብሔር ለክብሩ እንዲጠቀምብህ ምን ራእይ አለህ? ሠ) ያንን ራእይ ወደ ተግባር ለመለወጥ ምን እያደረግክ ነው? ረ) እግዚአብሔርን ለማገልገል ራእይ ከሌለህ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ጸልይ:: እግዚአብሔር ለክብሩና ለሕዝቡ ጥቅም እንዴት ሊጠቀምብህ እንደሚፈልግ ጠይቀው::

## 5. ጥርት ያለ ራእይ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጤንነት አስፈላጊ ነው::

«ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል» የሚል የአማርኛ ዘይቤያዊ አነጋገር አለ:: ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድን ሥራ ከመጀመራችን በፊት በጥንቃቄ ለማቀድ ጊዜ አንሰጥም:: ይልቁንም፣ ስለምናከናውነው ተግባር ለማሰብ የመጨረሻዋን ደቂቃ

እንጠብቃለን። በዚህ ጊዜ አስፈላጊ የሆኑትን ሳይሆን ድንገተኛ የሆኑትን ነገሮች ለማከናወን እንገደዳለን። በፍጥነት አስቸኳይ ነገሮችን በምናከናውንበት ጊዜ በአብዛኛው ጥሩ ውሳኔዎችን አናስተ ሳልፍም። ምን ልናደርግ እንደምንፈልግ ስለማናውቅና ቀደም ብለን ዕቅድ ስለማናወጣ፣ ለማሳካት የምንፈልጋቸውን ነገሮች አናሳካም፣ ወይም ገንዘብ እናባክናለን፣ ወይም ደግሞ ጥራት ያለው አገልግሎት አንሰጥም።

ሁሉንም ምእመናን የሚያሳትፍ ራእይ አስፈላጊ የሚሆነው እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ታላቅ ሥራ እንዲሠራ ብቻ ሳይሆን፣ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጤንነት ጭምር ነው። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግልጽ ራእይ በማይኖርበት ጊዜ የሚከተሉት ነገሮች ይከሰታሉ።

ሀ. ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ራእይ በግልጽ በማይረዱበት ጊዜ፣ በመንፈሳዊ ብስለት ሊያድጉ ወይም ውጤታማ አገልግሎት ሊያበረክቱ አይችሉም።

ልናከናውን ስለምንፈልገው ነገር ጥሩ ግንዛቤ ማግኘት (ግልጽ ራእይ) አንድ ግለሰብ ወይም መሪ ሊኖረው የሚገባው ወሳኝ የአመራር ክህሎት ነው። ይህ የጥሩ አመራር መጀመሪያ ነው። መሪዎች ጥሩ ዕቅድ ሊነድፉ የሚችሉት ለእግዚአብሔር ክብር ምን ሊያደርጉ እንደሚፈልጉ በትክክል ከተገነዘቡ በኋላ ብቻ ነው። ለማከናወን የምንፈልገው ነገር ግልጽ ካልሆነ፣ የምናደርገው ነገር የሚገባውን ያህል ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ሕንጻን እንደ መሥራትና ኮንፈረንስ እንደ ማዘጋጀት ካሉት ቀላል ነገሮች አንሥቶ ቤተ ክርስቲያን እምቅ ኃይሏን ተጠቅማ ውጤት እንድታስመዘግብ ማስቻል ዓይነት ውስብስብ የአመራር ጉዳዮችን ተግባራዊ ለማድረግ እውን ለማድረግ ስለምንፈልገው ነገር ግልጽ ራእይ ሊኖረን ይገባል። መሪዎች በመጨረሻው ላይ እንዲመጣ የሚፈልጉትን ውጤት በማሰላሰል ብዙ ጊዜ ካሳለፉ፣ የሚገኘው ውጤት ያማረ ይሆናል። ሰዎች፣ በተለይም መሪዎች



እንዲከናወን ስለሚፈለገው ነገር ግልጽና የተቀናጀ ግንዛቤ ከሌ ላቸው ብዙ ነገሮች ይከሰታሉ፦

1) ግልጽ ራእይ በማይኖርበት ጊዜ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሊሠራ የሚፈልገውን ነገር እንገድባለን። እግዚአብሔር የሚሠራው በእርሱ ላይ ባለን እምነትና በእኛ በኩል በሚያከናውነው ተግባር ላይ ባለን የተሳትፎ ደረጃ ነው። እግዚአብሔር በእኛ በኩል ለሚሠራው ነገር ትልቅ ራእይ ካለን፣ እግዚአብሔር ይህንን በማክበር ከምናስበው የበለጠ ሥራ ይሠራል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእኛ ለሚፈልገው ነገር ምንም ወይም ትንሽ ራአይ ካለን፣ ለእግዚአብሔር የምንሠራውም ያንኑ ያህል ነው። በማኅበረሰባችንም ሆነ በአገራችን ትልቅ ልዩነት ልናመጣ አንችልም። እንደ መሪዎች እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ለማወቅ ጊዜ የሚያጥረን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ራእዩን አይገልጥልንም። ኤልያስ እንደ ተገነዘበው፣ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ፈቃዱን የሚገልጸው በታላቅ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ ወይም በጸሎት ስብሰባዎች ሳይሆን፣ መሪዎች በጸጥታ ፈቃዱን በሚፈልጉበት ጊዜ ነው (1ኛ ነገሥ. 19:11-13)። መሪዎች አስተ ዳደራዊ ዝርዝር ጉዳዮችን በማስፈጸም ራሳቸውን ለጥድፊያ ከዳረጉ ወይም ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቧ እግዚአብሔር የወጠነላትን ራአይ ለማወቅ በዝግታ ድምጹን ለመስማት ካልቻሉ፣ ራእዩ ከቤተ ክርስቲያን ተሰውሮ ይቆያል። የመዘምራን ልብስ በመግዛት ወይም የተጣሉ አማኞችን በማስታረቅ ሥራ ስለሚበዛባቸው ወንጌሉን ለማኅበረሰቡ ለማምጣት ስለሚችሉበት መንገድ ለመጸለይ ጊዜ የሚያጥራቸው መሪዎች ስንቶች ናቸው? እግዚአብሔር ለእኛና ለቤተ ክርስቲያናችን ያለው ራእይ ካልታወቀ፣ ምአመኖቻችን እግዚአብሔር በሚፈልጋቸው እጅግ ጠቃሚ ሥራዎች ላይ ሊሳተ ፉ አይችሉም።

2) ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ጥልቅ ዕቅዶች ልትወጥን አትችልም። በሚገባ የተቀናጀ ዕቅድ የሚመጣው ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን የምንፈልገውን ነገር

ከማወቅ ነው። እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ካላወቅን፣ አገልግሎታችንን እንዴት ማከናወን እንዳለብን ማወቁ አስቸጋሪ ነው። ገንዘባችንን ለአዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መስጠት፣ ሌላ ወንጌላዊ መቅጠር፣ ወይስ ለወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮግራም መጀመር እንዳለብን ለማወቅ እንቸገራለን። የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋንኛ ግብ ምን እንደ ሆነ ካላወቅን፣ የትኛውን ተግባር ማከናወን እንዳለብን እንዴት እናውቃለን? ከእነዚህ አገልግሎቶች መካከል የእግዚአብሔር ታላቁ ዓላማ ለሆነው ነገር ሀብታችንን የምናውልበትን አገልግሎት እንድንመርጥ የሚያስችለን ግልጽ ራእይ ብቻ ነው። በተጨማሪም፣ ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በአንድ ግልጽ ግብ ማስተሳሰሩ ከባድ ይሆናል። ሁላችንም አንድ ላቅ ያለ ራእይ ከሌለን፣ አንደኛው መሪ ገንዘባችንን ለሙዚቃ መሣሪያ መግዣ እንድናውል ሲከራከር፣ ሌላኛው ደግሞ መጋቢ መቀጠር አለበት ሊል ይችላል። ሁሉንም ሰው የሚያሳትፍ የተቀናጀ ራእይ ከሌለ፣ በመሪዎችም ሆነ በምእመናን መካከል ክፍፍል ሊፈጠር ይችላል።

3) ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ ምእመናን ሕይወታቸውን ለምን ጉዳይ አሳልፈው እንደሚሰጡ ሊገነዘቡ አይችሉም። ሰዎች ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚሰጡት አስፈላጊ ነው ብለው ለሚያምኑት ነገር ነው። ሽማግሌዎች ራእዩ ለራሳቸው ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለምእመናን ለማብራራት አይቸገሩም። ነገር ግን ምእመናን ለቤተ ክርስቲያኒቱ የእግዚአብሔር ራእይ ምን እንደ ሆነ በትክክል ካላወቁ፣ ለአገልግሎቱ ራሳቸውን በሙሉ ልባቸው ሊሰጡ አይችሉም። ለእግዚአብሔር በሚከናወነው ታላቅ ሥራ ውስጥ በመሳተፋቸው ደስ ሊሰኙ አይችሉም። ነገር ግን፣ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ምንም ተግባር የማያከናውኑ ዳተኞች ይሆናሉ።

4) ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ይዋዥቃል። እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ውስጥ ደስታንና መንፈሳዊ ዕድገትን ለመፍጠር ራእይን ይጠቀማል። የቤተ



ክርስቲያን አባላት እሑድ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎቱ መሳተፍ አለባቸው። በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ እንዲችሉ እግዚአብሔር ለአገራቸውና ለማኅበረሰባቸው ባለው ራእይ ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። ትኩረታቸውን የሚያሳርፉበትን ግልጽ ራእይ ያሳወቁ ምእመናን ጉልበታቸውን ለራስ ወዳድ ዓላማዎች ያውላሉ። በለጋሽነት ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ወደ ቁሳዊ ምኞት ፊታቸውን ያዞራሉ። እንዲሁ የሌላውን ድክመት በማጉላት ክርክርና ሐሜት ይጀመራል። ከዚህም የተነሣ፣ በወጣቱና በአዋቂዎች፣ ወይም በተለያዩ ጎሳዎች፣ ወይም በመሪዎች መካከል ክፍፍል ይከሰታል። የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማጠናከር ቁልፍ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ለጋራ ራእይ መሥራት ነው (1ኛ ቆሮ. 1:10፤ ፊልጵ. 2:2)።

5) ያለ ግልጽ ራእይ፣ የሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ ጉልበትና ገንዘብ በብቃት ከጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም። ለማሳካት የምንፈልገውን ነገር ስናውቅ፣ ራእዩን እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ሥራዎች የሚዘረዝሩ ጥሩ ዕቅዶች ልናዘጋጅ እንችላለን። መሠራት ያለበትን ነገር በትክክል ስናውቅ፣ ሥራው በፍጥነት ይቋጭ ዘንድ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ለተለያዩ ሰዎች ልንሰጥ እንችላለን። በዚህም ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን መጠቀም ይጀምራሉ። ራእዩን እውን በማድረጉ ረገድ አገልግሎታቸው የሚጫወተውን ክፍል ስለሚያውቁ፣ ተግተው ይሠራሉ። ራእዩን ሳያውቁ አንድ ሥራ ብቻ እንዲያከናውኑ ቢጠየቁ፣ ያን ያህል ላይተጉ ይችላሉ። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ስለምናውቅ፣ ሕዝቡ አስፈላጊነቱ ለታመነበት ሥራ ገንዘቡን እንዲሰጥ ልናደፋፍር እንችላለን። ምእመናንም ገንዘባቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት በአግባቡ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ስለሚያውቁ፣ መሪዎቻቸውን በማመን የእግዚአብሔርን ራእይ ለመደገፍ ሲሉ ገንዘባቸውን ይሰጣሉ። ስ

ዎች ገንዘባቸው በከንቱ እየባከ ሳይሆን በአግባቡ ለትክክለኛ ዓላማ እየዋለ መሆኑን ሲያውቁ፣ በልግስና ይሰጣሉ::

6) ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚጋፈጧቸው ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ:: መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለማስተካከል እየተሯሯጡ ዳሩ ግን ወንጌሉን ለማስራጨት ጠቃሚ የሆኑትን ሥራዎች ላይሠሩ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ:: የታመሙትን በመጠየቅ፣ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የሞቱትን ሰዎች የቀብር ሥነ-ሥርዓት በማስፈጸም፣ በሌሎች ቤተ እምነቶች የተወሰዱባቸውን አባላት ለማስመለስ በመጣር ይባክናሉ:: እነዚህን አስቸኳይ ጉዳዮች ለማሳካት ሲሯሯጡ፣ ቤተ ክርስቲያናቸው በመንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ ወይም በማኅበረሰቡና በአገሪቱ ውስጥ ወንጌል ያልደረሳቸው ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ለማገዝ እምብዛም ጥረቶች ሳይታዩ ይቀራሉ:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ራእይ ለመፈጸም ወስነው አመራር መስጠት ሲገባቸው፣ ራሳቸውንና ጊዜያቸውን ለሁኔታዎች ያስገዛሉ:: ብዙውን ጊዜ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ዘላቂ ውጤት በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ በሚቀርቡላቸው ችግሮች ይወጠራሉ:: ይህም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ለማከናወን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበብ ነገሮችን የምንቆጣጠር መሪዎች ሳንሆን፣ የሁኔታዎች ወይም የሰዎች አስቸኳይ ጥያቄዎች ባሪያዎች እንድንሆን ያደርገናል:: በእምነት ዕቅድ ካወጣን በኋላ፣ ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ነገሮችን እግዚአብሔር እንድናከናውን ወደሚፈልገው ተግባር መምራት አለብን::

> 28ኛ ጥያቄ:- ግልጽ ራእይ ወይም ዕቅድ በማይኖርበት ጊዜ ይህ ችግር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲከሰት የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ::

ሰ. በራእዩ ላይ ግልጽ መረዳት ከሌለ፣ መሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ለመስማማት ይቸገራሉ::



ለመሪዎች ራእዩን ወይም ግቡን መረዳታቸው አስፈላጊ ነው:: ሁሉም ራእዩን ካልተረዱና ካልተስማሙበት፣ አያሌ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ:-

1) ሁሉም መሪዎች በራእዩ ካልተስማሙ፣ ራእዩ እውን እንዲሆን ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ላይሰጡ ይችላሉ:: መሪዎች ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚሰጡት አስፈላጊ ነው ብለው ለሚያምኑት ነገር ብቻ ነው:: እግዚእብሔር በሰጣቸው ራእይ ካመኑ፣ ሁሉም መሪዎች ከልባቸው፣ «ይህ አስፈላጊ ስለሆነ ለተግባራዊነቱ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ» ይላሉ::

2) መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ባለው ራእይ ላይ በአንድ ልብ ካልተስማሙ፣ በሚደረጉት ነገሮች ላይ ያለመስማማት ሊፈጠር ይችላል:: በአመራር ውስጥ ውጥረቶች ከሚፈጠሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ሽማግሌዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንነት ላይ እኩል ግንዛቤ ወይም ስምምነት ላይኖራቸው መቻሉ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ዋንኛ ራእይ ላይ ስምምነት ከሌለ፣ የተለያዩ መሪዎች በወንጌል ስርጭት፣ ወይም በማስተማር ወይም በልማት ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ:: እያንዳንዱ አገልጋይ የራሱ አገልግሎት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ እንደ ሆነ በማሰብ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል ይገፋፋል:: ነገር ግን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንድ ራእይ ላይ ከተስማሙ፣ አንድ ሰው ከዚህ ራእይ ጋር የማይሄድ አሳብ ቢያነሣ፣ ሌሎቹ እግዚአብሔር በሰጣቸው ራእይ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ በገርነት ያስታውሱታል::

3) መሪዎች በአንድ ራእይ ቀዳሚነት ላይ ካልተስማሙ፣ የትኞቹ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆኑ ለመወሰን ይቸገራሉ:: አንዱ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚወስድ ውሳኔ ይሰጣል:: ሌላው ደግሞ ምእመናን ሌላ መስመር እንዲከተሉ ያበረታታቸዋል:: ወይም ደግሞ ምእመናን አንድ አሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ መሪዎች አሳቡን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በመመዘኛነት የሚጠቀሙት ነገር አይኖራቸውም::

ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ነገሮች መወሰን የሚቻለው ቤተ ክርስቲያኒቱ ትኩረት የምትሰጣቸው ነገሮች ምን ምን እንደ ሆኑ የወሰንን እንደ ሆነ ብቻ ነው:: በዚህ ጊዜ ከብዙ መልካም አገልግሎቶች መካከል የትኞቹን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን እናውቃለን::

> 29ኛ ጥያቄ:- ሀ) የተሰያዩ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በአሳብ አንድ ተለያዩባቸው የሰማሃቸውን ነገሮች አስብ:: አብዛኞቹ አለመስማማቶች የተፈጠሩት ሁሉም የተስማሙበት የጋራ ራእይ ባለመኖሩ ነበርን? መልስህን አብራራ:: ለ) ሁሉም መሪዎች ሰቤተ ክርስቲያናቸው አንድ ዓይነት ራእይ ቢኖራቸው፣ ይህ በሽማግሌዎች የቦርድ ስብሰባ ላይ ውይይቶች የሚካሄዱበትን ሁኔታ እንዴት የሚሰውጥ ይመስልሃል?

### አራተኛ ቀን

## እግዚአብሔር ሁሉም አማኞች እንዲያደርጉና እንዲሆኑ የሚፈልገውን ራእይ እንዲያውቁ ይሻል::

ሁላችንም ለሕይወታችን «ራእይ» ያስፈልገናል:: ይህም ራእይ ልንሆንና ለእግዚአብሔር ልናደርግ የምንፈልገው ነገር ነው:: ለሕይወት ዓላማና ትርጉም የሚሰጠው ራእይ ያለው ሕይወት መምራትና ያንኑ ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ መጣር ነው:: ለሕይወታችን አብዛኛው የእግዚአብሔር ፈቃድ (ዕቅድ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአጠቃሳይ ትምህርት የተገለጸ ሲሆን፣ ለሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች የሚሠራ ነው:: ለምሳሌ፣ መቀደሳችን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ተገልጾአል:: (1ኛ ተሰ. 4:3ን አንብብ::) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን መምሰልና እንዴት መኖር እንዳለብን የሚናገር አጠቃላይ ትምህርት ሁሉ ለሕይወታችን የእግዚአብሔር አጠቃሳይ ራእይ ነው::

> 30ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሕይወትህ የእግዚአብሔር ፈቃድ (ዕቅድ) ሆነው የተገለጹትን 10 ነገሮች ዘርዝር:: (ለምሳሌ፣ መስቀልህን መሸከም፣ ቅድስና፣ ወዘተ . . . ) ለ) ከእነዚህ መካከል የትኞቹን ተግባራዊ እያደረግክ ነው? በአሁኑ ሰዓት በሕይወትህ ተግባራዊ የማታደርጋቸው የትኞቹ ናቸው?



ነገር ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችንም ግልጽ ዕቅድ አለው:: በመዝ. (139):13-16 እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በጥንቃቄ በእናታችን ማህጸን ውስጥ እንደ ሠራን እናነብባለን:: እርሱ ልዩ ማንነታችንንና ችሎታችንን ይሰጠናል:: ጳውሎስ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነልንን መልካም ሥራ ለመሥራት የተፈጠርንና ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ መሆናችንን ይናገራል:: (ኤፌ. 2:10 አንብብ::) ይህም እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ልዩ ዕቅድ እንዳለው ያሳያል:: ሕይወታችንን ከፈቃዱ ጋር በማስተሳሰር ለእግዚአብሔር በምናከናውነው ተግባር ውጤታማ እንሆን ዘንድ ለእኛ የወጠነው ልዩ ዕቅድ ምን እንደ ሆነ ማወቅ ይኖርብናል::

እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ውስጥ እርሱን እንዴት እንደምናገለግል የሚያሳይ ፍላጎት ወይም ሸክም ያኖራል:: እንድ አማኝ ማኅበረሰቡ ያገለላቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ለምጻሞች በማየቱ ለምጽን ለማጥፋትና በዚሁ በሽታ የተያዙ ሰዎች እገዛ የሚያገኙበትን መንገድ ሲፈልግ ሕይወቱን በሙሉ ለዚሁ አገልግሎት ሠውቷል:: ሌላው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሲራቡ በመመልከቱ ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ወርልድ ቪዥንን መሥርቷል:: ሌላው ደግሞ በሕንድ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የወንጌል ምስክርነት አለመካሄዱን በመመልከቱ ሚሲዮናዊ ሆነ:: ይህ ሚሲዮናዊ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ለማንበብ እንዲችሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተርጉሟል:: እነዚህ እግዚአብሔር ለግለሰቦች ራእይ መስጠቱን ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች ጥቂቶቹ ናቸው:: እንዲያውም፣ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርገው መጀመሪያ ለአንድ ግለሰብ ራእይ በመስጠት ነው:: ታላቅን ነገር ለማድረግ ራእዩን ለኮሚቴ የሚሰጥባቸው ብዙ አጋጣሚዎች የሉም::

1. እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ በዓለም ውስጥ እርሱን እንዲያገለግል የሚያደርግበት ልዩ መንገድ አለው::

እግዚአብሔር ጥቂት ሰዎች እንደ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ሆነው በሙሉ ጊዜ እንዲያገለግሉት ራእይ ይሰጣቸዋል:: ለአብዛኞቹ ያለው የእግዚአብሔር ራእይ ግን እንደ ገበሬዎች፣

አስተማሪዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች ወይም ነጋዴዎች እንዲሠሩ ነው። የሙሉ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ባንሆን እንኳን፣ እግዚአብሔር በምንሠራባቸው ቦታዎች ሁሉ እንድናገለግለው እንደ ጠራን መረዳት አለብን። የአንደኛ ደረጃ መምህራን ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ራእይ ገቢ እንድናገኝ ብቻ ላይሆን፣ በምናስተምራቸው ልጆች ሕይወት ላይ ለውጥ እንድናመጣ ጭምር ነው። የለውጥ ተጽዕኖ የምናሳድርባቸው ደግሞ ልጆቹ የምናስተምረውን ትምህርት በሚገባ እንዲረዱ የምናግዛቸው ግሩም አስተማሪዎች በመሆን ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ደግሞ ጥሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ በመርዳትም ሊሆን ይችላል። የሚቻል ሲሆን ደግሞ፣ በክርስቶስ እንዲያምኑ በማድረግ መልካም ተጽዕኖ ልናሳድርባቸው እንችላለን። «አገልግሎታችን» የምናስተምርበት ክፍል ነው። የመንግሥት ሠራተኞች ብንሆን፣ እግዚአብሔር በዚያ እንድናገለግለው ጠርቶናል ማለት ነው። ሥራችንን በታማኝነትና በእውነተኛነት ጥሩ አድርገን በመሥራት «እናገለግለዋለን»። ባልደረቦቻችን ወደ ኢየሱስ የማዳን እውቀት ይመጡ ዘንድ በፍቅር እንቀርባቸዋለን፤ ርዳታችንን የሚፈልጉትን ሁሉ እናገለግላቸዋለን። ምክንያቱም ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድታድግና እንድትለወጥ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማድረግ ስለምንፈልግ ነው። በአገሪቱ ውስጥ ጽድቅ የሚያብብባቸውን መንገዶች እንፈልጋለን። ገበሬዎች ከሆንን፣ እግዚአብሔር ምርጥ ገበሬዎች እንድንሆንለት ይፈልጋል። ለቤተ ለባችንና ለአገራችን ምግብ ለማምረት ተግተን እንሠራለን። እግዚአብሔር በኃላፊነት እንድንከባከብ የሰጠንን አካባቢ በእግባቡ እንይዛለን። (ዘፍጥ. 1:28፤ 2:15ን አንብብ።) በማኅበረሰባችን ውስጥ የሰዎችን ችግሮች በመቅረፍ እንረዳቸዋለን። በተለይም ስለ ክርስቶስ እንነገራቸዋለን። ስብከት ለመስማት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማይመጡ ጎረቤቶቻችን ጋር ስለ ክርስቶስ የመነጋገር ዕድል ይኖረናል።

እነዚህ ሁሉ ተግባራት ከእግዚአብሔር የተሰጡን ሲሆኑ፣ እርሱን የምናገለግልባቸው ልዩ ዕድሎች ናቸው። በአጋጣሚ ያገኘ ነው ነገር የለም። የተወለድንበት አገር፣ የትምህርት ዕድሎቻችን፣



ያገኘነው ሥልጠና ወይም ሥራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። እነዚህ እግዚአብሔር እርሱንና ሌሎች ሰዎችን ለማገልገል እንድንችል የሰጠን ልዩ ዕድሎች ናቸው። በልባችን፣ «እርሱን እንዳገለግለው እግዚአብሔር የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ቢያደርገኝ ደስ ይለኝ ነበር፤» ማለት አያስፈልግም። እግዚአብሔር በግልጽ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ እንድንሆን ካልተናገረን፣ ባስንበት በየትኛውም ስፍራ እንድናገለግለው መፍቀዱን መረዳት አለብን። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 7:17-24 እንደ ተናገረው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ወደ መዳን ባመጣን ጊዜ በነበርንበት ሆነን እርሱን ማገልገል ይኖርብናል።

2. እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ለእያንዳንዱ አማኝ ልዩ አገልግሎት አለው።

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን እርሱን እንድናገለግል ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሰጥቶናል። ከመንፈስ ቅዱስ የምንቀበለው ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን እርሱን እንድናገለግል በማቀድ የሰጠን ነው። ሮሜ 12:1-8 እንደሚለው፣ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስንሰጥ (ሕያው መሥዋዕት መሆን ማለት ይኸው ማለት ነው)፣ እና መንፈስ ቅዱስ አስተሳሰባችንን እንድንለውጥ እንዲያደርግ ስንፈቅድ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ግልጽ ፈቃድ እናውቃለን። እርሱ የሰጠንን ስጦታዎች በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርንና ሕዝቡን እናገለግላለን። ይህን እያደረግክ ነው? እግዚአብሔር እርሱን ለማገልገል ሕይወትህን እንዴት እንድትጠቀም እንደሚፈልግ ታውቃለህ?

31ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢትዮጵያ በማኅበረሰብህ ውስጥና በዓለም ለውጥ ለማምጣት እግዚአብሔር እንድታከናውን የሰጠህ ልዩ ራእይ ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሕይወትህ እውን ለማድረግ ምን እያደ ረግክ እንደ ሆነ አብራራ። ለ) በቤተ ክርስቲያን ለውጥ ለማምጣት እግዚአብሔር የሰጠህ ልዩ መንፈሳዊ ስወታ ምንድን ነው? ሐ) በሥራህ አካባቢና መንፈሳዊ ስጦታህን በመጠቀም እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ የምታገለግልባቸው መንገዶች ምን ምንድን ናቸው?

## እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንዲያደርጉ ስለሚፈልገው ነገር ግልጽ ራእይ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል

1. እግዚአብሔር ለእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ራእይና ልዩ ራእይ አለው።

ግለሰባዊ ዓላማችንን ወይም ራእያችንን ማወቅ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ያለውን ልዩ ዓላማ ማወቅ የበለጠ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንም እርሱን የምታገለግልበትን ራእይ ይሰጣል። ይህ ራእይ አጠቃላይና ልዩ ነው። አጠቃላይ ራእይ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔርን እንዲያስከብሩበት ነው። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ለእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ራእይ አለው። እርሱ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥና በዓለም ልዩ ሚና እንድትጫወት ይጠራል።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዲኖሩ አጠቃላይ እውነቶችን ይገልጻል። እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያኒቱ የሚጠበቀውን ነገር ለማወቅ የምንችልበት ከእግዚአብሔር የሆነ መሠረታዊ ዕቅድ (ራእይ) እንዲኖረን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን አጠቃላይ እውነቶች ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት እንድታካሂድና ሰዎች የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ እንድታስተምር ያዝዛል። (ማቴ. 28:19-20ን አንብብ።) ስለሆነም፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ሳልዳኑት መመስከርና አማኞች እውነተኛ የኢየሱስ ተከታዮች እንዲሆኑ ማስተማር አለባት። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በቅድስናና በጽድቅ በመመላለስ በዓለም ውስጥ ብርሃን መሆን እንዳለባቸው ያስረዳሉ (ማቴ. 5:14-16፤ ፊልጵ. 1:9-11)።

ሁሉም መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ማጥናት ካለባቸው ምክንያቶች አንዱ እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያኖቻችን



እንዲያደርጉ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማወቅ እንድንችል ነው። የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና ወንጌላውያን እግዚአብሔር ከሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ስለሚፈልጋቸው ነገሮች በቃሉ ውስጥ የገለጣቸውን እውነቶች የማወቅ ኃላፊነት አለባቸው። እግዚአብሔር ከሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሚፈልጋቸውን ነገሮች ካላወቅን፣ ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ፈቃዱን ልንፈጽም አንችልም። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአጠቃላይ የገለጣቸውን ነገሮች ካልታዘዝን፣ ልዩ ፈቃዱን አይገልጥልንም። መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ፈቃድ ለማወቅ ሁልጊዜም፣ «እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምን ማድረግ እንዳለብን የተናገረው ነገር ምንድን ነው?» ብለው መጠየቅ አለባቸው።

ለ. እግዚአብሔር በማኅበረሰባችን ውስጥ እርሱን እንዴት እንደምናገለግል የሚያሳይ ልዩ ራእይ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ይሰጣል። ምንም እንኳን ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሊያደርጓቸው የሚገቡ አጠቃላይ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው ቢገኙም፣ እነዚህን አገልግሎቶች ተግባራዊ የምናደርግበት መንገድ ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንና ከቤተ እምነት ቤተ እምነት ይለያያል። እግዚአብሔር ሁሉም ዛፎች አንድ ዓይነት እንዲሆኑ አድርጎ እንዳልፈጠራቸው ሁሉ፣ ሁሉም ቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓይነት እንዲሆን አይጠብቅም። እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ነች። እግዚአብሔርም ለእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ራእይ አለው። እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርንና ሕዝቧን የምታገለግልባቸው ልዩ ስጦታዎች አሏት። እንደዚሁም ምንም እንኳን ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የወንጌል ስርጭት ማካሄድ ቢኖርባቸውም፣ እግዚአብሔር ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው የጠነከረ የወንጌል ስርጭት ራእይ የሚሰጥ ይመስላል። ሌላው ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ድሆች፣ ወጣቶች፣ ሴተኛ አዳሪዎች ወይም የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችን የማገልገል ጠንካራ ራእይ ሊኖረው፣ ሌላው ደግሞ ሌሎች ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ሰዎችን የመድረስ ራእይ ሊኖራቸው ይችላል። እግዚአብሔር አንዱ

ቤተ ክርስቲያን ሌላውን እንዲኮርጅ ወይም አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርሳቸው በመፎካከር የበላይነትና የበታችነት ስሜት እንዲያድርባቸው አይፈልግም:: ይልቁንም፣ እግዚአብሔር ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየ ራእይ ስለ ሰጠን፣ ለእነርሱም እንደዚሁ በጣም አስፈላጊ ራእይ ስላሰው ደስ ሊሰን ይገባል:: በሰርግ ሥነ-ሥርዓት ላይ የምንጠቀምባቸው የተለያዩ አበቦች ውበትን እንደሚያሳዩ ሁሉ፣ በተለያዩ ነገሮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የተለያዩ ቤተ እምነቶችም በሰላምና በፍቅር አብረው ከሠሩ፣ ለዓለም የእግዚአብሔርን ባሕርይና ፈቃድ የሚያሳዩ ግሩም መገለጫዎች ይሆናሉ::

የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን አብረው በመሥራት እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ልዩ ራእይ እንዲያሳያቸው በጸሎት መጠየቅ አለባቸው:: ምንም እንኳን እግዚአብሔር በሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ሊመለከቱ ቢችሉም፣ ሌላውን ቤተ ክርስቲያን ለመኮረጅ መሞከር የለባቸውም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ምን የተለየ ነገር እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ መጠየቅ ይኖርባቸዋል::

32ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ ልታደርጋቸው የሚገቧትን አጠቃላይ ነገሮች ዘርዝር:: ለ) እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችሁ በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ልታደርግ የሚፈልጋቸውንና ምናልባትም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማያደርጓቸውን ነገሮች ዘርዝር::

2. እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ልዩ ራእዩን በተለያዩ መንገዶች ይገልጻል::

መሪዎች እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ራእይ በሽማግሌዎች በኩል እንደማይገልጽ ማወቅ አለባቸው:: ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ራእዩን የሚገልጸው ለአንድ ግለሰብ ሲሆን፣ ራእዩ ከእርሱ ወደ ሽማግሌዎች ይተላለፍና ቀጥሎ ለቤተ ክርስቲያን በሙሉ ይዳረሳል:: ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ራእይን ሊሰጥና ሊያሳድግ የሚችልባቸውን አራት መንገዶች ማወቅ አለባቸው:-



ሀ. እግዚአብሔር ብዙ ራእዮችን ለግለሰብ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊሰጥና እነዚያ ራእዮች መደበኛ የቤተ ክርስቲያን ራእዮች ሳይሆኑ የግለሰቦቹ ራእዮች ሆነው እንዲቆዩ ሊፈልግ ይችላል:: ለምሳሌ ያህል፣ እግዚአብሔር አንዲት አማኝ ሴተኛ አዳሪዎችን በወንጌል እንድትደርስ የሚጠይቅ ራእይ በልቧ ያኖራል እንበል:: እርሷም በየማታው ሴተኛ አዳሪዎቹ ወደሚሠሩባቸው ቦታዎች በመሄድ ጓደኝነት ትመሠርትና ትመሰክርላቸዋለች:: ለሴተኛ አዳሪዎች ወንጌል የሚመሰክር ድርጅት እንድትመሠርት እግዚአብሔር አልጠየቃትም:: ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ አስፈላጊ አገልግሎት አስተዳደራዊ ኃላፊነት እንድትወስድ አልጠየቃትም:: ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ሴቲቱ ይህንን የግል አገልግሎቷ አድርጋ እንድትወጣ ይፈልጋል:: የጸሎት ድጋፋቸውን ለማግኘት ራእይዋን ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መናገር ያስፈልጋታል:: እነርሱም ከቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል አገልግሎቷን ለመደገፍ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ አብረዋት በመሄድ ለሴተኛ አዳሪዎቹ እንዲመሰክሩ ማስታወቂያ ሊናገሩ ይችላሉ:: ይሁንና፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዚህ አገልግሎት አስተዳደራዊ ኃላፊነት አትወስድም:: ከዚህ ይልቅ፣ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ መንገዶች ማኅበረሰባቸውን የሚያገለግሉትን ግለሰቦች ታበረታታለች፣ የግል ራእያቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉም ታግዛለች::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኞቹ አገልግሎቶች መካሄድ ያለባቸው በዚህ መንገድ ነው:: እያንዳንዱ አማኝ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ራእይ ሊሰጠው በጽሞና እንዲያዳምጥ ማበረታታት ያስፈልጋል:: ይህም የምስክርነት፣ ሰዎችን የመርዳት፣ የማስተማር፣ የጸሎት ቡድን የመመሥረት፣ ወዘተ . . . አገልግሎት ሊሆን ይችላል:: ቤተ ክርስቲያን ለሥራው የገንዘብና የአስተዳደር ኃላፊነት ካላስፈለጋት በቀር እነዚህ አገልግሎቶች የግድ በቤተ ክርስቲያን ሥር መካሄድ የለባቸውም:: ጳውሎስ እያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳለው ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 12:7-11):: የዚያ መንፈሳዊ ስጦታ አጠቃቀም የሚወሰነው በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መሆን የለበትም:: ስጦታው እንዴት ከጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት የሚወስነው የቤተ ክርስቲያን ራስ

የሆነው ክርስቶስ እንጂ ሽማግሌዎች አይደሉም። ስለሆነም ሽማግሌዎች አማኞች ጌታችንን በማዳመጥ በተስጣቸው ስጦታና ራእይ አማካኝነት እንዲያገለግሉት ማበረታታት አለባቸው።

> 33ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መደበኛ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው፣ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን እንድታውቅና እንድትደግፍ፣ አንዳንድ ፈቃደኛ የሆኑ አባላትም አገዛ እንዲሰጡ በመጠየቅ በግለሰቦች ሊከናወኑ የሚችሉትን አገልግሎቶች ዘርዝር። ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላቷ እግዚአብሔርን ለማገልገል የግል ራእዮችን እንዲፈልጉ ልታበረታታ የምትችልባቸውን መንገዶች ግለጽ።

ሰ. አንዳንድ አገልግሎቶች በግለሰቦች ይጀመሩና ከአንድ ግለሰብ አቅም በላይ እየሆኑ በመሄድ መደበኛ አገልግሎቶች ይሆናሉ። ሥራው መደበኛ አስተዳደራዊ መዋቅር ያስፈልገዋል። ግለሰቦችና ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅ፣ አገልግሎቱ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ እንዲቀጥል ሊስማሙ ይችላሉ።

ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ ልትሳተፍ ብትችልም፣ ለቤተ ክርስቲያን ለብዙ ነገሮች አስተዳደራዊ ኃላፊነት መውሰዱ ጎጂ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ትኩረቷ ሊሆኑ በማይገባቸው ነገሮች ትጠመዳለች። ለምሳሌ ያህል፣ በሐዋርያት ሥራ 6:1-6 ሐዋርያት ወንጌሉን ከመስበክ ይልቅ ድሆችን በመርዳቱ ሥራ ላይ እንዳይጠመዱ መስጋታቸውን አመልክተዋል።

እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ለአንድ አገልግሎት አስተዳደራዊ ኃላፊነት እንዲወስዱ በማይመራቸው ጊዜ፣ ያ አገልግሎት በራሱ አስተዳደራዊ መዋቅር ከቤተ ክርስቲያን ውጭ መቀጠል አለበት። ቤተ ክርስቲያን በጸሎትና ምናልባትም በገንዘብ አገልግሎቱን ልትደግፍ ትችላለች። አንዳንድ አባላት የአገልግሎቱ አስተዳደራዊ አካላት ሆነው ሊሠሩ ይችላሉ። ነገር ግን ሽማግሌዎች አገልግሎቱን አይቆጣጠሩም።

በምዕራቡ ዓለም በግለሰቦች ወይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ማበረታቻ የተጀመሩ ብዙ አገልግሎቶች አሉ። ነገር ግን



አገልግሎቶቹ አድገው ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ ሲጠይቁ፣ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና አገልግሎቶች ሲያፈነግጡ፣ እነዚህ አገልግሎቶች ያለ ቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር በራሳቸው አሠራር እንዲቀጥሉ ይደረጋል። እንደ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች፣ ድሆችን የሚያግዙ ፕሮግራሞች፣ የወጣቶች ካምፖች፣ እና ትምህርት ቤቶች (አንደኛ ደረጃ፣ ኮሌጆችና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች) ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጀመሩና በኋላ በራሳቸው የገንዘብና አስተዳደራዊ መዋቅሮች ይካሄዳሉ። አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቱ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለራሱ አደገኛ የሆነ ተግባር እያከናወነ ነው ብለው የሚያስቡት ነገር በሚኖርበት ጊዜ የማስቆም እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ። ነገር ግን ዋናው አስተዳደር ያለው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን ከአቅሟ በላይ አገልግሎቶችን በገንዘብ ለመደገፍ እንዳትቸገር ያግዛታል። በተጨማሪም ይህ መሪ ዎች ትላልቅ ድርጅቶችን በመምራቱ ሥራ ላይ ጊዜያቸውን በማዋል ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ምሪትና ለምእመናን እንክብካቤ ከማድረግ እንዳይዘናጉ ያደርጋል።

ይህ ምናልባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልትከተል የሚገባት ጥሩ ምሳሌነት ሳይሆን አይቀርም። እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም የልማት አገልግሎት ወይም ልዩ አገልግሎት (ለምሳሌ፣ የስፖርት አገልግሎት፣ መቀሀማ) በገንዘብና በአስተዳደር ለመቆጣጠር ከመሞከር ይልቅ፣ ለብቻቸው እንዲካሄዱ ብታደርግ መልካም ነው። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ አቅም አዳዲስ አገልግሎቶችን ለማስተናገድ አይችልም ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን መደበኛ ፕሮግራም አካል በመሆኑ ምክንያት አገልግሎቱ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ሥራ እንዳታከናውን እንቅፋት ሊሆንባት ይችላል። ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ እንዲሰጡ ሳይጠበቁ አገልግሎቱ በራሱ እግሮች እንዲሮጥ ማድረጉ አይሻልምን? ብቃት ያለውና ውጤታማ አመራር መስጠት ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልግሎቱን ዕድገት ቢያደናቅፉ እግዚአብሔር በኃላፊነት አይጠይቃቸውም? መሪዎች «ሁሉ አማረሽ» በመሆን ከዋናው

የወንጌል ስርጭትና ለምእመናን መንፈሳዊ እንክብካቤ ከማድረግ በመደናቀፋቸው እግዚአብሔር በኃላፊነት አያጠይቃቸውም ይሆን?

እግዚአብሔር እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም አገልግሎት እንድታካሂድ አይጠይቃትም። ገንዘብ ለማግኘት ብለን ፕሮጀክቶች መክፈታችንንም አይደግፍም። ቤተ ክርስቲያን ገቢ አስገኚ (ለትርፍ የምትሠራ) ድርጅት መሆን የለባትም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የጠራት ሌሎችን የምታገለግል ድርጅት እንድትሆን ነው። በቀዳሚነት ሌሎችን የሚረዳና ተጨማሪ ገቢ ለቤተ ክርስቲያን በማስገኘት አገሪቱን የሚያሳድግ አገልግሎት ከፈለግን፣ አመለካከታችን ራስ ወዳድ በመሆኑ እግዚአብሔር ይፈርድብናል። እግዚአብሔር አገልግሎታችንን የሚደግፈው እርሱ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ስናደርግ ብቻ ነው። ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀው ደግሞ እርሱን ማስከበር እንጂ ራስን መጥቀም አይደለም።

| |
|---|
| 34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያን ወይም በግለሰቦች ሊጀመሩና ያለ ሽማግሌዎች ቁጥጥር ለብቻቸው በጥሩ ሁኔታ ሊካሄዱ የሚችሉ አገልግሎቶችን ዘርዝር። ለ) ለብቻቸው መካሄዳቸው ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለራሳቸው ለአገልግሎቶቹ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው? |

ሐ. አንዳንድ አገልግሎቶች በግለሰቦች ይጀመሩና እግዚአብሔር ራእያቸውን የቤተ ክርስቲያን መደበኛ ራእይ አካል ያደርገዋል። እግዚአብሔር ሊሠራ ስለሚፈልገው ነገር ብዙውን ጊዜ ለግለሰቦች ራእይ እንደሚሰጥ ተመልክተናል። ግለሰቡ አገልግሎቱን ሲጀምርና እያደገ ሲሄድ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ሽማግሌዎች አገልግሎቱ ቤተ ክርስቲያን ልታከናውን የሚገባት ተግባር መሆኑን እንዲገነዘቡ ይመራቸዋል። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱን ከጀመረው ግለሰብ ጋር በመተባበር መዋዕለ ንዋያዊና አስተዳደራዊ ኃላፊነት ትወስዳለች።

(ማስታወሻ፡- ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊና የተወሰነ የገንዘብ ኃላፊነት ሳትወስድ፣ የትኛውንም ፕሮጀክት በባለቤትነት ለመያዝ መሞከሯ ጎጂ ነው። ፕሮጀክቱ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሆን ካለበት፣ ሽማግሌዎች በአግባቡ ለማስተዳደርና የገንዘብ



ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀት አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን፣ በጣም ሥራ ከሚበዛባቸው ወይም ለአገልግሎቱ ግድየለሽ ከሆኑ ሽማግሌ ዎች ጋር መሥራቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ራእይ ይገድለዋል። እግዚአብሔር ለግለሰቡ የሰጠውን ራእይ በአግባቡ እንዲያካሂዱ በኃላፊነት ይጠይቃቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በመስጠትም መሳተፍ አለባት። ይህ ካልሆነና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው ገንዘብ ሁሉ የሚመጣው ከሌላ ድርጅት ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያላወጣችበትን አገልግሎት የእኔ ነው ልትል አትችልም። ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱን ለማካሄድ ገንዘብ እየተከፈላት ነው ማለት ነው።)

እግዚአብሔር ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተመሳሳይ አገልግሎቶችን እንዲያካሂዱ አይጠይቅም። እርሱ አንድ ቤተ ክርስቲያን የራሱ የሆነ አገልግሎት እንዲያካሂድ ይመራዋል። በመሆኑም፣ እግዚአብሔር አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ትዳር ለሌላቸው እናቶች፣ ወላጅ ላጡ ልጆች ወይም የኤድስ በሽተኞች የእንክብካቤ ፕሮግራሞችን እንዲያካሂዱ ወይም ትምህርት ቤቶችን እንዲከፍቱ መርቷቸዋል። ይህም እንደ ወንጌል ስርጭት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ወይም የሰንበት ትምህርት ቤቶች የቤተ ክርስቲያን ዕቅድ አካል ሆኗል። ከበጀታቸው የተወሰነው እነዚህን ፕሮግራሞች ለማካሄድ ይውላል። እግዚአብሔር እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያካሂዱ የሚፈልግ መሆኑን ስለ ተረዱ፣ ሽማግሌዎቹ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በመጠቀም እነዚህን አገልግሎቶች ይደግፋሉ።

| |
|---|
| 35ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢትዮጵያ የግለሰብ ራእይ ሆነው የተጀመሩና ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደርና የገንዘብ ኃላፊነት በመውሰድ የራሷ ልታደርጋቸው ይገባል የምትላቸው አገልግሎቶች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ይህ አገልግሎት ለወንጌል ስርጭትና እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን ለሚጠብቀው አገልግሎት ጠቃሚ ሆኖ ያገኘህበትን ሁኔታ ግለጽ። |

መ. አንዳንድ ራእዮች እግዚአብሔር ለሽማግሌዎች ወይም ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸው ናቸው። ምንም እንኳን ከእነዚህ ራእዮች አንዳንዶቹ መጀመሪያ በሽማግሌዎች ተጀምረው በኋላ

በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች በኩል ተግባራዊ ቢደረጉም (ለምሳሌ ያህል፣ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚካሄድ ትምህርት ቤት መጀመር)፣ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ራእዮች የቤተ ክርስቲያን ሆነው ይኖራሉ። ሽማግሌዎች አገልግሎቱን ይከታተሳሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን የገንዘብና የሰው ኃይል ትመድባለች። እነዚህ በጎረቤት አካባቢ ላሉ ወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮግራም መጀመር፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በወንጌል ለመድረስ የስፖርት ፕሮግራም መጀመር፣ ወይም በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች የእሑድ የመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮግራም መጀመር የመሳሰሉት ይሆናሉ።

ለምሳሌ ያህል፣ በሐዋርያት ሥራ 13፣ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና መሪዎች በሚጸልዩበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ሽማግሌዎቹ ሁሉ በርናባስንና ጳውሎስን በወንጌል መልእክተኛነት እንዲልኩ መራቸው። ራእዩ የመነጨው እንደ ጳውሎስና በርናባስ ካሉት ግለሰቦች ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከሽማግሌዎች ነበር። ከዚያ በኋላ ግን፣ ራእዩ የጳውሎስና የበርናባስ ሆኖ ስናገኝ እንመለከታለን። ጳውሎስና በርናባስ ወዴት መሄድ እንዳለባቸውና ምን መሥራት እንዳለባቸው፣ ወዘተ. . . ሽማግሌዎቹን ሊያስፈቅዱ አንመለከትም። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስንና በርናባስን እንደሚመራቸው አርግጠኞች ነበሩ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል መልእክተኞቿ ትጸልይና ምናልባትም ገንዘብ ትሰጣቸው ነበር። ጳውሎስና በርናባስ ለቤተ ክርስቲያናቸው ተጠያቂነት እንዳለባቸው ስለሚያምኑ፣ ከጉዞአቸው በሚመለሱበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ለመመስከር ወደ አንጾኪያ ይሄዱ ነበር (የሐዋ. 14:26-27)።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሽማግሌዎች አግዚአብሔር በቀጥታ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሊሳተፉባቸው የሚገቡትን አገልግሎቶች እንዲያሳያቸው በሚጠይቁበት ጊዜ በአብዛኛው እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲጀምሩ ይመራቸዋል። እነዚህ ሽማግሌዎች ያለ ብዙ ጫና አገልግሎቱን ለመምራት የውክልናን ሂደት በአግባቡ መጠቀም አለባቸው። (ማስታወሻ:- ውክልና አንድ መሪ ለአንድ



አገልግሎት ሰው በመወከል በኃላፊነት እንዲከታተል የሚያደርግበት አሠራር ነው። ስለ ውክልና ወደ በኋላ እንማራለን።)

መንፈሳዊ መሪዎች በክህሎት ለመምራት ከፈለጉ፣ ሁልጊዜም፣ «ለዚህ አገልግሎትና ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለው ነገር ምንድን ነው? በሽማግሌዎች መመራት ነው ወይስ የራሱን አስተዳደራዊ አካል ማበጀት?» ብለን መጠየቅ አለብን። የቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር የአገልግሎቱን ውጤታማነት የሚገድብ ከሆነ፣ ሽማግሌዎች አገልግሎቱ በራሱ ወይም በክፊል ቁጥጥር የሚካሄድበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው። ወይም ደግሞ ውጤታማ የውክልና አሠራር ለመጠቀም መሞከር አለባቸው። ሁልጊዜም ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳስባት ትልቁ ጉዳይ እግዚአብሔር ለግለሰብ ወይም ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ራእይ የሳቀ ውጤት ማምጣቱ ነው። ይህ ተግባራዊ እስከ ሆነ ድረስ ማንም ቢያስተዳድረው ወይም የትኛውም ድርጅት እውቅና ቢያገኝበት አሳሳቢ አይሆንም።

36ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በቀጥታ እንድትቆጣጠር ሰጥቷታል ብለህ የምታምንባቸውን አገልግሎቶች ዘርዝር። ለ) አግዚአብሔር እነዚህ አገልግሎቶች ሰብቻቸው ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን እንዲካሄዱ የፈለገው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ሰዎች ከአንድ አገልግሎት አውቅናና ክብር መፈለጋቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት መስፋፋት እንዴት እንደሚያደናቅፍ ግለጽ። መ) ቤተ ክርስቲያን የበለጠ እውቅና ሊጨምርላት የሚችለውን ፕሮግራም ለእግዚአብሔር መንግሥት ለሚያበረክተው አስተዋጽኦ ስትል የተወችበትን ሁኔታ ግለጽ።

## ራእይ የሌለው ዕቅድ በራእይ ላይ ከተመሠረተው ዕቅድ ያለው ልዩነት

37ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች፣ አንድ ሰው ስለ አንድ አገልግሎት ራእይ አለው ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ለ) ራእይ ያለው መሪ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ሐ) ራእይ ከድርጊት ዕቅድ (መርሐ ግብር) በምን ይለያል? መ) መሪ ራእይን የሚያገኘው እንዴት ነው? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ነበረው የምታውቃቸውን «ራእዮች» ዘርዝር። የመሪው ራእዮች

በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ያስከተሏቸው ውጤቶች ምን ምን ነበሩ? ረ) ሮሜ 12:1-2ን አንብብ። ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ፈቃድ ለማወቅ ምን ማድረግ አለብን ይላል?

በዕቅድና በራእይ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቁ አስፈላጊ ነው። ራእይ ስማከናወን የምንፈልገው ነገር ግብ ወይም የመጨረሻ ውጤት ነው። የእማኞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት መሞላት የቤተ ክርስቲያን ራእይ ሊሆን ይችላል። ዕቅድ ራእዩን እውን ለማድረግ የምናደርገው ነገር ነው። ራእያችንን እውን ስማድ ረግ የሚያስፈልገን በሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ 200 አባላት መገኘታቸው ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን ተ ግባራዊ ስማድረግ ልትጠቀማቸው የምትችላቸው አያሌ ነገሮች አሉ። አባላት የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያውቁ የምንፈልግ ከሆነ፣ አባላት እንዲያውቁ በምንፈልጋቸው ነገሮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ትምህርታዊ ሰብከቶች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ስሚገኙ ስዎች የሚሰጡ የስንበት ትምህርቶች፣ ወይም እንደ መቅሀማና ትመማ ያሉ የጥናት ፕሮግራሞችን ማካሄድ ይቻላል። እነዚህ ሁሉ ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያውቁ ስማገዝ የታሰመውን ራእይ እውን ለማድረግ የሚያግዙ ናቸው።

ብዙ መሪዎች «ራእያቸውን» በደንብ ሳያውቁ ዕቅድ በማውጣት ስሕተት ይፈጽማሉ። ዕቅዳችን 3 ወንጌላውያንን መላክ ነው፣ የቤተ ክርስቲያንን ጣሪያ በቆርቆሮ ማልበስ ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም ላይ 200 ሰዎች እንዲሳተፉ ማድረግ ነው ይላሉ። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ልንፈጽማቸው የምንፈልጋቸው ጥሩና ግልጽ ተግባራት ቢሆኑም፣ ራእይ አይደሉም። እነዚህን ተ ግባራት የምናከናውነው ለምንድን ነው? ግባችን ወይም ራእያችን ምንድን ነው? ተግባሮቻችን ሲጠናቀቁ ምን ስማድረግ ነው የምንፈልገው? ራእያችን ሦስት ወንጌላውያንን መላክ አይደለም፤ እግዚአብሔር አራት ወንጌላውያን እንድንልክ ቢፈልግስ? ስለዚህ፣ ራእያችን ወንጌሉን ላልዳኑት ሰዎች ማዳረስ መሆን አለበት። ሦስት ወንጌላውያንን መላክ ራእዩን እውን ከምናደርግባቸው መንገዶች



አንዱ ነው። ራእይ ግን አይደለም። 200 ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄዳቸውም ግባችንን ለመምታት ከሚከናወኑ ተግባራት እንዱ እንጂ በራሱ ራእይ አይደለም። ራእይ ዋንኛ ግባችንን የሚያመለክት ነው። ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲያካሂዱ የምንፈልገው አባላት በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲሞሉ ስማስቻል ነው። (ቈላ. 2:6-8ን አንብብ።) ምእመናን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲሞሉ ስማስቻል የታሰመውን ራእይ እውን ለማድረግ ከሚያግዙ ነገሮች አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

ከዚህ በታች ከተመለከተው ሠንጠረዥ ራእይ ያለውን ዕቅድና ራእይ የሌለውን ዕቅድ እነጻጽር

| **ራእይ የሌላቸው ዕቅዶች** | *ራእይ ያላቸው ዕቅዶች* |
|---|---|
| 1. በዚህ ዓመት አንድ ወንጌላዊ፣ በ5 ዓመታት ውስጥ 5 ወንጌላውያን መላክ።<br>2. ቤተ ክርስቲያናችንን ቆርቆሮ ማልበስ።<br>3. አዲስ የመዘምራን ልብስ መግዛት።<br>4. 30 ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት።<br>5. ኮንፈረንስ ማካሄድ።<br><br>*ማብራሪያ 1* | *ራእይ፡- ቤተ ክርስቲያናችን ለሰዎች ሁሉ ወንጌልን በማዳረስ አገልግሎት ላይ ትሳተፋለች።*<br>ዕቅዶች፡-<br>1. እያንዳንዱ አባል እምነቱን ስጎረቤቱ እንዲያካፍል እናሠለጥነዋለን።<br>2. በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚሠሩ ወንጌላውያንን ስመላክ ገንዘብ እናሰባስባለን።<br>3. ስጦታ ያላቸውን ሦስት ሰዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንልክና ሲጨርሱ (በሦስት ዓመት ውስጥ) በወንጌላዊነት እንልካቸዋለን።<br><br>*ማብራሪያ 2* |

በእነዚህ ሁለት ዕቅዶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ተመልከት። በመጀመሪያው ማብራሪያ ውስጥ በሚቀጥለው አንድ ዓመት ወይም አምስት ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያናችን እንድታከናውን

የምንፈልጋቸውን ነገሮች ዘርዝረናል። ነገር ግን ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮች ራእይ አልገለጽንም። ግልጽ ራእይ ከሌለ፣ የዘረዘርናቸው ሥራዎች ብዙም ለውጥ አያመጡም። ለምሳሌ ያህል፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አምስት ወንጌላውያንን በመላካቸው እግዚአብሔር እንዲሆኑ የፈለገውን ዓይነት አብያተ ክርስቲያን ሆነን ተገኝተናል ብለው ያስባሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉም አማኞች እንዲመሰክሩለት አይፈልግምን? ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት የማይመሰክሩ ከሆነ፣ የወንጌልን ስርጭት በትጋት የምናካሂድ ቤተ ክርስቲያን ነን ማለት ይቻላል? ራእይ ሳይኖር እግዚአብሔርን በብቃት ማገልገል አለማገልገላችንን መገምገሙ አስቸጋሪ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ጣሪያ አዲስ ቆርቆሮ በማልበስ ወይም አዲስ የመዘምራን ልብስ በመግዛት ለመፈጸም የምንፈልገው ተግባር ምንድን ነው? አስፈላጊው ነገር ይኸው ነው? ግልጽ ራእይ ከሌለን፣ ጊዜያችንንና ሀብታችንን ለየትኛው አገልግሎት በቀዳሚነት እንደምናውል ለመወሰን እንቸገራለን። ያለንን ገንዘብ ሁሉ ለቆርቆሮና ለመዘምራን ልብስ መግዣ ካዋልን በኋላ፣ ምናልባትም ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው ለምንለው የወንጌል ስርጭት ምንም ገንዘብ ላይተርፈን ይችላል። ወይም ዓላማው ምን እንደ ሆነ ሳናስብ ኮንፈረንስ ልናካሂድ እንችላለን። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ዓይነት የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ይጀምሩና በቀጣዩ ዓመት ሌላ ዓይነት የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ያካሂዳሉ። ይህንንም የሚያደርጉት የትኛው ውጤታማ እንደ ሆነ ሳይገመግሙ ወይም በደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ምን ውጤት ሊያመጡ እንደሚፈልጉ ሳያውቁ ነው። የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ምን ዓይነት ውጤት ለማየት እንደሚፈልጉ ሳያውቁ የሚያካሂዱት ተግባር ብዙ ጥረቶችን ያባክናል። ፕሮግራሙም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት እውነተኛ ለውጥ ሳያመጣ ይቀራል። ጥሩና ዘለቄታዊ ዕድገት እንዲኖር ከተፈለገ፣ ወደየትኛው አቅጣጫ ለማደግ እንደምንፈልግ በግልጽ ማወቅ አለብን።

በሁለተኛው ማብራሪያ ውስጥ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እኛም ሆንን እግዚአብሔር ምን እንደምንፈልግ በግልጽ ተቀምጧል።



ግባችንን ካወቅን በኋላ፣ ራእዩን እውን ለማድረግ የሚያስችሉንን የተለያዩ ነገሮች ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ ያህል፣ ቤተ ክርስቲያናችን በወንጌል ስርጭት ላይ በብቃት እንድትሳተፍ ከፈለግን፣ አባሎቻችን እምነታቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለሌሎች እንዲያካፍሉ ልናሠለጥናቸው እንችላለን። በኢትዮጵያና በሌሎችም የዓለም ክፍሎች ወንጌላውያንን ለመላክ የሚያስችል ገንዘብ እንዲሰጡ ልናበረታታቸው እንችላለን። ከቤተ ክርስቲያናችን ውስጥም ስጦታ ያላቸውን ሰዎች መልምለን በወንጌል ስርጭት እናሠለጥናለን። ቤተ ክርስቲያን ትጉሕ ወንጌል አገልጋይ እንድትሆን ለማድረግ ሌሎችም የምናከናውናቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ።

> 38ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚቀጥለው ዓመት እንዲከናወኑ የሚፈልጓቸውን ነገሮች እየዘረዘሩ፣ እንዲከናወኑ ለሚፈልጓቸው ነገሮች ግልጽ ምክንያት ወይም ራእይ የማያስፍሩባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ። ለ) ሁስቱን ሁንጠረዦች አነጻጽርና ለማከናወን የምትፈልገውን ራእይ ለይተህ ካወቅህ በኋላ ዕቅዶችን ማውጣት የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ዘርዝር።

## እምስተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ውይይት በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

### ሳምንታዊ ስብስባ

### የውይይት ጥያቄዎች:-

1. ሀ) የአመራር ክህሎትን ማዳበር ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ግለጽ? ለ) አንድ መሪ ቤተ ክርስቲያን የመምራት ክህሎት ማዳበሩ ለምን ያስፈልጋል? ሐ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአመራር ክህሎት የሌላቸው ለምንድን ነው? መ) ሽማግሌዎች የአመራር ክህሎት እንዲያዳብሩ ቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ልታደርግ ትችላለች?

2. ሀ) ነህምያ የአመራርን ክህሎት ያሳየው እንዴት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያንን በክህሎት ስለ መምራት ከነህምያ የምንማራቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

3. ሀ) ራእይ ያለው አመራር ከማስተዳደር ስጦታ እንዴት ይለያል? ለ) እነዚህ ሁለት የተለያዩ ስጦታዎችን የተለያዩ ሰዎች ሲጠቀሙ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) ራእይ ያላቸው መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ለጤናማ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚያስፈልጉ ግለጽ:: መ) ራእይ ያላቸው ሽማግሌዎች የሚገኙበት ቦርድ እና አስተዳዳሪዎች ያሉበት ቦርድ እንዴት እንደሚሠራ አብራራ:: ሠ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቦርዶች የትኛውን ይመስላሉ? ለመልስህ ምክንያትህን ዘርዝር::

4. ሀ) ለአንድ የተለየ አገልግሎት «ራእይ» ያለው አመራር መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚችሉትን የተለያዩ ራእዮች ዘርዝር:: ሐ) ለአብያተ ክርስቲያናት የአገልግሎት ራእይ መያዝ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? መ) ራእይ ከዕቅድ እንዴት ይለያል? ሠ) ዕቅዶቻችንን ከማውጣታችን በፊት ራእይ ማውጣት ሥራችንን የተሻለ የሚያደርገው እንዴት ነው?

5. ሀ) አማኞች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል «ራእይ» ሊኖራቸው የሚገባው እንዴት ነው? የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ያልሆኑ አማኞች እግዚአብሔር በሥራቸው እንዴት እንዲጠቀምባቸው እንደሚፈልጉ ራእይ ቢያወጡ እንዴት ሊሰወጡ እንደሚችሉ ግለጽ:: ለ) ለአገልጋዮች እግዚአብሔርን እንዴት ሊያገለግሉት እንደሚፈልጉ ራእይ ማዘጋጀት ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ:: ሐ) እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በሥራ ቦታውም ሆነ መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በመጠቀም ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግ የግል ራእዮቹን ይናገር::



# ትምህርት ዘጠኝ

## አንደኛ ቀን

ማንም ቢሆን የሚሄድበትን ቦታ ሳያውቅ ፈረስ ላይ አይወጣም፣ ወይም ታክሲ ላይ አይሳፈርም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ማንኛውም መሪ የት እንደሚወስዳቸው ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት የለበትም:: ለዎችን በክህሎት ለመምራት የመጀመሪያው እርምጃ ወዴት እንደምንመራቸው ማወቅ ነው:: ዛሬ መሪዎች እግዚአብሔር ሕዝቡን ወዴት እንዲመሩ እንደሚፈልግ ማወቅ እንዳለባቸው የሚያመለክተውን ግልጽ ራእይ የማውጣት ጥናታችንን እንቀጥላለን::

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) የሽማግሌዎች ቦርዳችሁ በራእይ የመምራት ክህሎት ያለው ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ለ) አንተ የቤተ ክርስቲያንህ የሽማግሌዎች ቦርድ ሰብሳቢ ነህ እንበል:: 1) እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችሁ ያለውን ራእይ በመረዳቱ ረገድ ምን ዓይነት ሚና ይኖርሃል? 2) ለቤተ ክርስቲያናችሁ የእግዚአብሔርን ራእይ ለመንደፍ ሌሎች ሽማግሌዎችስ ምን ሚና ይኖራቸዋል? 3) ራእይ በመንደፉ በኩል የአባላትስ ሚና ምን ይሆናል? ረ) ራእዩን በመግለጹና በመወሰኑ ረገድ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን ሊሆን ይችላል? መሪዎች የግል ፍላጎታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስንም እየሰሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት እንዴት ነው?

## ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በመንደፉ በኩል የመሪዎች ሚና

1. መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ራእይ ያለው አመራር መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለት ዓበይት የመሪነት ሚናዎች አሏቸው::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ «ራእይ ያላቸው መሪዎች» ናቸው:: በሕይወታቸው፣ በማስተማር ተግባራቸውና በሚሰጧቸው ውሳኔዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት የእግዚአብሔርን ፈቃድ